
የድርጅቱ ሃምሳ ዓመት የሚከበርበት የዛሬው ዕለት በድርጅቱ ታሪክ
እንደ ሁነኛ ምዕራፍ የሚያዝ ነው። በርግጥ የዛሬ ቀን ሊታወስ
የሚገባው ልዩ ቀን ነው። ይህ ሽልማት ለሕዝባችን፣ ለኢትዮጵያ
ሀገራችን ፣ ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክር[illegible]ያናችንና ለመላው
አፍሪካ አንድ ታላቅ ክብ[illegible] ነው።





ብፁዕ ወቅዱስ ዶክተር አቡነ ጳውሎስ የ2000 ዓ.ም (UNHCR) የናንሰን
ሜዳሊያ የአፍሪካ ተሸላሚ በሽልማቱ ሥነ-ሥርዓት በአፍሪካ አዳራሽ ንግግር ሲያደርጉ



© Safeguarding Religious Treasures of the Ethiopia Orthodox Church

# ፈለገ ጥበብ





[illegible] ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org

# እኛና እናንተ

## ጥምቀት ወይስ ሻወር

ውድ የፈለገ ጥበብ አዘጋጆች እንደምን አላችሁ? ይህችን ጽሑፍ እንድንጽፍላችሁ ያነሣሣን የተጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ይዞ በወጣ መጽሔት ላይ ያነበብነው ጽሑፍ እጅግ ስላሳዘነን ነው። ይኸውም በገጽ ፲፩ ተራ ቁጥር ፯ ላይ በአማርኛና በገጽ ፳ ቁ.፪ ላይ በእንግሊዝኛ የደብሩ የልማት እንቅስቃሴ በሰፈረ ጽሑፍ ላይ ለክርስትና ማስጠመቂያ ገንዳና የውኃ ማሞቂያ ማሠራቱን፤ በዚህም ምዕመናን እየተደሰቱ ልጆቻቸውን በማስጠመቅ እንዲጠቀሙበት እንዳደረገ ይናገራል።

ጌታ ጥምቀቱን በዮርዳኖስ ወንዝ በውሃ ነው ያደረገው። ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንም ጥምቀት በተዘቀዘ ውሃ እንደሚደረግ ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች። ጥምቀት በውኃ ያውም በተዘቀዘ መደረጉ ሁሉም በተላለ [illegible]

[illegible]

ከአዘጋጁ [illegible]

[illegible]

## አደራዬ የጠበቀ ነው።

የእግዚአብሔር አብ ሥላሴ የወልድ ፍቅር የመንፈስ ቅዱስ በረከት በእናንተ በአዘጋጆች ላይ ዘወትር ያድር ዘንድ ምኞቴን እገልጻለሁ።

ውድ አዘጋጅ በእውነቱ ስለመጽሔቷ አስተማሪነት በኔ ብዕር ለመግለፅ የሚቻል ብቻ ሣይሆን አይሞከርምም። እኛ የመንፈስ ቅዱስን በረከት እንድናወቅ ስለምታደርጉት አገልግሎት የመላእክት ተራዳኢነት የእመቤቴ ቅድስት ድንግል አማላጅነት ከእናንተ ጋር ይሁን ከማለት በስተቀር ቃላት የለኝም።

ውድ አዘጋጅ ከዚህ በመቀጠል በሚቀጥለው እትም እንዲያብራሩልኝ የምፈልገው በ፫ኛ ዓመት ቁጥር ፮ መስከረም –ኅዳር ፲፱፻፺፫ ዓ.ም መጽሔት ላይ ስለወጡት የፊት ለፊት ሽፋንና የጀርባው ሽፋን ሥዕል ጉዳይ ነው። ከፊት ሽፋን ላይ የተሣለው መስቀል እናት ላይ የተሣሉት ርግብ መሰል ቅርፆች ምንን ያመለክታሉ? ከጀርባው ሽፋን ላይ ከተገለጸው ሥዕል መካከል?

፩. ከጻድቁ አባታችን ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ሥዕልና ከጻድቁ አባታችን አቡነ አረጋዊ ሥዕል መሐከል ያለችዋ የሴት ሥዕል ምንድናት?

[illegible]

ከአዘጋጁ [illegible]

[illegible]

## አንድ በሉን

[illegible]

ከአዘጋጁ [illegible]

[illegible]

የፊት ለፊት ሽፋን (የእመቤታችን) ፎቶ በግርከ [illegible]

www.ethiopianorthodox.org

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትም/ቤቶች ማደራጃና ማስተባበርያ መምሪያ

በየ፫ ወሩ የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት

# ፈለገ ጥበብ

፫ኛ ዓመት ቁጥር ፯

ጥር – መጋቢት ፲፱፻፺፫ ዓ.ም

ማውጫ

የዓለማችን አሳሳቢ ጉዳይ . . . . . . . . . . ፪
ቃለበረከት
እኔም እንደ ጓደኞቹ ሁሉ ስምንት ዓመታት በእስር ቤት . . . . . . . . ፫
«እምነ ጽዮን ይብል ሰብእ» ሰው ሁሉ ጽዮን እናታችን ይላል . . . . . . . . ፮
መግረሬ ፀር
ልደተ ክርስቶስ የሚከበረው በ፳፱ ወይስ በ፳፰? . . . . . . . . ፲፩
ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን
የጥምቀትን ጥቅም የተረዳው ይኖር ይሆን? . . . . . . . . ፲፫
ትምህርተ ሃይማኖት
ማመን ከመስማት ነው . . . . . . . . ፲፮
እኔም ወጣት ነበርኩኝ
ለ፵፩ ዓመታት በቤተ ጉባኤ . . . . . . . . ፲፯
ዘመነ ሰብከት . . . . . . . . ፳፩
ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር
ሁሉም መርከብ ይሥራ . . . . . . . . ፳፫
ትምህርተ ኖሎት . . . . . . . . ፳፮
ከወጣቱ ለወጣቱ
የእግዚአብሔርን ስጦታ ከማንም ጋር ልናወዳድረው አንችልም . . . . . . . . ፳፰
ዜና መጽሔት . . . . . . . . ፴
እስትጉቡዕ
የጎሩይ ጊዮርጊስ ደብር አመሠራረት . . . . . . . . ፴፫
እኛና እናንተ . . . . . . . . (የሽፋኑ ፪ኛ ገጽ)

አርታዕያን (ኤዲተሮች)
ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁ
መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ
ቀሲስ በላይ ትጋት

አዘጋጆች
ዋና አዘጋጅ መምህር ዕንባቆም ተክሌ
ም/ዋና አዘጋጅ መልአከ ሰላም ኃይሉ ኢየሱስ ከበደ
ስልክ 55-26-52 ፣ 55-00-98 ፣
55-00-99 EX 46
ፖ.ሣ.ቁ. 81286 – አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

ርዕሰ አንቀጽ

# የዓለማችን አሳሳቢ ጉዳይ

ዛሬ በዓለማችን ትልቁ የመወያያ አጀንዳ ሆኖ የሚገኘው በቀሳፊነቱ ወደር ያልተገኘለት የኤድስ በሽታ መስፋፋት ጉዳይ ነው።

የዓለማችን ጠበብትም ከዚህ በሽታ የሚያድን መድኃኒት ለማግኘት ብዙ ጥረዋል፣ ደክመዋል። ውጤቱ ግን እንደ ተጠበቀው አልሆነም። ለዚህም ይመስላል ጠበብቱ አንድ ወንድ በአንዲት ሴት፣ አንዲት ሴት በአንድ ወንድ ጸንቶ መኖር ወደሚለው መርህ እንዲያዘነብሉ ያደረጋቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን እግዚአብሔር ሰብአ ትካትን በንፍር ውሃ የቀጣ በዚሁ በዝሙት ጠንቅ ነው። ሰብአ ሰዶምም በሰዶማዊ ግብራቸው ምክንያት ከሰማይ እሳት ወርዶ በላቸው።

አሁንም የመቅሰፍቱ ዓይነት ይለያይ እንጂ ዓለማችን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ. ቸል በማለቱ በራሱ ላይ የመቅሰፍት እሳት አቀጣጥሏል። ሰው በገዛ ራሱ ያቀጣጠለውን እሳት ለማጥፋት አልቻለም፤ ሰው ብርቱ ሲባልም በኤድስ በሽታ ግን ተሸንፏል (ዘሌ.፳፮፥)።

ዛሬ በዓለማችን ከ፴፩ ሚልዮን በላይ ሕዝቦች የዚሁ በሽታ ሰለባ እንደሆኑና ከዚህም ከ፳፫ ሚሊዮን በላይ በአፍሪካ የሚገኙ መሆኑን የዓለም ዜና አውታር በሰፊው ዘግበውታል። በሀገራችንም በዚህ በሽታ የተያዙት ከ፫ ሚሊዮን በላይ መድረሳቸው ነጋ ጠባ እየተነገረ ነው። ሚሊዮን በላይ መድረሳቸው ነጋ ጠባ እየተነገረ ነው። በጥቂት ዓመታት ይህን ያህል ወገን ማጣት፣ እጅግ አስደንጋጭና አሳዛኝ ድምፅ ነው።

የምንወዳቸውና የምናፈቅራቸው ወገኖቻችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በኤድስ በሽታ ምክንያት ሳንወድ በግድ ከጉያችን በሞት እየተነጠቁ ናቸው።

በሽታው የሚፈጥረው ውስብስብነት እጅግ የከፋ ሆኖአል። ምክንያቱ በአብዛኛው ለበሽታው የተጋለጡ ወገኖች የሀገሪቱ አምራች ኃይል የሆኑት ከ፲፭–፵፱ ዕድሜ ያላቸው በመሆኑና ሕፃናትን አባት እናት አልባ ማድረጉን፣ አረጋውያንን ጧሪ ቀባሪ ማሳጣቱ ነው። ውሃ የሌለው ወንዝና ሰው የሌለው ሀገር ምድረ በዳ እንደሚሆን ሁሉ ተተኪ የሌለው ትውልድም እንደዚያው ነው። ሰው ከሌለ ልማት ብሎ ነገር የለም። ሀገር ብሎ ነገር ከቶ ሊኖር አይችልም። ልማት የሚኖረው፣ በሀገር ብቁ ዜጋ ሲኖር ነው። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል እንደመሆንዋ መጠን ከብዙ ዘመናት ጀምሮ «አታመንዝር» የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል በማስተጋባት የምታስተምረው፤ ሰው ሁሉ በሕገ እግዚአብሔር ተወስኖ፤ በቅድስናና በንጽህና እንዲኖር ነው። አሁንም የኤድስን በሽታ ከምድረ ኢትዮጵያ እናጠፋለን ብለን ከተነሣን የመንግሥት ተቋማትና በጎ አድራጊ ድርጅቶች ሁሉ ከዚህች ቤተክርስቲያን ጋር በሁለንተናው አብረው መሥራት ይገባቸዋል።

ዛሬ ኤድስን ለመከላከል በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርካችን ብርቱ ጥረት እየተከናወነ ያለው ሰፊ አገልግሎትና እንዲሁም በልማት ኮሚሽንና በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ እጅግ አበረታችና ተስፋ የሚጣልበት ነው። አብዛኛው ወጣት በሰንበት ትምህርት ቤቶች የታቀፈ እንደመሆኑ መጠን መምሪያው ሁኔታዎች ከተመቻቹለት ባለው መዋቅር መሠረት ከአሁን በበለጠ ብዙ ሊሠራ ይችላል። እዚህ ላይ መልስ ማግኘት የሚገባው ጥያቄ ኤድስን ከምድረ ኢትዮጵያ እንዴት አድርገን እናስወግደው? የሚለው ነው።

በእኛ በኩል መወሰድ ይገባቸዋል ብለን ያመንባቸው፡

፩. መንግሥትና ቤተክርስቲያን በዚህ በሽታ እንቅስቃሴ ላይ አንድ ወጥ መርሐ ግብር ቢያዘጋጁ፣

፪. ሁሉም ኅብረተሰብ በሽታውን ለማጥፋት ራሱን ከኤድስ አደጋ መጠበቅ የሚያስችለው በቂ ግንዛቤ ቢኖረው፣

፫. ለአዲሱ ትውልድ በየትምህርት ቤቱ የሥነ ምግባር (ግብረገብ) ትምህርት እንዲሰጥ ቢደረግ፣

፬. የነበረውን የመከባበር ባሕል ቢያዳብር፤

፭. ስለ ኤድስ በሽታ የሚሰጠው የትምህርት ስርጭት በከተሞች ብቻ ሳይሆን በገጠሩም በአግባቡ እንዲሰጥ ትኩረት ቢደረግበት፣

፮. አደንዛዥ ዕፅን በሚያዘዋውሩና በሚወስዱ ሰዎች ሕጉ ጠንካራ በሆነ ክትትል ተግባራዊ የሚሆንበት መንገድ ቢመቻች፣

፯. ዝሙትን የሚያስፋፉ የባሕር ማዶ ማስታወቂያዎችና የቪዲዮ ፊልሞች በአጠቃላይ ድንበር ዘለል ባህሎች ፈጽሞ ቢከለከሉ የሚሉ ናቸው፣

ከዚህ ውጭ ግን ኮንዶምን እንደ መፍትሔ መውሰድ በተዘዋዋሪ መንገድ አመንዝራነትን ከማስፋፋት አልፎ በየትኛውም አቅጣጫ መድኃኒት ሆኖ አልተገኘምና ሊታ_ ሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው እንላለን።

እንግዲህ ከላይ እንደተገለጸው የበሽታው ስርጭት ከጊዜ ወደ ጊዜ በጣም እየሰፋ መጥቷል። የመከላከሉ ጥረት ግን ገና አሁን ነው የተጀመረው ለማለት ያስደፍራል። ብዙ ወገኖቻችን ከዚህም የተነሣ በሽታው ብዙ ቀድሞናል። ብዙ ወገኖቻችን በምን እንደሞቱ እንኳን ሳይታወቅ ከመካከላችን ተነጥለ[illegible] ምን እ[illegible]ቅን ነው?

# እኔም እንደ ጓደኞቼ ሁሉ፣ ስምንት ዓመታት በእስር ቤት

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀጳጳስ ዘአኩስም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ኅዳር ፲፱ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽን በአፍሪካ አዳራሽ የናንሰን ሽልማት በተሸለሙበት ጊዜና መስከረም ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ለአትሌቶቻችን አቀባበል ባደረጉበት ጊዜ ያስተላለፉት ቃለ በረከት፦



ብፁዕ ወቅዱስ ዶ/ር አቡነ ጳውሎስ የ2000 ዓ.ም (UNHCR) የናንሰን ሜዳሊያ የአፍሪካ ተሸላሚ በሽልማቱ ሥነሥርዓት ላይ በአፍሪካ አዳራሽ ንግግር ሲያደርጉ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

ክቡር አቶ ዳዊት ዮሐንስ

የተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ

ክቡር አቶ ሥዩም መስፍን

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

ወይዘሮ ዞቢዳ ሐሲም አሻግሬ የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽን የኢትዮጵያ ተወካይ

ክቡራትና ክቡራን

በመጀመሪያ ለግማሽ ምዕተ ዓመት ስደተኞችን ሲረዳና ሲንከባከብ የቆየው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የስደተኞች ኮሚሽን የናን ሰንን ሜዳሊያ ስለሸለመኝ ጥልቅ ምስጋናዬን ላቀርብ እወዳለሁ። የድርጅቱ ፶ኛ ዓመት የሚከበርበት የዛሬው ዕለት በድርጅቱ ታሪክ አንድ ሁነኛ ምዕራፍ የሚይዝ ነው። በርግጥ የዛሬ ቀን ሊታወስ የሚገባው ልዩ ቀን ነው። ይህ ሽልማት ለሕዝባችን ለኢትዮጵያ ሀገራችን ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ ለሀገራችን የሃይማኖት ተቋማትና ለመላው አፍሪካ አንድ ታላቅ ክብር ነው።

እንግዳ ሆኜ ተቀበላችሁኝ (ማቴ. ፳፭፥፴፭) ይህ ቃል በዕለተ ምጽአት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለጻድቃን የተናገረው ነው። ይህ የሰው ልጅ ደግነት የመጨረሻው መለኪያ ነው። ከሁሉም ይልቅ እንግዳን፣ ስደተኛን መቀበል ማስተናገድ የቱን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ አበክሮ ይገልጻል።

ስደተኛ ማለት የሚወደውን ነገር ሁሉ ያጣ ማለት ነው። ከሀገሩ፥ ከቀዬው ተፈናቅሎ፣ ከሚወዳቸው ሁሉ ተለይቶ፥ ከተወለደበት ምድርና ከየሚያፈቅራቸው ነገሮች ሁሉ አጥቶ፣ በባይተዋርነት የሚንከራተት ስደተኛ አንዳች የቀረው ነገር የለውም። ስደተኛ መሆን ይንጠለጠሉበት በሌለው ባዶ ሕዋ ውስጥ ተገፍትሮ እንደመጣል ነው። ተስፋ አልባ ባዶ ሕይወት ነው።

የስደተኝነት መንሥኤ ለሁላችንም ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ በደርግ ዘመን ኢትዮጵያውያን ስላጋጠማቸው ችግር አንዳንድ ነጥቦችን ለማንሳት እሻለሁ። በዚያን ዘመን ሀገራችን፣ ሕዝባችንና ቤተ ክርስቲያናችን ከፍተኛ ችግር ላይ ወድቀው ነበር። በቀይ ሽብር፣ ጭቆናና ጦርነት የተነሳ አያሌ ኢትዮጵያውያን ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል። ተሰድደዋል፣ ሞተዋልም። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ከቅርብ ጊዜ በፊት በተለያዩ ሀገሮች በተለይም በክፍለ ዓለማችን አፍሪካ በሩዋንዳ፣ ሴራሊዮን፣ ኮንጎ፣ ደቡብ አፍሪካ ወዘተ...አሰቃቂ እልቂት፣ የሩዋንዳ ወታደሮች ጭካኔ በተመላበት ሁኔታ እጆቻቸውና እግሮቻቸው ተቆርጧል።

እኔም እንደ ሌሎች ጓደኞቼ ሁሉ፣ ስምንት ዓመታት በእስር ቤትና በቁም እስር ከዚያም አስር ዓመት በስደት ያሳለፍኩት በደርግ ዘመን ነበር። በስደተኝነት ዘመኔም ከብዙ የሥራ ጓደኞቼ ጋር የመሰል ስደተኞችን ችግር በማቃለልና በማጽናናት ረገድ በሠፊው ተንቀሳቅሰናል።

ከዚህም ሌላ ከቅርብ ጊዜ በፊት በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል

www.ethiopianorthodox.org

ግጭት በተፈጠረበት ጊዜ አንስቶ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች የኢትዮጵያ የሃይ ማኖት መሪዎች ጋር በመሆን ችግሩ በሰላም እንዲፈታ ብርቱ ጥረት አድ ርጋለች። እኛ የሁለት ሀገሮች የሃይ ማኖት መሪዎች በተከታታይ በኖ ርዌይ፣ ጀርመን፣ ፈረንሳይና በአሜ ሪካ ብዙ ስብሰባዎች ካካሄድን በኋላ የጀመርነውን የሰላም ውይይት በመቀ ጠል ዘላቂ በሁለቱ ሀገሮች ሕዝቦች መካከል ሰላም፣ እርቅና ስምምነት ለማምጣት እንደምንጥር ተስማም ተናል።

በኢትዮጵያ የሃይማኖት መሪዎች ስም የኖርዌይ ቤተ ክርስቲያን የርዳታ ድርጅት ስብሰባዎችን ሁሉ በማዘ ጋጀትና በማሳካት ላደረገው ከፍተኛ ጥረት ከልብ ላመሰግን እወዳለሁ።

ወደ ስደተኞች ጉዳይ ስንመለስ፣ በአሁኑ ወቅት ሚሊዮኖች በየቦታው እየሮጡ ናቸው። ብዙ ሺህዎች በየዋ ሻው ተጨናንቀው ይታያሉ። ብዙ መቶዎች ደግሞ በአልባሌ ካምፖች የስቃይ ኑሮ ይገፋሉ። በርግጥ፣ ድረ ሱልኝ እያለ የሚጣራ ታላቅ ተንሳፋፊ የሰው ልጅ ክምችት ነው። የችግሩ ዓለም አቀፋዊ ይዘት፣ የጭካኔው ክፋትና የመብት ዕጦቱ ስፋት የሰውን ልጅ የርኅራኄ ስሜት ያደነዘዘው ይመ ስላል። ይሁን እንጂ፣ በእግዚአብሔር አምሳልና አርአያ የተፈጠረና ባልን ጀራውን እንደራሱ እንዲወድ በእግዚ አብሔር የታዘዘ የሰው ልጅ የወን ድሞቹና እህቶቹ ስቃይ አይሰማውም ብሎ ለመገመት ያስቸግራል።

አሁን ትልቁ ጥያቄ የስደተኞችን ችግር ለማቃለል ምን መደረግ አለበት የሚለው ነው። የሚከተሉትን ርም ጃዎች በመውሰድ ችግሩን ከመሠረቱ መዋጋት ያለብን ይመስለኛል። ተቀዳ ሚው ርምጃ ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ የሚለውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸም ነው። ራሱ ፍቅር የሆነው እግዚአብሔር (ዮሐ.፩፥፰) ሰውን የፈጠረው ርስ በርሱ እንዲፋ ቀርና እንዲተሳሰብ እንጂ እንዲ ጠፋፋና አንዱ ሌላውን እንዲጨቁን አይደለም። የሰው ልጅ ልቡንና ሕሊናውን ወደ እግዚአብሔር በመመ ለስ የርስ በርስ መዋደድን ዘላቂ ጥቅም ሊያስታውስ ይገባል። ከዚህም በቀር የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር አስተዋይ ሕሊና ተሰጥቶታል። ይህም በሰው ልጅ ነፍስ ውስጥ ያለ የእግዚአብሔር ድምፅ በመሆን ሁል ጊዜ መልካም ነገር እንዲሠራ ይገፋፋዋል።

እግዚአብሔር አምላክ ለሰው ልጅ በፍቅር ሊጠቀምበት የሚቻ ለውን ሠፊ ዓለም አሟልቶ ስለሰጠው ጠብ የሚያበቅልበት ምክንያት ባል ኖረው ነበር። ሰው በተፈጥሮው ማኅበ ራዊ ፍጡር ስለሆነ ነገዶች አብሮ መኖርን ሊማሩ ይገባል። ማኅበረሰቦች ከመተላለቅ የሚገኝ አንዳችም ትርፍ እንደሌለ ሊያስተውሉ ይገባቸዋል። መንግሥታት የጥፋት፣ የጭካኔ፣ የስቃይና የኃዘን ሁሉ እናት የሆነው ጦርነት ከቶውንም ዕድገትን እንደ ማያስገኝ ማወቅ ይኖርባቸዋል። የሚ ያስገኘው ነገር ቢኖር ስደተኛን፣ አካለ ጐደለውንና ተስፋ የለሹን ሰው ብቻ ነው። ስለዚህ የስደተኝነት ችግር ይቃለል ዘንድ የሰው ልጅ ቅዱሱን የእግዚአብሔር የሕይወት ሥርዓት በሚገባ ተገንዝቦ በሰላም አብሮ ለመኖር መቻል አለበት። የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አምላክ የላቀ ፍቅርና ጥበብ በክብር የተፈጠረ ስለሆነ መብቱ ሊጠበቅለት ይገባል። የሰብአዊ መብት መጣስና የፍትሕ መጓደል የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፃረር ድርጊት ከመሆኑም በላይ ለሕዝብ በብዛት መፈናቀል ምክንያት ነው። ስለዚህ ዲሞክራሲ፣ ብልህ አመራር የሠፈነበትና ለሕዝብ ተጠያቂ የሆነ መልካም አመራር በ[...]

ሊሠፍን ይገባል። መንግሥታትና ማኅበረሰቦች ሕዝቦች በገዛ ሀገራቸው ሕዝብ መካከል በሰላም ተረጋግተው የመኖር መሠረታዊ መብታቸውን ሊያከብሩ ይገባል።

የስደተኞችን ችግር ማቃለያ ዋነ ኛው መፍትሔ ስደተኞችን ወደ ትው ልድ ሀገራቸው መመለስ ነው። ይህ ይሆን ዘንድ የመንግሥታት በጐ ፈቃድ፣ በቂ ገንዘብ መመደብና ሰላማ ዊና ምቹ ሁኔታ መፈጠር አለበት። ቀላል ሥራ አይደለም። ከመንግ ሥታት፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና ከሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ቁርጠኝነትና ራእይን ይጠይቃል።

ባጠቃላይ፣ የስደተኞችን ችግር ለማቃለል የውጭ ሰዎችን የመጥላት የዘረኝነት አዝማሚያ መወገድ ይኖር በታል። እየተናጋ ያለው የሰው ልጅ ማኅበረሰብ የሞራል መሠረት ስደተ ኞችን በመርዳት በማበረታታትና በማስተማር ሊጠናከር ይገባዋል።

ከሁሉም በላይ መንግሥታት ሰላምን፣ ፍትሕን፣ መገንባት አለባ ቸው። በዚህ አጋጣሚ መንግሥታት ራሳቸው በእግዚአብሔር ፈቃድ የተሾሙ መሆናቸውንና በመሠረቱ አመራር የሰላም ተልዕኮ መሆኑን በማሰብ የእግዚአብሔርን ሕዝቦች በትክክል እንዲያስተዳድሩና ስደተኝ ነትንና እርሱም ለሚያስከትለው ስቃይ መንሥኤ የሚሆኑትን ምክን ያቶች እንዲያስወግዱ ጥሪያችንን እናቀርባለን። በመንግሥታትና ማኅበ ረሰብ መካከል ሰላምና ፍትሕ ካል ሠፈነ የስደተኝነት ማዕበል ሊገታ አይችልም። ጥላቻና ብጥብጥ የሚፈ ጥሩት የጥል ግድግዳ ፈርሶ (ኤፌ. ፪፥፲፬) በሰላም ባህል መተካት አለበት።

በዚህ አጋጣሚ የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽን አመራርና ሠራተኞቹ ለሃምሳ ዓመት



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ከሚስተር ካሉዶ ዶሀርቲ የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር (UNHCR) አፍሪካ ዳይሬክተር እጅ የናንሰን ሜዳሊያ ሲቀበሉ

ዕድሜ በሚልዮን የሚቆጠሩ ስደተኞችን በመርዳቱ በድጋሚ ላመስግን እወዳለሁ። በዚህ ሂደት ብዙዎቹ የሌሎችን ሕይወት ለመታደግ ሲሉ ውድ ሕይወታቸውን አሳልፈው መስጠታቸው ሊታወስ ይገባል።

ይሁን እንጂ ሕይወታቸውን አሳ ልፈው የሰጡት ከሁሉም ዓላማዎች ለላቀው ነው። (ማቴ.፲፥፴፱) በታላቅ ክብር እናስባቸዋለን፣ እግዚአብሔር ነፍሳቸውን በሰላም እንዲያሳርፍ እንጸልያለን። ድርጅቱ የተጓዘው «የማይቻል ጉዞ» አርኪና ውጤታማ ነበር። ዳሩ ግን አሁንም «የማይቻል ጉዞ» ከፊቱ ይጠብቀዋል። ሆኖም ካለው ጽናት፣ የተካበተ ልምድና ቆራጥነት ጋር በቂ ገንዘብ ከተመ ደበለት ፈተናውን በሚገባ እንደ ሚወጣ ዕኑ እምነት አለን።

እኔ በበኩሌ፣ መንግሥታት አንዳ ችም ስደተኛ ባይኖራቸው ምንኛ ደስ ባለኝ ነበር። ነገር ግን በታሪክ እንደተመለከተውና እንዳነበብነው የሰው ልጅ ተፈጥሮ አስቸጋሪ ስለሆነ ይህ ምኞት ተምኔታዊ ሊመስል ይቻ ላል። ሆኖም ከትውልድ ሀገራቸው ኃይል የተፈናቀሉትን መልሶ ለማቋ ቋምና ከኅብረተሰቡ ለማቀላቀል የተባ በሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚ ሽን የሚከተሉትን ርምጃዎች እንዲ ወስድ በትሕትና ሐሳብ አቀርባለሁ።

ለስደት ተመላሾች ልጆች ትምህ ርት ቤት እንዲቋቋም

ለስደት ተመላሹ ማኅበረሰብ ክሊኒኮችና አስፈላጊ ተቋማትን ማደራጀት።

ከፍተኛ ትምህርት ሊገበዩ እንዲ ችሉ የስኮላርሺፕ ትምህርት መከ ታተል የሚያስችል ገንዘብ እንዲ መደብ፣

ሰብአዊ ክብራቸውንና በራስ የመተማመን ስሜታቸውን ሊያዳብር የሚያስችል፣ መንፈሳዊ፣ ሞራላዊና ባህላዊ ርምጃ መውሰድ፣

ተመላሾችን ሙሉ በሙሉ ሊያቋ ቁማቸውና ከኅብረተሰቡ ሊቀላ ቅላቸው የሚያስችል እንዲህ ዓይነቱ ሁለገብ ርምጃ ካልተወሰደ፣ የግብር ይውጣ ርምጃዎች ብቻ ራሳቸውን እንዲችሉ አያደርጋቸውም፣ በገዛ ሀገራቸው ለሀገር ውስጥ ስደተኝነት ይዳርጋቸዋል።

ይህ የናንሰን ሜዳልያ ለመሸለም በመብቃቴ ክብርና ደስታ እንደ ተሰማኝ ዳግም ልገልጽ እወዳለሁ። የስደተኞች ችግር እጅግ ሠፊ ነው። እኛ ግን ያከናወነው በጣም ትንሽ ነው። ይሁን እንጂ ይኸው ትንሹ ጥረ ታችን ዕውቅና ማግኘቱ የስደተኞችን ሸክም ለማቃለል ለሚጥሩት ሁሉ የሚያበረታታ የተስፋ ምንጭ ነው። በዚህ መልካም አጋጣሚ ከኃላፊነ ታቸው የሚሰናበቱት ኮሚሽነር ሳዳኮ ኦጋታ ባለፉት አስር ዓመታት ውስጥ ላበረከቱት አርኪ ውጤት ልባዊ ምስጋናዬን ላቀርብላቸው እወዳለሁ።

በመጨረሻም፣ «ከሃያኛው ምዕተ ዓመት ታላላቅ በጐ አድራ ጊዎች አንዱና» ግምባር ቀደም ተሟ ጋች ተደርገው የሚቆጠሩት ናንሰን ይከተሉት የነበረውን መርሐ ልጠቅስ እሻለሁ። ርሱም «የሰውን ልጅ ማፍቀር ተግባራዊ ግዴታ» ነው የሚል ነው። የሰው ልጅ የዘለቄታ መልካም ሕይወት በፍቅር ላይ

www.ethiopianorthodox.org

የተመሠረተ ነው። በማንኛውም ጊዜና ቦታ ተግባራችን በፍቅር ላይ ከተመ ሠረተ ራስ ወዳድነት፣ ጭካኔ፣ የሰው ልጅ ስቃይና መንገላታት እንደ በረዶ ይቀልጣል፤ ምክንያቱም ክፉ ሥራ ሁሉ የፍቅር መጥፋት ውጤት ነውና።

ከዚያ ቀደም ባሉ ዕለታት መስከረም ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ከስድኒ ኦሎምፒክ መልስ ለውድ አትሌታችን ቤተክርስቲያናችን ባደረ ገችው የክብር አቀባበል የተናገሩት መልእክት። «በዚህ እኩሪ ውጤት ይዛችሁ ወደ ቅድስት ሀገራችሁ ስትመለሱ እናንተን ለመቀበልና ለማየት ያልቻከለ ሰው አልነበረም።

የእናንተ መጀመሪያ ቋንቋችሁ ወላጆቻችሁና ቤተክርስቲያናችሁ እንድትጸልይላችሁ ሥራችሁ እግዚ አብሔር የተቃና እንዲያደርግላችሁ በተለያየ ጊዜ በተጠየቃችሁ ጋዜጣዊ መጠይቅ በመጀመሪያ የንግግራችሁ መጀመሪያ የነበረው የእግዚአብሔርን ስም በመጥራት ስለሆነና እናንተም በሁላችሁ አቅም እንደሌላችሁ፣ ነገር ግን ሁሉም የእግዚአብሔር እንደ መሆኑ መጠን፣ የኢትዮጵያ አምላክ እግዚአብሔር አባቶቻችንን፣ እናቶቻ ችንን በረዥሙ የታሪክ ዘመናችን እንደረዳቸው፣ እናንተም እንዲረ ዳችሁ፣ በመማጸን፣ ይኸ እናንተ የጀመራችሁት በእምነት ጸንቶ በእግዚአብሔር መማፀን፣ አዲስ ነገር አይደለም። የኢትዮጵያችን ታሪክ ተመዝግቦ የሚገኘው ቁም ነገር ሁሉ፣ በእግዚአብሔር በመታመን በተደረገ ሥራ ነው። እንደሌሎው የክፍለ ዓለ ማት በየዘመኑ የተፈጠሩት ቁሳቁሶችና መሣሪያዎችን ትምክሕት በማድረግ የተሠራ አልነበረም። በረዥሙ ታሪካችን ተመዝግቦ እንደሚገኘው፣ አባቶቻችን፣ እናቶቻችን ሕሊናቸ ውን ወደ እግዚአብሔር በማንበርከክ የጀመሩትን ሥራ ረዥሙ የኢትዮጵያ ታሪክ እዚህ መዘርዘር አይቻልም በዘመናችን የዚህ ዓይነት ታሪክ የተፈጸመ አንድ ጉዳይ አለ።

ይኸውም በአፄ ምኒልክ ዘመን [illegible] የአድዋው ጦርነት እሳ

ቸው የገጠሙት በዓለሙ ላይ ካሉት በቁሳቁስ ከበለጸጉ፣ የተለያየ የሚያ ስመካ መሣሪያ ከነበራቸው፣ እኛ ነን ከሚሉት ሰዎች ጋር ነው የገጠሙት።

ወደ ጦር ሜዳ ይዘውት የሄዱት ትልቁ መሣሪያቸው በእግዚአብሔር መታመን ነበር። እምነታቸውን ጋሻ አድርገው ባለመሣሪያዎችን መሣሪያ በሌለው አሸንፈው የመጡት እምነታ ቸውን ይዘው ስለሄዱ ነው። እናንተም ልጆቻችን በአሁኑ ዘመን በተለያዩ ዓለማት ከመላው የዓለም ኅብረተሰብ የተወዳደራችሁት ለዚሁ ዓላማ የሚሰለጥኑበት ብዙ ቁሳቁስ አላቸው። ሁሉም ተሟልቶላቸዋል። ያልተሟላ ነገር የለም፤ በዚያ ያለው አቅም እኛ እናውቀዋለን። የእኛ ዝግጅት የሚያስመካ እንዳልነበረ እናው ቀዋለን።

እናንተ ግን ይኸን ያህል መሣሪያ ካላቸው ሰዎች፣ ከሰለጠኑ ሰዎች አንቀርብም ሳትሉ በመጀመሪያ እንደ ሰለስቱ ደቂቅ አምላካችን ከሁሉ ያድነናል ብለው እንደተሰለፉ፣ እንደ ዚሁም አባቶቻችን በታሪክ እንደዚህ ብለው እንደተመኩ፣ እናንተም የአባ ቶቻችንና የእናቶቻችን አምላክ ይረ ዳናል። እናንተ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆናችሁ ኢትዮጵያውያኖች ጸልዩ ልን የሚለው ጋሻ ይዛችሁ ነው የሄዳችሁት።

ይኸ ዓለም ትክክለኛውን በመና ገር ኃጢአቱን መግለጽ ብዙ ያስቸ ግረዋል። እንጂ አሁን የተደረገው ድርጊት ዓለምን በሙሉ የሚያስገርም ነው።

አሁን እናንተም በቆማችሁበት እምነት ጸንታችሁ በመገኘታችሁ እንዲህ ያለ ታሪካዊ ሥራ ሠርታች ኋል። በዚህም የወላጆቻችሁ ልጆች ሆናችሁ ነው የተገኛችሁት። ማንም ሰው በእግዚአብሔር የታመነ አያፍ ርም፣ ለዚሁም ነው የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔርም ሰዎች ምዕመናንና ምዕመናት በእግዚ አብሔር ላይ ያለው እምነታቸው፣ የተሟላ፣ የተጠናከረ፣ ሕፀፅ የሌለበት እንዲሆን የምትጠይቀውና አቅምዋ በሚፈቅደው አዘውትራ የምታስተ ምረው። አሁንም ኩሩ የሆነችው ሀገራችን በንጹህ ታሪክ በጀግንነት፣ በመንፈሳዊ አርበኝነት፣ በማናቸውም አቅጣጫ አፍራ የማ[illegible]

የእግዚአብሔር ጠገኛ የሆነችው የኢትዮጵያ ልጆች [illegible]ርዓቱን ተከታት ላችሁ በኩራት ላይ ኩራትን ስለጨ መራችሁልን እግዚአብሔር ይባር ካችሁ። እንኳን ይኸንኑ የደመቀ ታሪካዊ ግዳጅ ፈጽማችሁ በሰላም ወደ ሀገራችሁ መጣችሁ።

እንግዲህ እናንተ ልጆቻችን ሁላችንም እንወዳችኋለን። ይኸ በዓለም ላይ የተደነቀው ታሪክ ወይም ጦርነት አሸንፋችሁ መጥታችኋል። ኢትዮጵያውያኖች በተሰለፉበት ሁሉ እያሸነፉ ናቸው። እናንተም ይህ የሰላም ጦርነት አሸንፋችሁ መጣችሁ። ከእንግዲህ ወዲህ ሌላ ጦርነት በሀገራችን ላይ ስለ አለ በተለይም እንደናንተ የመሰሉ ወጣት ልጆቻችንን የሚጸናወት ቀሳፊው በሽታ (ኤችአይቢ) ስለሆነ እናንተም እግዚአብሔር ስለወደዳችሁ እናንተ ከመናገር አታቋርጡ። ከእናንተ ያነሱ ወጣት ልጆቻችን በእናንተ ደረጃ እንደምሪታቸውና ዝንባሌያቸው ቢሰማሩበት እኩሪ ሆነው እንዲገኙ አለጊዜያቸው እንዳይቀጩብን፣ ይህ ቀሳፊ በሽታ በኅብረተሰቡ እንዳይ ኖር፣ እንዲጠፋ ለማድረግ እናንተም ስበኩ። አስተምሩ። መልካሙን ነገር መናገር ለሀገር፣ ለወገን የሚጠቅም ሥራ መሥራት ልማት ማለት እሱ ነውና።


ሁሉም በሃይማኖቱ ጸንቶ ዓላማውን ጠብቆ፣ ወደ ኋላ ሳይል ሳይወላውል፣ ወገኑ ሁሉ እንዲማርና እንዲያድግ፣ በየአለበት ደረጃ እንዲያስተምር፣ ግዴታው ነው። አዋቂ ሕዝብ፣ የተማረ ሕዝብ ሥራው ይሄው ነው።

ስለዚህ ልጆቻችን እኛ እንደ ወደድናችሁ አውቃችሁ፣ ሌሎችም ሁላችን ረድተናቸው ወጣት ልጆቻ ችንን በማያውቁት መንገድ የሚሰና ከሉትን፣ ሕመሙ እንዳይቀ ጥልባቸው ለማድረግ ከዛሬ ጀምሮ ሕዝብ ይጠራችኋል፣ ይጋብዛችኋል፣ ስለሚያዳምጣችሁ ይህ የሚደመጠው ድምፅ ሳይነገር እንዳይቀር ነው አጥብቄ የማሳስበው። እግዚአብሔር ይባርካችሁ ልጆቼ እንኳን ለዚህ ክብር አበቃን። እግዚአብሔር ዓለማችንን [illegible]። ✣

«እምነ ጽዮን ይብል ሰብእ»

# ሰው ሁሉ ጽዮን እናታችን ይላል

ከአባ ገሪማ
የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት፣ የውጭ ግንኙነት የበላይ ኃላፊና
የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ሊቀ ጳጳስ



«ሰዎች ሁሉ ጽዮን እናታችን ናት፣ እግዚአብሔር አባታችን ነው ይላሉ።» (መዝ.፹፮፥፭) ይህ ከልደተ ክርስቶስ በፊት በአንድ ሺህ ዓመተ ዓለም፣ እግዚአብሔር በነቢዩ ዳዊት አንደበት የተናገረው ወይንም ያናገረው ነው።

«ጽዮን» የሚለው ቃል አምባ መጠጊያ ማለት ነው። ነቢዩ ዳዊት የኢየሩሳሌምን አምባ የቤተ መንግሥት ከተማ እንዲሆን መረጠው (፪ኛ ሳሙ.፶፮፥፲)።

ከኢያሱ በኋላ አራት መቶ ሃምሳ ዘመን ያህል እንደሆነ የእስራኤል [illegible]ንጉሥ ዳዊት፣ ኢየሩሳሌምን ከኢያቡ ሳውያን እጅ ወስዶ የመንግሥቱ ከተማ አደረጋት። (፪ኛ ሳሙኤል ፭፥፩-፲፮) (የሐዋ.ሥራ ፲፫፥፳)

ቤተ መንግሥቱንም በደብረ ጽዮን ሠራ። ደብረ ጽዮን የዳዊት ከተማ የተሠራበት ቦታ ነበር። ዛሬም ጽርሐ ጽዮን እየተባለ ይጠራል።

ቤተ መቅደስ የተሠራበት የሞርያ ተራራም እግዚአብሔር ለመሠዊያነት አገልግሎት የመረጠው ቦታ ሆነ።

«እስመ ኀረያ እግዚአብሔር ለጽዮን፤

ወአብደራ ከመ ትኩኖ ማኅደሮ፤

ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም፤

ዝየ አኀድር እስመ ኀረይክዋ፤ (መዝ.፻፴፪፥፲፫-፲፬)

እግዚአብሔር ቦታውን እንደመ ረጠውም የሚያስረዳው ንጉሥ ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ሠርቶ በፈጸመ ጊዜ ጸጋ እግዚአብሔር በብሩህ ደመና አምሳል ወርዶ ቤተ መቅደሱን መልቶ መገለጡና መታየቱ ነው። (፪ኛዜና መዋዕል ፭፥፲፫-፲፬)

እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን የስሙ መጠሪያ፤ የአምልኮቱ መከ በሪያ እንድትሆን ከጥንት ጀምሮ መርጧታል።

ሰሎሞንም ያባቱ የንጉሥ ዳዊት ምኞት የነበረውን ዕውነተኛውን የአምልኮት ቤተ መቅደስ ሠራባት፤ በዚህም ስሙ ታወቀ፤ ዜናውም ደመቀ።

በዘመነ ኦሪት አሕዛብ ሳይቀሩ በየዓመት በዓሉ ወደ ኢየሩሳሌም እየወጡ ለእስራኤል አምላክ ሲሰግዱ ይታዩ ነበር። (ሚክያስ ፬፥፪-፫፤ ዘካ.፰፥፳፩-፳፫)

በዘመነ ሐዲስም ሕዝብና አሕዛብ ከምሥራቅና ከምዕራብ፣ ከሰሜንና ከደቡብ ከልዩ ልዩ ትውልድና ወገን ቅድስት ሀገር፣ የእግዚአብሔር ከተማ እያሉ በየዘመኑ እየመጡ በኢየሩሳ ሌም ለእግዚአብሔር ይሰግዳሉ።

ከተማውም ለዓለም ማዕከለ ምድር፣ ለቤተ እሥራኤል መንግሥ ትም የተመቸ ቦታ ነበር። ከጢሮስና

www.ethiopianorthodox.org

ሲዶናም ጥበበኞቹን እያስመጣ ከተማውን አዲስ አድርጎ አሠራው፤ የዳዊት ከተማም ተብሎ ተጠራ።

ንጉሥ ዳዊት ኢየሩሳሌምን ከከተመና የዳዊት ከተማም ተብሎ ከተጠራ ወደ ሦስት ሺህ ዘመናት ደርሷል ማለት ነው።

ደብረ ጽዮን የቤተ መንግሥት ከተማ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንዲሠራበትና እሥራኤላውያንም ሁሉ እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት ዋና ከተማ እንዲሆን እግዚአብሔር አደረገ።

ቀደም ሲል የእሥራኤል ልጆች በኬብሮን፥ በባርዜባ፥ በቤቴል፥ በጊልጌልና በሴኬም አምልኮታቸውን ሲፈጽሙ ነበር። ከዚያን ጊዜም ጀምሮ ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከተማ ሆነች።

በምሳሌነትም፥ ጽዮን መንግሥተ ሰማያትን የምታመለክት ናት። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «...ወደ ጽዮን ተራራና ወደ ሕያው እግዚአብሔር ከተማ ደርሳችኋል ወደ ሰማያዊቱም ኢየሩሳሌም» ይላል (ዕብ.፲፪፥፳፪) ምድራዊቷ ኢየሩሳሌም በሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም አንጻር የምትታይ ናት።

መጽሐፍ ቅዱስ በእምነትና በምግባረ ሠናይ የፀኑ ወደ ኋለኛይቱ ኢየሩሳሌም ይደርሳሉ በማለት የእግዚአብሔርን መንግሥት ሁኔታ በኢየሩሳሌም ምሳሌነት አንጻር ያስረዳል። (ማቴ.፭፥፴፭፤ ገላ.፬፥፳–፳፮፤ ዕብ.፲፪፥፳፪፤ ራእ.፫፥፲፪)

ሊቁ አባ ሕርያቆስ ጳጳስ ቆጵስ ዘሀገረ ብሕንሳ «ኦ አንትሙ ሕዝበ ክርስቲያን በከመ ተጋባዕክሙ በዛቲ ዕለት ከማሁ ያስተጋብዕክሙ በደብረ ጽዮን ቅድስት ወበኢየሩሳሌም አግዓዚት እንተ በሰማያት እናንተ የክርስቲያን ወገኖች ሆይ፤ በዚህች ቀን እንደተሰበሰባችሁ እንደዚሁ ክብርት በምትሆን በደብረ ጽዮንና በሰማይ ባለች ነፃ በምታወጣ በኢየሩሳሌም ይሰብስባችሁ» ይላል። (ቅዳሴ ማርያም)

በመሠረቱ ከዘመነ መሳፍንት ከሙሴና ከኢያሱ ዘመን ጀምሮ ዓሥራ ሁለቱ ነገደ እሥራኤል ይማጠኑባት፥ ከጠላትም ኃይል ይጠበቁባት የነበረችው የሕጉ ማደሪያ፥ የስሙ መጸፊያ የሆነችው ጽላተ ሙሴ ናት።

ሙሴ ከእግዚአብሔር ተጠርቶ ወደ ሲና ተራራ በወጣ ጊዜ ዓርባ መዓልትና ዓርባ ሌሊት ከሰው ተለይቶ ከእህልና ውሀም ርቆ ከጾመ በኋላ ይህችን ጽላት ከእግዚአብሔር እጅ በመቀበል ሕጉን ለቤተ እስራኤል ሊያስትምር ችሏል። (ዘጸ.፴፥፳፪)

ጽላተ ሙሴ በዘመነ ሐዲስ ላለነው ክርስቲያናት መማፀኛ የሆነችው የእመቤታችን ድንግል ማርያም ምሳሌዋ ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር በረቂቅ ጥበቡ ቀደም ብሎ ጊዜው ሳይደርስ ያዘጋጃት ነበረች።

ምሳሌነቷም፥ ጽላተ ሙሴ በማናቸውም ሁኔታ ሁሉ በጠበብት እጅ ያልተዘጋጀች፥ ቃሉም በግብር አምላካዊ ተጽፎ የተገኘ ነው።

ቃሉ ያለ ጸሐፊ እጅ ተጽፎባት እንደተገኘ ሁሉ ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ያለዘርዐ ብእሲ ከሥጋዋ ሥጋን፥ ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ በመዋሐድ ፍጹም አምላክ፥ ፍጹም ሰው መሆኑን ያስረዳናል።

ታቦተ ጽዮን ጽላተ ሙሴ በኢያሱ ዘመን ካደረገቻቸው ተአምራትና ድንቅ ሥራዎች፥

፩ኛው አሥራ ሁለቱ ነገደ እሥራኤል በኢያሱ መሪነት ዮርዳኖስን ተሻግረው ወደ ምድረ ርስት መግባታቸው።

፪ኛው የኢያሪኮን ግንብ በማፍረስ የታየው ተአምር ነው።

ከዚህ ላይ በተ[ር]ዳኖስ ወንዝና በኢያሪኮ ከተማ የተፈጸመው በእግዚአብሔር ኃይል በታቦተ ጽዮን ተአምራት ሠሪነት መሆኑን ለማስገንዘብ እንወዳለን።

ደብረ ጽዮን ኢየሩሳሌም በእግዚአብሔርና በሰው ዘንድ የተከበረች የተቀደሰች ከተማ ብትሆንም ስሟ ከተጠራበት ዘመን ጀምሮ የመከራዋ ታሪክ ስፍር ቁጥር የለውም። በየዘመኑና በየጊዜው የጦር መዛመቻ፥ የጠላት መዘበቻ የመከራ መካተቻ ከመሆን አልዳነችም።

እግዚአብሔር ከፈጠረው ምድር ሁሉ በዘመነ ብሉይም ሆነ በዘመነ ሐዲስ እንደ ኢየሩሳሌም ያለ የሰው ደም እንደ ውሀ ጎርፍ የፈሰሰበት በዓለም አይገኝም። ይህ ሁሉ ታሪኳም በመጽሐፍ ቅዱስ ተመዝግቦ ይገኛል።

የደብረ ጽዮን ኢየሩሳሌም ዋና የእድገቷ ጊዜ በንጉሥ ዳዊትና በልጁ በንጉሥ ሰሎሞን ዘመን አከትሟል።

እሥራኤላውያን ከፊልስጥኤማውያን ጋር በየጊዜው ጦርነት ማድረጋቸው በመጽሐፍ ቅዱስ የታወቀ ሲሆን ከመጨረሻዎቹ ታላላቅ መሳፍንት አንዱ በነበረው በሳሙኤል ዘመን ፍልስጥኤማውያን በእሥራኤል ላይ በጦርነት ቦታ ሆነው በካህኑ በዔሊ ቤተሰብ ጥፋት ወይም በደል ምክንያት የጦርነቱ ድል ለፍልስጥኤማውያን ሆኖ በጦርነቱ እሥራኤላውያን ከመኀዳታቸውም በላይ የቃል ኪዳኑ ታቦት ታቦተ ጽዮን ተማረከች፤ ሁለቱም የዔሊ ልጆች ካህናት አፍኒንና ፊንሐስ በጦርነቱ ተመቱና ሞቱ (ወደቁ)።

እሥራኤላውያንን ዐርባ ዓመት ሲያገለግል የኖረውና ዘጠና ስምንት ዓመት ዕድሜ የነበረው ሊቀ ካህናቱ ዔሊም የልጆቹን በጦር ሜዳ መገደል፥ የእሥራኤላውያንን ሽንፈትና የታቦተ ጽዮንን በፍልስጥኤማውያን መማረክ በሰማ ጊዜ ደንግጦ ከተቀመጠበት ወንበር ወድቆ አንገቱ ተቈልምሞ ሞተ። (፩ኛሳሙ.፬)

ከዚህ በኋላ ፍልስጥኤማውያን የማረኳት ታቦተ ጽዮን መቀመጥ ያለባት ከጣዖቱ ጋር ነው በማለት የዳጎን ካህናት ከቀድሞ ጀምሮ ያድነናል ብለው በሚያመልኩትና በሚማጸኑት ዳጎን እየተባለ የሚጠራው ጣዖት ከሚኖርበት ቤተ ጣዖት አስገብተው ከዳጎን ጋር አስቀመጧት፤ በነጋታውም ወደ ቤተ ጣዖቱ ሔደው ሲመለከቱ ዳጎን የተባለው ጣዖት በእግዚአብሔር ታቦተ ሕግ ፊት በግንባሩ ወድቆ ያገኙታል።

አሁንም የዳጎን ካህናት ከአቀማመጥ ጉድለት የተነሣ የወደቀ መስሏቸው ጣዖቱን ጠጋግነው ታቦተ ጽዮንን በታች፣ ዳጎንን በላይ አስቀምጠውት ከሔዱ በኋላ በማግስቱ ወደ ቤተ ጣዖቱ ገብተው ሲመለከቱ የዳጎን ራሱም እጆቹም ተቈራርጠው፥ መላ አካሉ ሁሉ ተከስክሶ በመድረኩ ላይ ተበታትኖ ያገኙታል።

ታቦተ ጽዮን ባሳየችው ተአምር መነሻነት፥ የዳጎን ካህናትም ሆኑ ወደ ዳጎን ቤት ይገቡ የነበሩት ፍልስጥኤማውያን ሁሉ የጣዖቱ ውድቀት ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ ተስፋ በመቁረጥ የቤተ ጣዖቱን መድረክ ተመልሰው ረግጠውት እንደማያውቁ መጽሐፍ ቅዱስ አብራርቶ ያስረዳናል። (፩ኛ ሳሙ.፭፥፭)

የፍልስጥኤማውያን ጦር በእሥራኤል ሠራዊት ላይ አይሎና ድል ተቀዳጅቶ የነበረውን ያህል «ኢይትርፍ ግፍዕ...» ነውና ታቦተ ጽዮን በተዘዋወረችበት ሀገር ሁሉ በተለያየ የበሽታ ዓይነት ፍልስጥኤማውያን ስለተመቱ ዕቅዳቸው ፈርሶ፥ ያሰቡት ሁሉ ሳይሳካላቸው በመቅረቱ አዘኑ፥ ፈሩ፤ ተንቀጠቀጡ።

የእግዚአብሔር ታቦት በፍልስጥኤማውያን ሀገር ከሰባት ወራት ቈይታ በኋላ ፍልስጥኤማውያን ምክር እንዲለግሱአቸው ካህናተ ጣዖቱንና ጠበብቱን ጠርተው በሰላም መኖር ይችሉ ዘንድ ከጭንቀታቸው አንጻር የእግዚአብሔርን ታቦተ ሕግ ወደ ሥፍራዋ እንዴት መመለስ እንደሚችሉ ላቀረቡት ጥያቄ፥ ቀንበር ያልነካቸው የሚያጠቡ ሁለት ላሞች የሚያንቀሳቅሱት ሠረገላ ሠርተው፥ በሠረገላውም ከታቦተ ጽዮን ጋር ለእሥራኤል አምላክ ክብር፥ የሚገባ ገጸ በረከት አኑረው ጥጆችን ከእናታቸው በመለየት አሸኛኘት ቢደረግ፣ እግዚአብሔር በምሕረቱ፥ በቸርነቱ ሊጎበኛቸው እንደሚችል ገለፁላቸው።

በዚሁ መሠረት ዝግጅቱ ተጠናቆ ታቦተ ጽዮን ያለችበት ሠረገላ ወደ ግራና ቀኝ ሳይል በቀጥታ ጉዞውን ቀጥሎ ታቦተ ጽዮን ወደ ቤተ እሥራኤል እንድትመለስ ተወሰነ። በኮረብታውም ላይ ወደ አለው ወደ ቤተ አሚናዳብ እንድታርፍ ተደረገ። (፩ኛሳሙ.፭ና፮)

የቃል ኪዳኑ ታቦት ከአሚናዳብ ቤት ወደ ኢየሩሳሌም መወሰዱ

ዳዊት ከቤተ እስራኤል የተመረጡትን ሠላሳ ሺህ ያህል ሰዎች ሰብስቦ የእግዚአብሔርን ታቦት በአዲስ ሠረገላ ላይ አስጭኖ ከነበረበት ከአሚናዳብ ቤት አውጥቶ በቅኔና በበገና፥ በመሰንቆ፥ በከበሮ፥ በነጋሪትና በጸናጽል በክብር በሚያንጉዝበት ጊዜ የአሚናዳብ ልጆችም ዖዛና አሒዮ አዲሱን ሠረገላ ይነዱ ነበር።

የእግዚአብሔርን ታቦት ይዘው ሲኄዙ አሒዮ በታቦቱ ፊት ይሔድ ነበር።

ወደ ናኮንም አውድማ በደረሱ ጊዜ በሬዎቹ ይፋንኑ ነበርና ዖዛ እጁን ዘርግቶ የእግዚአብሔርን ታቦት ያዘ፤ የእግዚአብሔርም ቁጣ በዖዛ ላይ ነደደ። እግዚአብሔርም ስለድፍረቱ በዚያው ቀሰፈው። በእግዚአብሔርም ታቦት አጠገብ በዚያው ሞተ። እግዚአብሔርም ዖዛን ስለሰበረው ዳዊት አዘነ፤ እስከዛሬም ድረስ የዚያ ስፍራ ስም የዖዛ ስብራት ተብሎ ተጠራ። (፪ኛ ሳሙ.፮፥፩–፱)

ከዚህ የተነሣ ዳዊት ፈርቶ የእግዚአብሔር ታቦት ወደኢየሩሳሌም ይመጣ ዘንድ አልወደደም። ዳዊት ታቦተ ሕጉን በጌት ሰው በአቢዳራ ቤት አገባው። (፪ኛሳሙ.፮፥፲)

ንጉሥ ዳዊት ታቦተ ሕጉን የተዳፈረው ዖዛ መቀሰፉን ተመልክቶ ለጊዜው ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም ለማምጣት አልወደደም ነበር። ንጉሥ ዳዊት ታቦተ ሕጉን ከመፍራትና ከማክበር ያደረገው እንጂ በንቀት የሆነ አልነበረም።

[እ]ግዚአብሔርም ታቦት በጌት ሰው በአቢዳራ ቤት ለሦስት ወራት ያህል በተቀመጠ ጊዜ እግዚአብሔር አቢዳራንና ቤቱን ሁሉ ባረከ።

ንጉሥ ዳዊትም እግዚአብሔር የአቢዳራን ቤትና የነበረውን ሁሉ ስለ እግዚአብሔር ታቦት የባረከለት መሆኑን በሰማ ጊዜ የእግዚአብሔርን ታቦት ከአቢዳራ ቤት ወደ ዳዊት ከተማ ኢየሩሳሌም በደስታ አመጣው።

ታቦተ ሕጉ በኃይለ እግዚአብሔር ገቢረ ተአምር እያሳየ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ከጊዜ በኋላም በእሥራኤልና በፍልስጥኤማውያን መካከል በተለያየ ምክንያት ጦርነት በተነሣ ቁጥር ድሉ ለእሥራኤል እየሆነ ጎልቶ መታየቱ ፍልስጥኤማውያን ውድቀታቸው እየተቃረበ መምጣቱን ተረዱ።

ከዚህ በኋላ በመስፍኑ በሳሙኤል ዳኝነትና አደራዳሪነት ቀደም ሲል ፍልስጥኤማውያን በድል አድራጊነት ወስደውት የነበረው የእስራኤል ቦታ ሁሉ ዳር ድንበሩ ተለይቶ እንዲመለስላቸው በታቀደው መሠረት ከአስቀሎና ጀምሮ እስከ ጌት ድረስ ያለው ቦታና ፍልስጥኤማውያን የወሰዱአቸው ከተሞች ሁሉ ለእሥራኤል ተመለሱ።

ሳሙኤልም ፍልስጥኤማውያን ከራሳቸው ቦታ ዳር ድንበር አልፈው አስፈላጊ ያልሆነውን ከመፈጸም ይገቱ ዘንድ የእሥራኤልንና የፍልስጥኤምን ቦታ በሚያገናኘው ድንበር መካከል የወሰን መከለያ ድንጋይ በማስቀመጥ «አቤንኤዘር» በሚል ስያሜ ጠራው። ይህም ማለት «እግዚአብሔር ረድቶናል» ማለት እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ተብራርቶ ተገልጿል። (፩ኛሳሙ.፯፥፲፪)

ሳሙኤል ገና ከሕፃንነቱ ጀምሮ በቤተ እግዚአብሔር ሲኖር እግዚአብሔር ተገለጠለት፤ የነቢይነት መንፈስም አደረበት፤ በዔሊ ልጆች ኃጢአት ምክንያት በዔሊና በልጆቹ የሚመጣውን መከራ አስቀድሞ ነግሮት ነበር። በማናቸውም ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ከሳሙኤል ጋር ነበር።

እስራኤላውያን ሁሉ ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ድረስ ሳሙኤል

www.ethiopianorthodox.org

ለእግዚአብሔር የታመነ ነቢይ እንደሆነ ዐወቁ፤ ከዚህ በኋላም ነቢዩ ሳሙኤል ለዔሊ የተናገረው ትንቢት በዚያው ዘመን ተፈጸመ።

ሳሙኤል በዘመኑ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ተጐናጽፎ በእውነተኛ ነቢይነቱ፣ በቅን ፈራጅነቱ ለሃያ ዓመታት ያህል እሥራኤላውያንን ጠበቀ፤ መገበ። (፩ኛሳሙ.፯፥፲፭—፲፯)

ከዚህ በኋላ እስራኤላውያን ሳሙኤልን ንጉሥ እንግሥልን አሉት፤ በጥያቄያቸውም መሠረት ሳሙኤል እግዚአብሔርን አነጋግሮ ሳኦልን ቀብቶ አንገሠላቸው። (፩ኛሳሙ.፰፥፩—፳፪፣ ፲፥፩—፪)

ከጊዜ በኋላም የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ሳሙኤል ዳዊትን ቀብቶ አነገሠው። (፩ኛሳሙ.፲፮፥፲፪—፲፬) ዳዊት በፈቃደ እግዚአብሔር የእሥራኤልን መንግሥት በመያዝ ሥልጣኑን ቢቀበልም በሌላ ጎኑ ደግሞ ሳኦል በዓመፅ ተነሣስቶ የእግዛዝ እጁን ከቤተ እሥራኤል ባለማንሣቱ በዳዊት መንግሥት አስተዳደር በጣልቃ ገብነት ሁከትን ይፈጥር እንደ ነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት የሚቻል ነው። (፪ኛሳሙ.፫፥፩)

ሳኦል በዳዊት መንግሥት አስተዳዳር ላይ ቅንዓትና ምቀኝነት አድሮበት በፍልስጥኤማውያን ሊያስገድለው ቢሞክርም ዳዊት ግን ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር በመስጠት የሳኦልን ልጅ ሜልኮልን አግብቶ ለመዛመድ (ባለሟልነትን ለማግኘት) ሞክሮ ነበር።

የዳዊት ከሳኦል ጋር በጋብቻ መዛመድ በንጉሡ በሳኦል ዘንድ ከፍተኛ ድጋፍን አግኝቷል፤ ምክንያቱም ሳኦል ዳዊትን በፍልስጥኤማውያን ለማስገደል በማሰብ ልጁ ሜልኮል በግድያው አፈጻጸም እንደ ምትተባበር ስለአመነ ነበር።

የሜልኮል ጋብቻ የአባቷን የሳኦልን ፈቃድ ለመፈጸም በተደረገው ስምምነት ላይ ብቻ የተመሠረተ ሳይሆን በራሷ ሙሉ ፈቃደኛነት ጭምር በመሆኑና ከዚህም በላይ በጣም ታፈቅረው ስለነበረ በባሏ በዳዊት ሕይወት ላይ እጇን ለማንሣት ፈጽሞ አልሞከረችም ነበር።

በሁለቱ ነገሥታት በሳኦልና በዳዊት መካከል ተፈጥሮ የቆየው አለመግባባት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ቢሔድም የእግዚአብሔር ኃይል ከዳዊት መንግሥት ያልተለየ በመሆኑ ከየአቅጣጫው በሚነሣው ፍልሚያ ሁሉ ንጉሥ ዳዊት እንደ አመጣጡ በመመከትና በመመለስ ድልን ተቀዳጅቶ የእሥራኤልና የይሁዳ ንጉሥ በመሆን የእሥራኤልን መንግሥት አጠቃሎ ከያዘ በኋላ ኢያቡሳውያንን በጦርነት አሸንፎ በጽዮን ተራራ የሠሩትን ምሽጋቸውን «ኢየሩሳሌም የዳዊት ከተማ» ብሎ የሠየማት መሆኑ ቀደም ሲል ተነግሯል።

የንጉሥ ዳዊት የእሥራኤልን የግዛት አንድነት ማስከበር ለታቦተ ጽዮን ወደ ኢየሩሳሌም መግባት ምክንያት በመሆኑ የቃል ኪዳን ታቦት በኮረብታ ላይ ከሚገኘው ከቤተ አቢዳራ ወጥቶ ወደ ኢየሩሳሌም ባመራበት ጊዜ እንደ በፊቱ ዳዊትና እሥራኤላውያን ሁሉ የበገና፣ የመሰንቆ፣ የከበሮ፣ የጸናጽልና የቃጭል ድምፅ እያሰሙ ለእግዚአብሔር ክብር በመዘመር በሆታና በዕልልታ ተቀብለውታል።

የእግዚአብሔርም ታቦተ ሕግ በዳዊት ከተማ ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ የዳዊት ሚስት ሜልኮል ባሏ ዳዊት ስለታቦተ ጽዮን ክብር ሲዘፍን ባየች፣ በተመለከተች ጊዜ ናቀችው።

ስለዚህም ነገር የሜልኮል ማኅፀን ልጅ ከመውለድ ተከለከለችና ሜልኮል መካን ሁና ኖረች። እስከ ዕለተ ሞቷም ድረስ ልጅ አልወለደችም።

እስራኤላውያን ቀደም ሲል በሙሴ መሪነት፣ በእግዚአብሔር ቸርነት፣ በመልአኩ ተራዳኢነት ባሕረ ኤርትራን ተሻግረው በሲና በረሀ ዓርባ ዘመን ሙሉ ተንከራተው የሞቱት ሞተው፣ በጉዞው ላይ እያሉ የተወለዱት እስራኤላውያን ደግሞ ወደ ምድረ ርስት ለመግባት እየተቃረቡ ሳለ፣ ታላቁ መሪያቸው ሙሴ ሞቶ እንደተቀበረ በፈቃደ እግዚአብሔር በቦታው ኢያሱ ተተክቶ በኢያሱ መሪነት በታቦተ ሕጉ ተራዳኢነት ዮርዳኖስን ተሻግረው በምድረ ከነዓን በየነገዳቸው ድርሻቸውን አውቀው ከሠፈሩ በኋላ እግዚአብሔር ያወረሳቸውን ርስታቸውንና ነገዳቸውን፣ ወገናቸውን የሚያሰጋ ጠላት በሚመጣባቸው ጊዜ ለጦርነት ሲነሡ እግዚአብሔር በመካከላቸው እንዳለ የሚያውቁት በታቦተ ሕጉ ዙሪያ ተሰባስበው ጠላቶቻቸውን ድል ሲያደርጉ ብቻ ነበር። (መሳ.፳፥፳፫)

በዚያ ዘመን የነበሩ እስራኤላውያን ይገጥማቸው የነበረ ፈተና ሁሉ ዛሬም ለእኛ ከሚገጥመን ፈተና ተመሳሳይ ስለሆነ፤ ሕይወታችንን በሕገ እግዚአብሔር መምራት እንድንችል የብሉይ ኪዳኑን ታሪክ መመልከቱና ማወቁ ጠቃሚ ይሆናል።

እስከዚህ የተነገረው ዋና መልእክት፤ ለእግዚአብሔር ያለመታዘዝ ውድቀትንና ጥፋትን እንደሚያስከትል፤ ታማኝ ሁኖ መገኘት በረከትንና የሕይወት መሳካትን እንደሚያስገኝ ያሳያል።

ይህም እግዚአብሔር ለካህኑ ለዔሊ «እኔ፣ የሚያከብሩኝን አከብራለሁ፤ የሚንቁኝንም አዋርዳለሁ» በማለት የተናገረው ቃል ግልጥ ሁኖ ይታያል። (፩ኛሳሙ.፪፥፴)

«እምነ ጽዮን ይብል ሰብእ» «ሰው ሁሉ ጽዮን እናታችን ናት እግዚአብሔር አባታችን ነው» በሚል መነሻ ከሙሴ እስከ ንጉሥ ዳዊት ከታቦተ ጽዮን ጋር የሆነውን ድርጊት ሁሉ ባጭሩ ለመመልከት ችለናል።

ጽዮን ቅድስት ድንግል ማርያም እናታችን፤ መሠረተ ሕይወታችን፣ ተስፋችን፣ አለኝታችን፣ መመኪያችንናት።

የዔሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ በድፍረት በፈጸሙት ኢሕጋዊ ድርጊት እስራኤላውያንን በደለኞች በማድረጋቸውና በዚሁ ምክንያት እግዚአብሔር ስለራቃቸው በአንድ ወቅት በእስራኤላውያንና በፍልስጤማውያን መካከል ጦርነት ተደርጎ ድሉ ለፍልስጥኤማውያን ሁኖ በዚያ ጦርነት ሠላሳ ሺህ የእስራኤል እግረኛ ጦር አለቀ፤ ታቦተ ሕጉ ተማረከ፤ አፍኒንና ፊንሐስ ሞቱ፤ አባታቸው ዔሊም በጦሩ ሜዳ የሆነውን ሁሉ አስከፊ ዜና ሰምቶ ከወንበሩ ላይ ወድቆ ሞተ፤ ክብር ከቤተ እስራኤል መራቁንም ቀደም ሲል ተረድተናል።

ከዚህም ጋር እግዚአብሔር ያከበረውን ታቦተ ሕጉን በናቁና ባቃለሉ በአዛና በሜልኮል ላይ የደረሰውን የመውደቅና የመምከን አደጋ ተመልክተናል።

ሁሉም ሰው «ቀዳሚሃ ለጥበብ ፈሪሃ እግዚአብሔር» «የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው» በሚለው መዝሙረ ዳዊት መመራት ይኖርበታል። (መዝ.፻፲፥፲)

«ሕግ ይወጽእ እምጽዮን፤ ወቃለ እግዚአብሔር እምኢየሩሳሌም» ተብሎ በነቢያት አንደበት ተነግሯልና። ✣


# መግረሬ ፀር

ይህ ዓምድ መናፍቃንንና ሕጽራረ ቤተክርስቲያንን የሚያጋልጡ ጽሑፎች የሚቀርቡበት፣ የእምነታችን፣ የጻድቃን፣ የሰማዕታት፣ አማላጅነትና ተራዳኢነት የሚተነተንበት ስለሆነ መግረሬ ፀር ተባለ።


## ልደተ ክርስቶስ የሚከበረው በ፳፱ ወይስ በ፳፰?

ከየኔታ ገብረ ሥላሴ አወቀ የመጻሕፍተ ብሉያትና ሐዲሳት፣ የቅኔና የአቋቋም፣ የመጻሕፍተ ሊቃውንትና ፍትሐ ነገሥት ሊቅ።



የመድኃኔዓለም ክርስቶስን በዓለ ልደት አከባበር አስመልክቶ የተጻፉ ብዙ መጻሕፍት አሉ፤ ልደተ ክርስቶስ የሚከበረው ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ብቻ ነው። ታኅሣሥ ፳፱ መከበር የሚገባ ስለመሆኑም ብዙ መረጃዎችን መጥቀስ ይቻላል፤ ሐዋርያት በዲዲስቅልያ ጽፈዋል፣ ሰለሥቱ ምእትም ወስነዋል፣ በሃይማኖተ አበው ሊቃውንት ጽፈዋል፣ በ፳፰ የበዓለ ልደት ፋሲካ ይሁን የሚል አንድም መጽሐፍ የለም። ልደተ ክርስቶስ በ፳፱ እንዲከበር ከ፳፱ እንደማይወጣና እንደማይወርድ የሚደነግጉ መጻሕፍት ብዙ ናቸው። አለቃ ኪዳነ ወልድም ተንትነው አስቀምጠውታል።

ልደት በዘመነ ዮሐንስ ታኅሣሥ ፳፰ ቀን መከበር አለበት የሚል ሐሳብ ያመጡ ሐሳዊ ሚናስና እንድራኦስ የሚባሉ መናፍቃን ናቸው። እነዚህ

መናፍቃን ጳጉሜ ስድስት ስትሆን በዓል ታፋልሳለች አሉ፤ እኸ እንዴት አድርጋ ታፋልሳለች?፣ ጳጉሜ ስድስተኛይቱ ቀን ደግሞ አራቱ ወንጌላውያን ሦስት ሰዓተ ሌሊት፣ ሦስት ሰዓተ መዓልት ከዮሐንስ ፮ ሰዓት፣ ከማቴዎስ ፮ ሰዓት፣ ከማርቆስ ፮ ሰዓት፣ ከሉቃስ ፮ ሰዓት በድምሩ ፳፬ ሰዓት አንድ ቀን ሆኖ በሉቃስ ትፈጸማለች።

ስድስተኛዋ ቀን ጳጉሜን በዮሐንስ በዓላትን ታፋልሳለች ካላችሁ ግዝረት መቼ ይሁን? ጥምቀት መቼ ይሁን? ትንሣኤስ እሑድን ትቶ ቅዳሜ ይሁን? ቢሉአቸው መልስ አጡ።

መናፍቃኑ እነ ሐሳዊ ሚናስ መስሉአቸው ስለተሳሳቱ ነው እንጂ የልደት በዓል በ፳፱ ነው። ለዘለዓለሙ አይናወጥም። አዘዘነ ሲኖዶስ ዘጸሐፈ ቀሌምንጦስ ካለው ትእዛዝ ስምንት ላይ «ወይግበሩ በዓለ ልደቱ ለእግዚእነ በዕለተ ተወልደ በበዓመት አመ ፳ወ፱ ለወርኅ ታኅሣሥ እስመ ውእቱ ርእሰ በዓላት»፣ ማለትም ቀሌምንጦስ ከጻፈው ሲኖዶስ ላይ «የጌታችን በዓለ ልደት በተወለደበት ዕለት በየዓመቱ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን አድርጉ (አክብሩ) እሱ የበዓላት ርእስ ነውና» ብሏል። በአራቱ ዓመት በአራቱ ወንጌላውያን በ፳፱ ቀን እንዲከበር አዟል።

ዳግመኛም ሐዋርያት በዲድስቅልያ በአንቀጽ ፳፱፣ ሠለስቱ ምዕትም በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፲፱፤ «አኀዊነ ተዐቀቡ በዕለተ በዓላት ዘውእቱ በዓለ ልደቱ ለእግዚእነ ወግበሩ አመ ፳ወ፰ ለታስዕ ወርኅ ዘዕብራውያን፤ ዘውእቱ አመ፳ወ፱ ለራብዕ ወርኅ ዘግብፃውያን» «ወንድሞቻችን ሆይ በበዓላት ጊዜ ተጠንቀቁ እሱም የጌታችን በዓለ ልደቱ በዕብራውያን በዘጠነኛው ወርኅ በ፳፰ኛው ቀን እሱም በግብፃውያን በ፬ኛው ወር በ፳፱ኛው ቀን ነው» ብሏል።

የዕብራውያን ቀን መለወጫ በሚያዝያ ነውና ከሚያዝያ ወር ጀምሮ እስከ ታኅሣሥ ዘጠኝ ወር አለ፤ ወሩንም የሚያብቱ በአምስት (የአቦ) ዕለት ነው። እኛ ግን ከመባቻው

www.ethiopianorthodox.org

ጀምረን ቈጥረን ነው ፳፱ ቀን የምንለውን። እነሱ ከአቦ (ከአምስት ቀን) ጀምረው ቈጥረው ፳፰ኛው አሉ። ይህን አስተውል የኢትዮጵያውያንና የግብፃውያን ዘመን መለወጫ መስከረም ነውና ከመስከረም ጀምሮ እስከ ታኅሣሥ አራተኛው ወር ቈጥሮ በ፳፱ኛው አለ፤ የዲድስቅልያና የፍትሐ ነገሥት ቃሉ ያው ነው። (አንድ ነው) የተለያየ አይምሰልህ። ሃያ ስምንትስ ፍትሐ ነገሥት በ፲፰ አንቀጽ «ድራረ ጾመ ልደት» የልደት ዋዜማ አድርጐ «ጹ.ሙ» አለ እንጂ በዓሉን አክብር አላለም።

ይህን ፋሲካ ማድረግ ድፍረት፣ ዓመጽ፣ ነው።

የወንጌላዊው ማርቆስ፣ ገድለ ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ፣ መጽሐፈ ሐዊ፣ እነዚሁ ሁሉ በ፳፱ ቀን አክብሩ አሉ እንጂ በ፳፰ ቀን አክብሩ አላሉም። ሃይማኖተ አበው ዘቴዎዶጦስንም ተመልከት።

ጌታችን ከተወለደ ጀምሮ እስ ኪሰቀል ወንጌላዊው ዮሐንስ ስምንት ጊዜ ውሏል በዚህ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በ፳፱ ቀን እየወጣች ታከብር ነበር።

ሐዋርያትም በ፳፱ ቀን ያከብሩ ነበርና፣ ልደትን በ፳፱ ቀን አክብሩ ብሏል። ስድስተኛይቱ ጳጉሜን የተረፈው ስድስት ሰዓት ስድስት ሰዓት ተሰብስቦ ፳፬ ሰዓት ይሆናል። ይህም በሉቃስ ይፈጸማል እንጂ ወደ ዮሐንስ አይሻገርም። በዮሐንስ ዕለት እንደ አዲስ አንድ ተብሎ ነው የሚቆጠረው። ምክንያቱም ፳፬ ሰዓቱ በዮሐንስ ብቻ የተገኘ አይደለምና። ጳጉሜን ስድስት ቀን በሆነችበት ዘመን በ፳፰ ቀን አክብሩ ያለ መናፍቅ አንስጣስዮስ ንጉሥ ነበርና በዚህ የተነሣ ፫ መቶ የግብፅ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በሰማዕትነት ሙተዋል።

በደገኛይቱ ዘመን ከግራኝ በፊት በተጻፈ ስንክሣር በ፳፰ ቀን አክብሩ የሚል የለም። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ጐንደር የደብረ ብርሃን ሥላሴ ስንክሣር፣ ጋይንት አንስታ ቈላ እስቴ ከሚባል ሀገር ከአንድ ቦታ ያለ ስንክሣር፣ በዘጌ መሐል ዘጌ ጊዮርጊስ ያለ ስንክሣር በ፳፰ ቀን አክብሩ አላሉም። እንደዚህ የመሰሉ መጻሕፍት በየሀገሩ ቢፈለጉ አልፎ አልፎ አይታጡም።

ቅዱስ ያሬድም ተርታ በዓል ሁሉ «ለእመ ኮነ» እያለ ሲጽፍ፣ ትልቁ የጌታችን የልደት በዓል ግን ጳጉሜን ስድስት ሲሆን በ፳፰ ቀን «ዮም ፍስሓ ኮነ» በል ሳይል በ፳፱ ቀን «ዮም ፍሥሓ ኮነ» ብሎ አምልቶ አስተምሯል። ጳጉሜ ስድስት ሲሆን በዓለ ልደት ወደ ፳፰ ቀን የሚወርድ ከሆነ፣ ግዝረትም፣ ጥምቀትም፣ በዓለ ስምኦንም፣ የግንቦት ልደታን ካለበት አንድ ቀን ወደ ኋላ መውረድ አለባቸው ማለት ነው። ጥምቀት ጥር ፲፩ ቀን መሆኑ ቀርቶ ወደ ፲፣ ትንሣኤም እሑድን ትቶ ቅዳሜ መከበር ነበረበት ማለት ነው። በዓላት ሁሉ ወደ ዋዜማ በወረዱ ነበር ማለት ነው።

ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ «ወባሕቱ አንትሙ አሠረዚአነ ትልው አንት ሙሰ መልአክ እምሰማይ ለእመ መሀረክሙ ካልአ እምዘ መሀርናክሙ ውጉዘ ለይኩን» «እናንተ ግን የኛን ፍለጋ ተከተሉ፤ እናንተስ መልአክ ስንኳ ከሰማይ ወርዶ እኛ ካስተማርናችሁ ትምህርት ሌላ ቢያስተምራችሁ ውጉዝ (የተለየ) ይሁን።» ብሏል ገላትያ ምዕ.፩ ቁጥር ፰።

የእነዚህን መጻሕፍት ቃል መጣስ ድፍረትና ክሕደት ነውና በጥንቱ ትምህርትና ሥርዓት ጸንቶ መኖር ነው። «ሰላመ እግዚአብሔር የሃሉ ምስሌክሙ ወያብርህ አዕይንተ አልባቢክሙ» «የእግዚአብሔር ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን ዐይነ ልቡናችሁንም ያብራ። አሜን።

## መልእክት ለአንባብያን

የፈለገ ጥበብ መጽሔት ቋሚ ደንበኛ ለመሆን ለምትፈልጉ ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች የሚከተለውን የክፍያ መጠን በመፈጸም መጽሔቱን በየ፫ወሩ ማግኘት የምትችሉ መሆናችሁን እየገለጽን፣

ደንበኞች ክፍያውን በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ ለሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሂሳብ ቁጥር 1955 ገቢ በማድረግ ሙሉ ስማችሁን ከነ አድራሻችሁ በፖስታ ሳጥን ቁጥር 81286 መላክ የምትችሉ መሆናችሁን የምናረጋግጠው በደስታ ነው።

| ቦታ | የሁለት እትም /ግማሽ ዓመት | የአራት እትም የዓመት |
|---|---|---|
| አዲስ አበባ | 6.25 | 12.50 |
| ክፍለ ሀገር | 7.00 | 14.30 |
| ውጭ ሀገር | 4 ዶላር | 8 ዶላር |

በተጨማሪ በደርዘን ለመውሰድ የሚፈልጉ ደምበኞቻችን በቅናሽ ዋጋ ጠቅላይ ቤተክህነት በሚገኘው ቢሮአችን ብቅ ቢሉ የፈለጉትን ያገኛሉ።

በአዲስ አበባም ሆነው መመዝገብ የሚፈልጉም በአካል ቀርበው መመዝገብ የሚችሉ መሆኑን እንገልጻለን።

# ሥርዓተ ቤተክርስቲያን

## የጥምቀትን ጥቅም የተረዳው ይኖር ይሆን?

በብፁዕ አቡነ ሰላማ
የሰሜን ጎንደር አገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ

«ያመነ የተጠመቀ ይድናል» ማር.፲፮፥፲፮

ይህ ቃል የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መሪ ቃል ነው። ጥምቀትን ካነሣን ዘንድ ጥምቀት በብሉይ ኪዳን በምሳሌነት ይነገር ነበር። በነቢዩ ሕዝቅኤል አድሮ ትንቢቱን እንዲህ በማለት ይገልጻል። «በተቀደስሁባችሁ ጊዜ እኔ እግዚአብሔር እንደሆንሁ አሕዛብ ያውቃሉ» ይልና እግዚአብሔር ከአሕዛብ መካከል የተማረኩ ሕዝበ እስራኤልን እንደሚያወጣቸው ከየሀገሩ ሁሉ እንደሚሰበስባቸውና ወደየሀገራቸው ወደ ገዛ ምድራቸው እንደሚያመጣቸው በማስመልከት ከተነበየ በኋላ «ጥሩ ውኃንም እረጭባችኋለሁ እናንተም ትጠራላችሁ ከርኩሰታችሁም ሁሉ፣ ከጣዖቶቻችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ፣ አዲስም ልብስ እሰጣችኋለሁ፣ አዲስም መንፈስ በልባችሁ ውስጥ አኖራለሁ፣ የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ፣ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ» ይላል ሕዝ.፴፮፥፳፭–፳፯

ከዚህ ላይ ማየት ያለብን ምስጢር በውኃ መረጨትን ሳይሆን ያደፈው የቆሸሸው ልብስ፣ ያስከፋው የከረፋው ሰውነት በውኃ ጸድቶ የምናየው በማይታይና በማይመረመር ምስጢር ነው። ቆሻሻው ውልቅ ብሎ አምሮ ተዘጋጅቶ የሚገኘው ልብስ ውኃው ሲገባ፣ ጣት ኖሮት በጣቱ መርምሮ፣ ጥፍር ኖሮት በጥፍሩ ሰርስሮ፣ እድፉን፣ ቆሻሻውን ሲያስለቅቀው አናይም። ይህም ሰው ተጠምቆ ከኃጢአት ደዌ፣ ከፍዳ፣ ከቁራኝነት፣ ከፃዕር፣ ከገዓር በጠቅላላው ከዲያብሎስ ግዛት፣ ከጨለማው አርነት ሲላቀቅ በማይመረመር ምስጢራዊ ግብር መሆኑን በትንቢተ ነቢያት ምሳሌነት ልንረዳው ይገባናል። በውኃ ያልታጠበ ልብስ ትቢያ ቅሞ፣ ቆሻሻ ተሸክሞ፣ ጢስ ጠጥቶ ጥቀርሻ መስሎ ሲታይ እጅግ የሚያስጠላ ሆኖ ከመታየቱም ሌላ በሰው ፊት ለብሰውት ሊቆሙ የማይገባ ሆኖ ይገኛል። ሰውነትም ቢሆን ውኃ ከተለየው ይሸታል፣ ይቀረናል፣ በእድፍ ይቆራረጣል፣ በልዩ ልዩ ደዌ በእከክ ባልታወቀ ቁስል ይቆራመዳል፤ ደሙ እዥ መግሉ በላዩ ላይ ፈሶ የተለያዩ ተሐዋስያን ከበውት በላዩ ሰፍረው ማየት ለዓይን ያስከፋል፣ ላፍንጫም ይከረፋል። ሰብአዊ ክብሩ ተገፎ፣ አንገቱን ሰብሮ፣ ሰው ሁሉ ርቆት የብቸኝነት ባሕር አጥልቶት ትካዜ መትቶት የኃዘን መዝናኛ ሆኖ ሲያዩት እጅግ ያሳዝናል። ይህ ሁሉ መሆኑ ታዲያ ጽዳት የማያስወድድ ደዌ ስለተጸናወተው ብቻ ነው። በውኃ ቢታጠብ ይህ ሁሉ ስቃይ ሊፈራረቅበት ባልቻለም ነበር፤ የውኃንም ጥቅም ባለ ማወቅ በመርገም ጨርቅ ድንቁርና ተጠቅሎ በችግር ገመድ ተጠልፎ ወደሚወድቁበት ዓለም ባልተጣለም ነበር። እንግዲህ አንባቢያን ወገኖቼ በሰቂለ ሕሊና በአንቃዕድዎ ልቡና ሆናችሁ ይህን ጥልቅ ምስጢረ ጥምቀትን መርምሩ፤ ልብሱን ያላጠበ ሰው–ነቱን በውኃ ያልታጠበ ሰው በተሰጠው ሰብአዊ አእምሮ ጉድለት ባለመጠቀሙ ይህ ሁሉ ጉዳት የሚደርስበት ከሆነ «ያመነ የተጠመቀ ይድናል» ብሎ አምላክ ያዘዘውን ትእዛዝ የናቀ ያቃለለ፣ አምኖ በጥምቀት ከውኃ ከመንፈስ ያልተወለደ ሰው በነፍስ የሚያገኘው ፍዳ፣ ጥልቀቱ፣ ምጥቀቱና ርዝመቱ ምን ያህል መሆኑን የመረዳት ዳኝነቱን ለሕሊናችሁ ሰጥቼ፣ ርኩሰት ወደሚለው ቃል ስመለስ ርኩሰት ከመሠረቱ የሕሊና ርስሐት ነው። ከሕሊና የሚወጣው አላስፈላጊ ነገር ሁሉ ከውስጥ የሚወጣ ስለሆነ ርኩሰት ይባላል። ይኸም የሚነጻው በምሥጢራዊ መልእክት ይሆናል። ሕሊና የክፋትና የበጎነት መዝገብ ስለሆነ የጨለማ አበጋዝ የዲያብሎስ ግብር መጣያ ርስት የሚሆንበት ጊዜ አለ፤ ደግሞም የመንፈስ ቅዱስ ግብር መጣያ ርስት የሚሆንበት ጊዜ ይኖራል። ክህደትን፣ ኑፋቄን፣ ተንኮልን፣ ምቀኝነትን፤ ሐሰት መናገርን በሚፈጽምበት ጊዜ፣ ርስተ ዲያብሎስ ይሆናል። በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን በሚመራበት ርኅራኄን፣ ቸርነትን፣

www.ethiopianorthodox.org



በጠቅላላ ምግባረ ሠናይን በሚፈጽምበት ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ይሆናል። ሕሊና የበጎውም የክፉውም መግቢያ መውጫ እንደመሆኑ መጠን የእግዚአብሔር ወገን ሆኖ ሲገኝ ሰውየው በብፅዕና በ ቅ ድ ስ ና ይወሳል፤ የዓለም ወገን ሆኖ ሲገኝ ከኋላየ ሂድ ሰይጣን ተብሎ ተግሳጽ ይወርድበታል። በመረጃ ለመጠቀም ካስፈለገም ማቴ.፲፮፥፲፯–፳፪ ይመልከቱ።

ይህ አባባል ያስፈለገበት ዋና ምክንያት ሕሊና ረቂቅ እንደ መሆኑ መጠን ሰው ሁሉ አምኖ ቢጠመቅ የፈጣሪውንም ትእዛዝ ቢጠብቅ በረቂቅ ምስጢረ ጥምቀት ሕሊናው ከርኩሰት ይነጻል ለማለት ነው። ከዚህም ጋራ ኢዮብ በዮርዳኖስ ውኃ ታጥቦ ከደዌው ተፈውሷል፤ ኢዮብ የምእመናን፣ ዮርዳኖስ የአማናዊው ጥምቀት፣ ደዌ ሥጋ የፍዳ የመርገም፣ ድኅነተ ሥጋ የድኅነተ ነፍስ ምሳሌ ነው። ስንክሳር መስ፩ ተመልከት። በሌላም በኩል የሶርያ ንጉሥ ሠራዊት አለቃ የነበረው ንዕማን ወደ እግዚአብሔር ሰው ወደ ኤልሳዕ መጥቶ ከደዌ ለምጽ እንዲፈወስ ኤልሳዕ ምክሩን በትእዛዝ መልክ ቢለግሰው ተቆጥቶ ምክሩን በመናቅ (በማቃለል) ወደመጣበት ሲመለስ ባለሟሎቹ ቀርበው ቢመክሩት ምክራቸውን ተቀብሎ የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ እንደተናገረው በዮርዳኖስ ገብቶ ሰባት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ብሎ ቢወጣ ከደዌ ለምጹ ተፈውሶ ሥጋው እንደገና እንደ ትንሽ ብላቴና ሥጋ ሆኖ ንጹሕም ሆኖ መመለሱ ተነግሯል። (፪ነገሥ ካል.፭፥፱)። ይህም ከኢዮብ ታሪክ ጋራ የተያያዘ ምሳሌ ነው። ከዚህ በላይ የአማናዊው ጥምቀት ምሳሌ ሆኖ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ወደ ዋናው ጥምቀት ዓላማ ዝርዝር ከመግባታችን አስቀድሞ ጥምቀት በምን ምክንያት መጣ? የሚለውን ግንዛቤ መውሰድ ግድ ሊሆንብን ነው። ለማንኛውም ነገር ምክንያትና መነሻ እንዳለው ሁሉ ለዚህም ምክንያትና መነሻ አለው። ቃሉንም ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ካስተላለፈው መልእክቱ ተነሥተን ለሕሊናችን እናጉርሰው፤ አእምሯችንን እናለስልሰው፤ እነሆ ቃሉ «ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ደርሶ ሞት ነገሠ አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው ለእርሱ አምሳሉ ነውና» ካለ በኋላ ሸጦታው እንደ በደሉ መጠን አለመሆኑን በአንድ ሰው በደል ብዙዎች ለሞት መዳረጋቸውንና ደግሞ በአንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ስጦታ ከዚያ ይልቅ ለብዙዎቹ ቤዛ መሆኑን ይገልጻል። ሮሜ.፭፥፲፬ ይህ ቃል የሚያመለክተን በአዳም መተላለፍ ምክንያት ወደ ዓለም የገባው ተንቀሳቃሽ የዲያብሎስ ጦር ሞት፣ በዳግም አዳም በክርስቶስ ጥምቀት መከላከያ ኃይልነት በዮርዳኖስ መደምሰሱንና ድል መነሳቱን ነው። በዚህም ምክንያት ሞት ነግሦ እንደ ነበረ ሁሉ፣ ሕይወት በክርስቶስ ላመነ ሁሉ ነገሠ። ነፃነት ተሰበከ፣ መራራው የኃጢአት ፍዳ ጠፋ። ሆኖም ወደ አማንዊው ጥምቀት ታሪክ ከገባን ዘንድ አማናዊው ጥምቀት በአራት ይከፈላል፤ ፬ ወገን ነው።

፩ኛ. የጌታ ጥምቀት፣

፪ኛ. የንስሐ ዕንባ፣

፫ኛ. የሰማዕታት ደም (ደመ ሰማዕታት)

፬ኛ. ባሕረ እሳት ናቸው።

የጌታ ጥምቀት በማቴዎስ ወንጌል እንዲህ ሲል የምናገኘው ቃል ይሆናል። «ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ለመጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ» ካለ በኋላ፣ ዮሐንስ ግን ሎሌ በጌታ እጅ ይጠመቃል እንጂ ጌታ በሎሌ እጅ ይጠመቃል? እኔ በአንተ እጅ እጠመቃለሁ እንጂ አንተ በእኔ እጅ ትጠመቃለህ? ብሎ እንደ ተከላከለ ጌታችንም መልሶ የነቢያትን ትንቢትና ጽድቅን መፈጸም አለብንና ተው እንዳለው፣ በዚህም መሠረት ወደመጠመቂያው ዮርዳኖስ ወርደው እንዳጠመቀው፣ ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ሰማያት እንደተከፈቱ ታይቷል። ከዚያ በፊት ተነግሮ የማያውቅ ነገር ተነገረ፤ ያልተገለጸ ምሥጢር ተገለጸ፤ ይህም ያልተገለጸ ምሥጢር ተገለጸ ያልነው፣ አካላዊ ቃል በተለየ አካሉ በለበሰው ሥጋ በዮርዳኖስ ቆሞ፣ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ መታየት፤ ተነግሮ የማያውቅ ነገር መነገር፤ ማለትም አብ በደመና ሆኖ «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» ብሎ ድምፅ ማሰማት፣ በዚህም ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ያልተገለጸ ምሥጢር አንድነት፣ ሦስትነት መገለጽ ነው። ጥምቀት ማለትም ለሚያውቀውና ለሚረዳው ይህን ሁሉ የምሥጢር ቁም ነገር ያሠፈረ ወደብ ማለት ነው። የጌታችንንና የሌላውን የጥምቀት ዘይቤ ለይቶ ማወቅ ይገባል። የጌታችን ጥምቀት ባሕርያዊ ነው። የኛ የጸጋ፣ እሱ ዮርዳኖስ ገብቶ መጠመቁ ለማክበር፣ ለመቀደስ እንጂ ላለማክበር፣ ላለመቀደስ አይደለም። ለምሳሌነት፣ ለአርአያነት ለመጥቀም እንጂ፣ ለመጠቀም፣ አይደለም። እኛ ግን በክብሩ ለመክበር በቀዳሽነቱ ለመቀደስ፣ በአርአያነቱ፣ በምሳሌነቱ ለመጠቀም ከሰይጣን አርነት ቁራኝነት ለመላቀቅ ነው። ስንጠመቅ ከኃጢአት ከቁራኝነት እንላቀቃለን ቅብዐ ሜሮን ስንቀባ እንደተለሰነ እንዳተሰቀለቀ ቤት እንሆናለን።

ሜሮን ስንቀባ ንጉሥ ከነባለሟሎቹ እንደገባበት ቤት እንሆናለን፤ እኛ ይሄንን ሁሉ ከሱ እናገኛለን እንጂ እርሱ ከጥምቀት የሚያገኘው ነገር ምንም የለም። ይህም ሁሉ ሆኖ በሰማይና በምድር ያለ ሥልጣኑን ለካህናት፣ ላመነበት ሁሉ ለማስገብየት፣ ደቀመዛሙርቱን «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው። እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከናንተ ጋር ነኝ» ብሎ አዘዛቸው። (ማቴ.፳፰፥፳፱–፳) እነሱም ቃሉን አክብረው በልዩ ልዩ አምልኮት ተተብትቦና ተጠፍሮ ወዳለው ዓለም በሕይወታቸው ቆርጠው በመግባት በተከፈተላቸው የሕይወት በር ወራሪውን የዲያብሎስ ጦር አሳፍረው በሥጋ ደዌ የገባውን በተአምራት፣ በነፍስ ደዌ የገባውን በትምሕርት መሳሪያ እያርበተበቱ ከባሕርዩ የምትነቃ መርዙን እያጠፉ፣ አሽክላውን እየቆረጡ፣ በጊዜው ማደሪያ እያሳጡ መንፈሳዊ አርበኝነታቸውን አጠናክረው የቃል ኪዳን አገራቸው ወንጌልን አደራጅተው፣ ለምእመናን የሥላሴን የልጅነት ሉል አስጨብጠዋል። ጠላት ዲያብሎስ የከታመባቸው ጣዖታትን እያፈራ ረሱ መስቀለ ክርስቶስ እንዲተከልባቸው፣ ቤተክርስቲያን እንዲታነጽባቸው፣ ምእመናን እንዲያመልኩባቸው፣ ፈጣሪ እንዲመሰገንባቸው አድርገዋል። በዚህም ዛሬ አማኝ ትውልድ ከክሕደት፣ ከቀቢጸ ተስፋ ተላቆ በጥምቀት መንፈሳዊ የነፃነት ፀሐይ ሙቀ በእምንቱ የሚኮራበትን ርስት መንግሥተ ሰማያትን ያስጨበጡት እነዚሁ በዓለማቸው ጸንተው ለዓለም መንፈሳዊ ነፃነት፣ ለፍትሕ፣ ለሰላም፤ ለእኩልነት፣ ግብዝነት ለሌለው ፍቅር ሲዋደቁ፣ ጠባብተኝነትን፣ ዘረኝነትን፣ ጕጠኝነትን፣ እነዚህን የሰይጣን መደብሮች በማፈራረስ የአንድነትን ማዕከል በጥምቀት በመመሥረት ዓለምን ሲያገለግሉ የዲያብሎስን አፍራሽ ተልዕኮ በመቃወም ነበር። «የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ልበሱ። መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፣ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር፣ ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዥዎች ጋር፣ በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፉት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ» (ኤፌ.፮፥፲፩–፲፫፣ ፩ጴጥ.፭፥፰፣ ያዕ.፬፥፯።)

እንዲህ እንዲህ እያሉ በዲያብሎስ ሥልጣን ሰንሰለት የኋሊት ተጠፍሮ ታስሮ የነበረውን ጣኦታዊ ዓለም በጥምቀት ፈተው ሕዝብና አሕዛብን ከተበታተነበት አሰባስበው የአንድነት ችቦ፣ የነፃነት ፋና እንዲያበራ ሲያደርጉት፣ አንዱን ከአንዱ በማብለጥ ወይም በማሳነስ አልነበረም። በሥርዓተ ጥምቀት ንጉሡን ከሠራዊቱ፣ ዘመዱን ከባእዱ የሚለዩበት ሕግ አልነበራቸውም። የንጉሡን ስም ለሎሌው፣ የንግሥቲቱን ስም ለገረዲቱ እንዴት እንሰጣለን ብለው የበላይና የበታች ማሳወቂያ ስርዓት በጥምቀት አልሠሩም። ኃይለ ሥላሴ የንጉሡ ስም ቢሆን ደኀውም ክርስትና ሲነሳ በዚሁ ስም ይጠራበታል። የንግሥቲቱና የገረዲቱም እንደዚሁ ከላይ እንደተነገረው በቀለም በዘረኝነት በድኃ በባለፀግነት መካከል በጥምቀት ልዩነት ቢኖርማ ኖሮ ጊዮርጊስ፣ መርቆሬዎስ፣ ቂርቆስ፣ ፋሲለደስ፣ ፀቱ ቅዱሳን፣ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ከኢትዮጵያውያን ጋራ ምንም ግንኙነት ባልነበራቸውም ነበር። አገናኝቶ ያዋደደን፣ ያከባበረን፣ አንድ ያደረገን ጥምቀት አይደለምን? ከቶ የጥምቀትን ውለታ፣ የጥምቀትን ጥቅም የተረዳው ይኖር ይሆን? እንግዲህ የሥጋ ፈውስ የነፍስ ፈውስ፤ የሥጋ ድኅነት የነፍስ ድኅነት መሆኑን ተረድተን፣ የጥምቀትንም ጥቅም አውቀን መኖር ያለብን መሆኑን ለማሳሰብ ያህል የቀረበ ሥነ ጽሑፍ ነውና እዚሁ ላይ እንዲቆየን ይሁን። ✣

www.ethiopianorthodox.org

# ትምህርተ ሃይማኖት

አሚንሰ እምሰሚዕ

ማመን ከመስማት የተነሣ ነው

ወእምሰሚዕ አሚን በቃለ እግዚአ ብሔር ክርስቶስ

ከመስማት የተነሣ ማመንም በእግ ዚአብሔር ቃል በክርስቶስ በእግዚ አብሔር በባሕርይ ሕይወቱ በመንፈስ ቅዱስ ነው።

ዲዮ በሰቂለ ሕሊና በነቂሐ ልቡና ሁነን ወደ እግዚአብሔር በጸሎት እናመልከት። ያን ጊዜ በመለኮት ከተ ጻፉ፣ የመለኮትን ነገር ከሚናገሩ ከቅ ዱሳት መጻሕፍት ምሥጢር ይገለጥ ልናል። ከመጻሕፍት አግኝተን ከሊ ቃውንት ጠይቀን በመረዳት የሦስቱን ስም በመጥራት አዋቂዎች እንሆ ናለን። ይኸውም እምነታችን ነው። ለመላእክት ሁሉ ጸጋው ክብሩ ከነሱ የሚገኝላቸው ሥላሴን እናመሰግ ናቸዋለን። ጸጋን ክብርን ልጅነትን በመላእክት እንዳሳደሩ መጠን በኛም ላይ በማሳደራቸው ካለመኖር ወደ መኖር፣ ካለመታየት ወደ መታየት፣ ካለመዳሰስ ወደ መዳሰስ፣ ከርቀት ወደ ግዘፍ፣ አምጥተው በሰማይ በም ድር ያለውን ፍጥረት ሁሉ በርህቀት በርቀት ፈጥረው ያስገኙ እነሱ ናቸውና።

፩. በርህቀት ናጌብን፣ አድማስን፣ ብሔሞትንና ሌዋታንን፣ ሰዎችን፣ ምድርን፣ ባሕርን፣ እንስሳትን፣ አራ ዊትን፣ አዕዋፍን ሌሎችንም በተመ ለከተ ነው፤

፪. በርቀት ነፋሳትን፣ ነፍሳትን፣ መላእክትን በየነገዳቸው ወስነው ያኖሯቸው እነሱ ናቸው። ገዥዎ ቻቸው በሕይወትም የሚያኖሯቸው ናቸውና በሃይማኖት ይመረጣሉ ወደ ነሱ የሚቀርቡትን በልጅነት ይቀበላሉ ወይም ከነሱ ርቀው የነበሩትን በንስሐ ይቀበላሉ፤ ለሁሉ የሚያዝኑ የሚራሩ ይቅር ባዮች ናቸውና። በተፈጥሮ ከተሰጠው የጸጋ ክብር ተለይቶ በኃጢአት በክሕደት በስርቆት፣ ነፍስ በመግደል፣ በዝሙት ያረጀውን የሰው ልጅ ሕይወት በንስሐ ያድሳሉ፤ ያነጻሉ፤ ያከብራሉ፤ በኃጢአት የደከሙትንም በንጽሕና በቅድስና እንዲጸኑ የሚያደርጓቸው እነሱ ናቸው። በምግባር በሃይማኖት ወደነሱ የሚቀርቡትን ወደ ጸጋ ወደ ክብር መርተው የሚአደርሷቸው እነሱ ናቸው። ዕውቀትን ምሥጢርን የሚገ ልጡ ብርሃናት ናቸው። ፍጹምነት የሚገባቸው በሃይማኖት ፍጹማን የሚያደርጉአቸው፣ በሃይማኖት በምናኔ ከዓለም የተለየ ብቸኛውን በንጽህናው የሚዋሐዱት እነሱ ናቸው። ደጋጉን መላእክት ሁሉ በረቂቁ ዓለም ረቂቅ ሹመት ሹመው

> ## አሚንሰ እምሰሚዕ
> ## ማመን ከመስማት ነው
>
> ከብፁዕ አቡነ እንድርያስ ጳጳስ
>
> የሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ
> ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት የበላይ ኃላፊ

ያከበሩ፣ ዲያብሎስን ያዋረዱ፣ ለሚገባቸው ረቂቅ ጸጋን የሚሰጡ ናቸው። የሕያዋን ሁሉ ሕይወት ናቸው ከማለት አንደበታችንን አንወስንም። ሰውን ሁሉ የፈጠሩ ናቸው፤ ቅድመ ዓለም የነበሩ ዛሬም ያሉ ወደፊትም ለዘለዓለሙ በሕያ ውነት ጸንተው ሁሉን አሣልፈው የሚኖሩ ናቸው። ሀብታት ምሥጢራ ትንም የሚያድሉ ናቸው። መለኮት ከጻፋቸው አንድነትን ሦስትነትን ከሚናገሩ ቅዱሳት መጻሕፍት ይህንን ተምረናል። ዳግመኛም የሚያመሰግኑ ምዕመናንን በመለኮት አነጋገር እርሱ አምላክ እንዲባል አማልክት ሲባሉ አባት ናቸው «አማልክት አንትሙ ወደቂቀ ልዑል ኵልክሙ» ተብሎ እንደ ተጻፈ አምላክ መባል ለሥላሴ ባሕርይ ለሥላሴ አካል የሚገባው ስለሆነ ስለዚህ ነገር አንድነቱን የሚያመሰግኑ ሦስቱን ያመሰግናሉ፤ እነሱን ብቻ ያገለግላሉ፤ የማይመ ረመር የማይለይ አንድነታቸውን እየተናገሩ። ከፍጡራን ሁሉ የራቀ የረቀቀ ልዩ ነው፤ በባሕ... ናቸውና አንድ ስለሆን አንድ ይባላሉ። የሥላሴ ገጻት በየቅርጻቸው ልዩ ልዩ ሲሆኑ በመለኮት አንድ አድራጊነት ጸንተው ይኖራሉ። ሦስቱን ለማስ ረዳት ሦስት እንደ ሆኑ አውቀው አመሰገኑአቸው።

እነዚህም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ናቸው።

አንድ ሲሆኑ ሦስት እንደ ሆኑ አውቀው መላእክትም ሰዎች በአንድ ነት አመሰገኑአቸው።

አብ ብርሃን ወላዲ አሥራፂ ጥንት አሥገኝ ይባላል

ወልድ ከብርሃን አብ የተወለደ ብርሃን ተወላዲ ጥንት አሥገኝ ነው ይባላል። መንፈስ ቅዱስም ከብርሃን አብ የተገኘ ብርሃን ሠራፂ ጥንት አሥገኝ ሕይወት ይባላል። ከአብ የወልድ መወለድ የመንፈስ ቅዱስ መሥረጽ በዕፁብ ይወሰናል። (ዕፁብ ዕፁብ ዕፁብ) ይባላል እንጂ እንዲህ ነው ተብሎ አይነገርም። ከሰው ከመላእክት አእምሮ (ሕ...ናት) ሁሉ የራቀ የረቀቀ የተሰወረ ነው አይመረመርም። በዚህ ዓለም ንጉሥ ገዥ አለቃ ጳጳስ ሊቀ ጳጳስ ፓትርያርክ ተብሎ የሚሾመው ሁሉ ከነሱ የተሰጠ ነው፤ የ... አሥገኝ መገኛ ናቸውና ሁሉን የፈጠሩ ናቸው። ሁሉም በቸርነታቸው ለመፈጠር ለመገኘት ለመ?ለጥና ለክብር በቅቷልና አመሰገኑአቸው። በመፍጠር በማስገኘት በማክበርና በመመገብ ዕውቀት የባሕርያቸው ነውና አመስግኑአቸው። ሰዎች ሁሉ ከክህደት ከኃጢአት ተለይተው በምግባር፣ በሃይማኖት ፍጹማን በሆኑ ጊዜ በባሕርያቸው ሳያዩአቸው በዘፈቀደ ተገልጸው ለሰዎች አእምሮ በሚታወቅና መረዳት በሚችልበት ተግባር ምሥጢር ይገለጡላቸዋል። ሰውን እንደ መውደዳቸው መጠን። ይኸውም ሊታወቅ ከሦስቱ አካላት በአንዱ አካል በእውነት ተዛምደ ውናልና። ✥

# እኔም ወጣት ነበርኩ

## ለ፵፬ ዓመታት በቤተ ጉባኤ

የብዕር ቅኝት በመምህር ዕንቈ ባሕርይ ተከ...


የኔታ ሄኖክ ወልደሚካኤል ይባላሉ የዛሬ ያክብር እንግዳችን የኔታ ሄኖክ በአሁኑ ጊዜ በጐንደር ከተማ በደብረ ኃይል ወደብረ ጥበብ በአታ በአባቶቻቸው እግር ተተክተው እልፍ አዕላፍ ሊቃውንት እያስተማሩ በማስማራት ጥንታዊውን የአባታችን የቅዱስ ያሬድን ዜማ ሳይበረዝ ሳይከለስ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ በማድረግ ላይ ናቸው።

ዛሬ እሉን ከምንላቸውና በመጀመሪያ ምዕራፍ ከምናገኛቸው ታላላቅ ሊቃውንት አንዱ ናቸው። ምን ጊዜም ከየአቅጣጫው ወደ ጐንደር የሚጐርፈው ተማሪ ከየኔታ ሄኖክ ትምህርትንና እውቀትን ለመቅሰም ነው።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አሉኝ ከምትላቸው የአብነት ምስክር ቦታቸው አንዱ ጐንደር ደብረ ኃይል ወደብረ ጥበብ በዓታ ሲሆን የዚሁ የአብነት አባት ወይም ርዕሰ ማዕምራን እንደ ዘመኑ ቋንቋ ፕሮፌሰር የኔታ ሄኖክ ናቸው።

የኔታ ሄኖክ ዛሬ ዕድሜያቸው ፸፬ ዓመት ሆኗቸዋል። እንደዚያም ሆነው አሁንም ለአንድ አፍታ እንኳን ወንበር አያቋርጡም። እኒህ ታላቅ ሊቅ ወንበር ዘርግተው፣ ጉባኤ አስፍተው ማስተማር ከጀመሩ ፵፬ ዓመታት ሆኖአቸዋል።

በዚህም ጊዜ እልፍ አዕላፍ ልጆችን በእውቀት ወልደዋል፤ አሳድገዋል። አሁንም የማስተምርበት አዳራሽ ስሩልኝ፣ የምቀመጥበት ወንበር አምጡልኝ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በዚያ በትልቁ ወይራ ሥር ሆነው በማስተማር ላይ ይገኛሉ። መላ ሕይወታቸውን ከቃለ እግዚአብሔር ሳይለዩ፣ ቃለ እግዚአብሔሩም ከእሳቸው ሳይለይ በመገኘቱ፣ ሊቃውንት ልጆቻቸው ይኮሩባቸዋል፤ ይመኩባቸዋል። እኒህ ታላቅ ሊቅ ዛሬ በዚህ ዝግጅት ብዙ የሚነግሩን አለና እንከተላቸው።



**ፈ**ለገ ጥበብ – ለአንባብያንና ...ሪክ ተመራማሪዎች ግልጽ ለማድ ረግ ይቻል ዘንድ የተወለዱት በየት ኛው ቦታ? በስንት ዓመተ ምሕረት ነው? የወላጆችዎ ስም እነማን ይባላሉ?

**የ**ኔታ ሄኖክ – የተወለድኩት በላስታ ነው አውራጃው ዋግ ሲሆን ልዩ ስሙ ጻድቃኔ ማርያም ቤተክር ስቲያን ነው። የተወለድኩበት ዓመተ ምሕረት በ፲፱፻፲፱ ዓ.ም ነው። አባቴ ወልደሚካኤል ዕንቈ ሥላሴ፣ እናቴ ወይዘሮ ጣፈጠች ዓለሜ ይባላሉ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – መንፈሳዊ ትምህ ርት መማር የጀመሩት መቼ ነው?

**የ**ኔታ ሄኖክ – መንፈሳዊ ትምህ ርት የጀመርኩበት ጊዜ በሕፃንነቴ ነው። እምብዛም በጣም ትዝ አይለ ኝም። ካወቁ ነው ወደቅኔ ቤት የወጣሁት በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ነው። ከ፲፱፻፴፫–፲፱፻፴፯ ዓ.ም በቅኔ ቤት ነው የነበርኩት።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ቅኔ የተማሩት ከማን ነው?

**የ**ኔታ ሄኖክ – ከአለቃ መኮንን ሰዳክዩ ላስታ ወስኄ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

**ፈለገ ጥበብ** – ከሕፃንነትዎ እስከ ቤተ ጉባኤ ያለው የታሪክ ጉዞዎ ሰፋ አድርገው ቢገልጹልኝ?

**የኔታ ሄኖክ** – ያለኝ ታሪክ የትምህርት ታሪክ እንጂ ሌላ የለኝም። ለመማር የወጣሁት በ፲፪ ዓመቴ ይሆናል። ትምህርቱን ያጠቃለልኩት በመምህርነት እስከምመረቅ ድረስ በአጠቃላይ ፲፯ ዓመታት ነው።

**ፈለገ ጥበብ** – ዜማና ሌላም መንፈሳዊ ትምህርት ከእነማን እንደ ተማሩ ቢያስረዱኝ?

**የኔታ ሄኖክ** – የቅኔውን አሁን ገልጬዋለሁ፤ ዜማ ደግሞ ያው አለቃ መኮንን ይባላሉ። በዋግ ውስጥ የነበሩ ናቸው።

**ፈለገ ጥበብ** – እሳቸው ሙያቸው ምንና ምን ነበረ?

**የኔታ ሄኖክ** – ቅኔና ዜማ፤ ድጓ ነው።

**ፈለገ ጥበብ** – የአቋቋም ታች ቤት፣ ላይ ቤት፣ ሳንኳ፣ መጻሕፍተ ትርጓሜያት የተማሩት ከእነማን ነበረ?

**የኔታ ሄኖክ** – መቼም መጀመሪያ የተማርኩት ላይ ቤት ነው። ኋላ ታች ቤት በበዓታ ነው የተማርኩት።

**ፈለገ ጥበብ** – ላይ ቤት ከማን ነው የተማሩት?

**የኔታ ሄኖክ** – ላይ ቤት በላስታ ከነበሩ መርጌታ ታረቀኝ፣ ታች ቤት ግን ያው ከዚያው ጐንደር በዓታ ነው።

**ፈለገ ጥበብ** – ማን ከሚባሉ?

**የኔታ ሄኖክ** – ከየኔታ ክፍሌ ወልደጻድቅ ዘብሔረ ሸዋ ልዩ መንደራቸው ሰለሎ ቅዱስ ሚካኤል።

**ፈለገ ጥበብ** – ሳንኳስ በማድመጥ ነው ወይስ ወንበር ነበረው?

**የኔታ ሄኖክ** – ሳንኳ ወንበር የለውም፤ በማድመጥ ነው። ላይ ቤት ቢሆንም ከዚያ ወዲህ ወንበር የለውም። እኔ መጀመሪያ ያስተማሩኝ ላይ ቤት ስለነበር ነው።

**ፈለገ ጥበብ** – ለምንድነው ወንበር እንዳይኖረው የሆነው?

**የኔ** የሚል ስለጠፋ ነው። ነገሩን ግልጽ ቢያደርጉልን የኔታ ሄኖክ ላይ ቤት የሚያስተምሩት ሊቃውንት እያለቁ ስለሄዱ ከዚያም የኔ ብሎ የሚያስተምር ስለአልተገኘ ነው።

**ፈለገ ጥበብ** – የታች ቤት አቋቋም፣ የላይ ቤት፣ የሳንኳ አቋቋም አመሠራረት እንዴት ነው? አሁንስ ያለው ደረጃ?

**የኔታ ሄኖክ** – መቼም አሁን ባለበት ደረጃ ላይ ቤትና ሳንኳ በትምህርት ገበታ የለም። አይሰጥም። አሁን በጠቅላላው የሚሰጠው የታች ቤት ትምህርት ነው።

**ፈለገ ጥበብ** – የላይ ቤት አመጣጥስ?

**የኔታ ሄኖክ** – ላይ ቤት የሚለው ፊት የትርጓሜ መጻሕፍት ስያሜ ነበር፤ የታች ቤት አማርኛ፤ የላይ ቤት አማርኛ፤ እየተባለ ኋላ ወደ አቋቋም ተዛውረዋል።

**ፈለገ ጥበብ** – የሳንኳ አቋቋምስ?

**የኔታ ሄኖክ** – ሳንኳ እንኳ ቀለሙን ያቀኑት ሳንኳ ከሚባል ከጐጃም የሄዱ ናቸው። ቀለሙ ግን ከጐጃም ሄደ ማለት አይደለም። ከዚያ ነው ያቀኑት እነሱ ሥር መሠረታቸው ከዚያ ስለመጡ ቀለሙ በእነሱ ስያሜ ተሰይሟል።

**ፈለገ ጥበብ** – የሳንኳን ቀለም በአብነት ይዘውታል ተብለው ከሚታመንባቸው የጐንደር አብያተ ክርስቲያናት እነማን ናቸው?

**የኔታ ሄኖክ** – የመጀመሪያ ደብረ ፀሐይ ቁስቋም በሳንኳ አውራይቱ ናት።

**ፈለገ ጥበብ** – ደብረ ብርሃን ሥላሴስ?

**የኔታ ሄኖክ** – ደብረ ብርሃን እንግዲህ ቀለሙ ሳንኳ ነው ልክ ነው። ግን ሳንኳ ተብሎ አይነገርም ነው የሚባለው። ሳንኳ የሚባል የሃይማኖት ልዩነት ስለነበር ደብረ ብርሃኖች ሳንኳ ቢሉዋቸው ይቀየማሉ። ደብረ ብርሃን ተዋሕዶ ነው ሳንኳ የሚባለው ቅብአት ነው ይባላል። የራሳቸው ቀለም። «ድኲሌ ቤት» ይሉታል።

**ፈለገ ጥበብ** – «ድኲሌ» ማለት ምን ማለት ነው?

**የኔታ ሄኖክ** – የንጉሡ የፈረስ ስም ነው ይሉታል።

**ፈለገ ጥበብ** – የታች ቤት ቀለም የሚነገርባቸው አብያተ ክርስቲያናት ማንና ማን ይባላሉ?

**የኔታ ሄኖክ** – ፩. ደብረ ኃይል ወደብረ ጥበብ ፪. አደባባይ ኢየሱስ ፫. አደባባይ ተክለ ሃይማኖት።

**ፈለገ ጥበብ** – የላይ ቤትስ መሥራቾቹና አብያተ ክርስቲያናቱ?

**የኔታ ሄኖክ** – ሮሥራቾቹ አሜር እሸቱ የመጀመሪያ ሊቅ፤ ሁለተኛ በጣም ያደራጁት የኔታ ገብረ ዮሐንስ ናቸው። የላይ ቤት አብያተ ክርስቲያናቱ አቢየ እግዚእ፤ ፊት ሚካኤል፤ ገብርኤል፤ ግምጃ ቤት ማርያም ናቸው። ፍጹም ላይ ቤት የሚነገርባቸው ማለት ነው።

**ፈለገ ጥበብ** – ቅልቅል ያለባቸውስ እነማን ናቸው?

**የኔታ ሄኖክ** – ቅልቅል ያለባቸው አባጃሌ፤ ቁርቆስ፤ ፊትአቦ፤ ደብረ ምጥማቅ፤ ጐንደሮች ጊዮርጊስ፤ ጐንደሮች ማርያም ናቸው።

**ፈለገ ጥበብ** – ሳንኳስ?

**የኔታ ሄኖክ** – ሳንኳ ቁስቋም፤ መጥምቁ ዮሐንስ፤ ቀሐ ኢየሱስ፤ ልደታ ለማርያም፤ አበራ ጊዮርጊስ፤ አጣጣሚ ሚካኤል፤ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ናቸው። ሌሎችም ምንም እንኳ ሳንኳ ብለው ባይጠሩም መድኃኔዓለም፣ ደብረብርሃን ሥላሴ፣ እልፍኝ ጊዮርጊስም ቀለማቸው ሳንኳ ነው።

**ፈለገ ጥበብ** – ሩፋኤል ወዴት ነው? የሚቆጠረው?

**የኔታ ሄኖክ** – ሩፋኤልና አርባዕቱ እንስሳ ራሳቸውን ችለው ነው የሚቆጠሩ ቀደም ብለን እንደገለጽናቸው ለየት ይላሉ በቁም ማንሻ ላይ በቁም የሚል ላይ ቤት ነው። አርባዕቱ እንስሳና ሩፋኤል ወደላይ ቤት ናቸው።

**ፈለገ ጥበብ** – ከዚሁ አያይዤ የምጠይቆት ቅዱስ ያሬድ በዜማው ያልጠቀሳቸው በኋላ ሊቃውንት የተዘመሩ አሉ ለምሳሌ እንደነዚቅ የመሳሰሉ ከዚህም ከዚያም የተሰባሰቡ እና ይኸንን ያሰባሰቡ ሊቃውንት በየትኛው ዘመን አካባቢ የነበሩ ናቸው? በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ አልፎ አልፎ እንደነ «ሥላሴ ትትረመም» የመሳሰሉ አዋልድ አቡኖች ስለነዚህ ቢገልጹልኝ?

**የኔታ ሄኖክ** – አዋልድ የሚባሉ ያው ከቅዱስ ያሬድ በኋላ ሊቃውንት የፈለሰፉዋቸው ናቸው። ዚቅ ሰፋ ብሎ የመጣው ከአድያም ሰገድ ኢያሱ ጊዜ ጀምሮ ነው። ሊቃውንቱ መልኩን እያዩ ያዘጋጁት ነው።

**ፈለገ ጥበብ** – ከቅዱስ ያሬድ በኋላ የመጡ እንደ አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ እንደ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የመሳሰሉ በኋላ ዘመን የተነሱ በቅዱስ ያሬድ መዝሙር ይገለገላሉ ማን ነው ያዘጋጀላቸው?

**የኔታ ሄኖክ** – ቅዱስ ያሬድ በድምር ላለፉትም ሆነ በኋላ ለሚነሱት መንፈስ ቅዱስ በገለጸለት መሠረት የጻድቃን፤ የሰማዕታት ብሎ አስቀምጦታል።

**ፈለገ ጥበብ** – እርስዎ በአሁን ጊዜ አቋቋምን በምስክርነት የሚያስተምሩት በሀገሪቱ የምስክሩ ተጠያቂ መምህር ነዎት። ስለዚህ ማስተማር የጀመሩት መቼ ነው? የምስክርነቱ ቦታስ የያዙት እንዴት ነው? ከተጀመረ ጀምሮ እስከ አሁን ስንት ያህሉ መምህራን አስመርቀዋል?

**የኔታ ሄኖክ** – በምስክርነት ደረጃ ማስተማር የጀመርኩት በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም፤ የኔታ ክፍሌ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ነው። ያስተማርኳቸው ሊቃውንትም ቁጥራቸው ለመታወቅ የሚችለው መዝገብ ከታተመ በኋላ ነው እንጂ፤ ከዚያ ቀደም አስመስክረው የሄዱ ቁጥራቸው ብዙ ስለሆኑ ስንቱ ይታወቃል ብዙዎች ናቸው።

**ፈለገ ጥበብ** – በአሁን ደረጃ በቤተ ጉባኤ ስንት ያህል ደቀመዛሙርት ይገኛሉ?

**የኔታ ሄኖክ** – ጉባኤው ሰፊ ነው፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ በጣም እየሰፋ ነው እየሄደ ያለው፤ አሁን አድራሾቹ ብቻ ከሞቶ በላይ ናቸው፤ ሌሎችም ብዛት ያላቸው ደቀመዛሙርት አሉ።

**ፈለገ ጥበብ** – የጐንደር ቀለም ቀሐን ተሻግሮ መሄድ አይችልም የሚል አባባል አለ። (በጐንደሮች) ይህ አነጋገር እውነታው ምን ያህል ነው?

**የኔታ ሄኖክ** – ይኸ እንኳ መቼም አነጋገሩ ቢኖርም ይህ አባባል ትክክለኛ ነው ብዬ አልገምትም ባይሆን የሚሉት ቀሐን ተሻግሮ ከሌላ ሲቀላቀሉ ወዙ ስለሚመዝናቸው ነው እንጂ ቀለሙ ከዚያ ይቀራል ማለት አይደለም። ከዚያ ተስማምቶ በአንድ ድምፅ ነው የሚሉት ወጣ ካሉ ግን ከሌላ ጋር ስለሚቀላቀል የጐንደሩ ከቀሐ ወዲህ ያለው ትንሽ ሲነገር ትክክለኛ እንደ ጐንደር አይሆንም ለማለት ነው እንጂ ቃለ እግዚአብሔሩ እውነት የማይሻገር ሆኖ አይደለም።

**ፈለገ ጥበብ** – በቅርቡ «መዳልወ አልበብ» የተባለው ቋሚ መጽሐፍ አዘጋጅተው አሳትመዋል። ይህም በአቋቋም ታሪክ በምልክት ተ፡ዘጋጅቶ ሲታተም የመጀመሪያ ነው። በመሆኑም ይህንን ለመሥራት ያነሳሳዎ ምን ነበር?

**የኔታ ሄኖክ** – አዎ ተተኪው ትውልድ ብዙ ችግር እንዳይገጥመው አሁን ሁላችሁም እንደምታውቁት ሰው ሐሳቡ ብትን ነው ችኩላ አለ፤ ይኸ መጽሐፍ ከወጣ ግን ደኅና ነው፤ መጽሐፉ እየረዳቸው እነሱም ችግር አይገጥማቸውም፤ በአጭሩ ወጣቱ ትውልድ ችግር እንዳይገጥመው ነው።

**ፈለገ ጥበብ** – መጽሐፉ ከታተመ በኋላ ውጤቱ እንዴት አገኙት?

**የኔታ ሄኖክ** – ጥሩ ነው ደቀመዛሙርቱ በእሱ ብዙ ስለተጠቀሙና ስለረኩ የእነሱን ሁኔታ እያየሁ ደስ ይለኛል።

**ፈለገ ጥበብ** – ስለየኔታ ክፍሌ ዘትግራይ እና የጀነታ ክፍሌ ዘሸዋ ታሪክ ብዙ ጠልቀን የምናውቀው የለምና ስለነዚህ ስለ ሁለቱ ሊቃውንት ሰፋ አድርገው ቢያብራሩልኝ?

**የኔታ ሄኖክ** – የትግራይ ክፍሌ ዜናቸውን ነው እንጂ አላውቃቸውም አልደረስኩባቸውም፤ እኒህኛው የኔታ ክፍሌ ወልደ ጻድቅ ዘሸዋው ግን ደግ ነበሩ ማጋነን አይሁን እንጂ ሥራቸው እንደ አቡነ ተክለ ሃይማኖት (ፓትርያርክ) የሆኑ፤ ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት የማያንስ ትሩፋት የነበራቸው ናቸው። ሲያስትምሩንም ሆነ በንጽሕናቸው፤ በትሩፋታቸው፤ በዘመናቸው ከነበሩት በጣም ከፍ ብለው የሚታዩ አባት ነበሩ።

www.ethiopianorthodox.org

**ፈ**ለገ ጥበብ – የኔታ እርስዎ አሁን እየሸመገሉ ነዎት ከእርሶ በኋላ በእርስዎ ዕግር ተተክቶ እርስዎን ተክቶ የሚያስተምር ሊቅ ማነው ብለው ያምናሉ?

**የ**ኔታ ሄኖክ – ይኸ ማን እንደ ሚተካ እግዚአብሔር ነው የሚያ ውቀው እሷ እመቤታችን ገባሪተ ኃይል እሷ እንጂ እኔ ይኸ ነው የም ለው አይኖርም።

**ፈ**ለገ ጥበብ – እስከ አሁን ካስተማሩዋቸውስ፣ ትንሽ ሕሊናዎ የሚፈቅደው የለም?

**የ**ኔታ ሄኖክ – እሱማ ብዙዎች ይኖራሉ፣ ለመኖሩ አሁን እኮ ችግሩ፣ ወይም ጥያቄው የሚተካው ሰው ምን በልቶ ይቀመጣል ነው፤ ከዚያ እኮ የተማሩቱ ብዙ ሊቃውንት ናቸው። የሆነ ሆኖ ግን በችግር ምክንያት ከዚያ ስለማይቀመጥ ጉዳዩ አሳሳቢ ነው ምንም ተስፋ ስለሌለው ምን ብሎ ተተኪ ለመሆን ያስቧል? ተምሮ የሚመገበው ሲኖረው እኮ ሊተካ የሚችለው፣ አሁን ሁሉም ተምሮ ወደሚሆነው መሄድ ነው እንጂ ከዚያ የሚቀመጥ የለም።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በአሁኑ ጊዜ ብዙዎቹ የጉባኤ መምህራን ጉባኤያ ቸውን ፈትተው ወደ ከተማ ይጐርፋሉ ከዚህም ለብዙ ዓመታት ያካበ ቱት ብዙ ዕውቀት እየረሱ እገሌ መም ህር ነው ከመባል በስተቀር አያስተ ምሩም፣ በዚህ ሁኔታ እንዲህ ሆኖ በሚያዩበት ጊዜ ምን ስሜት ይሰማዎታል?

**የ**ኔታ ሄኖክ – ይኸ እንኳ ለሊቃ ውንቱ እስከ አሁን ድረስ እየነገር ናቸው ነው፣ በጣም ችግር፣ መከራ፣ ካልጸናበት በስተቀር በዚያ ጸንቶ ማስተማር እንደሚገባ ላስተማ ርናቸው ሁሉ እንነግራቸዋለን፣ ማስ ተማሩ ነው የሚጠቅም እንጂ፣ ወደከ ተማ መጉረፉ ብዙ ጥቅም እንደ ሌለውና ለታሪክም የሚበቃ ተግባር ስለሌለው በዚያ ጸንታችሁ ባላች ሁበት ሀገር አስትምሩ እያልኩኝ ነው የምመክራቸው፣ የሆነ ሆኖ በዚህ ምክር የሚጠቀሙ ጥቂቶች ናቸው። ወደዚህ ነው የሚጐርፉት ያለ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ከሕፃንነትዎ እስከ አሁን በደጉም ይሁን በመጥፎ መልኩ የገጠመዎት የሚያስታውሱት ነገር ካለ ቢነግሩን?

**የ**ኔታ ሄኖክ – ደኅና መቼም ብዙም ከፍ ያለ ደስታም ይኸ ነው የምለው ነገር የለም። በጣም ደግሞ ያገኘኝ ጉዳት የለም። በመካከል ነው የምኖር፣ ፈጣሪዬን አመሰግነዋለሁ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ታድያ በሕፃንነትዎ እያሉ ከጓደኛዎ ወይም ከሚመራዎ ተጣልተው አያውቁም?

**የ**ኔታ ሄኖክ – ጠብ ማለት እኮ ጠንከር ያለ ሲሆን ነው። የምድኝ ጠብ ጠብ ሊባል አይችልም። ከፍቅር በስተቀር እንዲህ ያለስ ገጥሞኝም አያውቅም። እኔስ ዕድሌ ደህና ነው። የሚያስቸግር ተማሪም አጋጥሞኝ አያውቅም።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ከቅዱስ ያሬድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ቅርስና ተተኪ የማይገኝለት ትምህርት ወደ ቀጣይ ትውልድ ሊተላለፍ ይችል ዘንድ ምን መደረግ አለበት ብለው ያምናሉ?

**የ**ኔታ ሄኖክ – ይኸማ እንዲቀጥል ከተፈለገ በላይ ያሉ የቤተክርስቲያን አባቶች ትኩረት ቢሰጡት? በአሁን ጊዜ እኮ ትኩረት አልሰጡትም ዝም ብሎ ነው ያለ። እስከ አሁን ድረስ እንኳ ደህና ነው ያለው። ከእንግዲህ ወዲህ ግን ወጣቱ ትውልድ ብዙ ድካምና ጥረት ስለማይፈልግ፣ ትኩረት ቢደረግበት፣ የቤተክርስቲያን አባቶች ቤተክርስቲያን እንድትገለገልበት ለተማሩ ሰዎች ደሞዝ ቢመድቡ ጉባኤው እንዲጠናከር እንደሌሎቹ መጻሕፍት ቤት ለተማሪው ሥርከ ሕብስት ቢመደብ፣ ለመምህራን እንክብካቤ ቢደረግ ላቸው እነሱን እያየ ነገም ለእኔ እንዲህ ይደረግልኛል እያለ ሙያውን ይይዘዋል።

በዚህም ትምህርቱን ለቀጣይ ትውልድ ማስተላለፍ ይቻላል። አለበለዚያ የተማረ ጠሙን እያደረ ላልተማረ ደሞዝ ቢጨማ ምሩት ትርጉም አይኖረውም።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በመጨረሻም ለመም ህራንም ለአንባብያንም በአጠቃላይ ለሕዝበ ክርስቲያኑ የሚያስተላልፉት መልእክት ምንድነው?

**የ**ኔታ ሄኖክ – ይህ ዓለም አላፊ ነውና መንፈሳዊ ሕይወታችንን ልንጠብቅ ይገባናል። «ወይ ጓጉዕ ዓለም ከመይኀልፍ» «ይህ ዓለም ለማለፍ ይቸኩላል»። እንደተባለው ኃላፊነ ታችን ተገንዝበን ሃይማኖታችንን ብናጠብቅ፣ ወዲያና ወዲህ ባንል በቤተ ክርስቲያን ተማኅጸኖአችንን ብናጠብቅ ይጠቅማል ብየ ነው የማስተላልፈው። ለመምህራንም መከራ ውን ሳትሰለቹ ጠንክራችሁ አስተምሩ ነው የምለው፣ የማሳስባቸው ይሄ ብቻ ነው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ሐሳቤን በማጠቃለል ላይ ነኝ ስለዚህ ቅኔም ያውቃሉና ከድሮ ቅኔዎት ትንሽ ቆንጠር አድርገው ቢነግሩኝ?

**የ**ኔታ ሄኖክ – የቅኔ ነገር ብዙ ለመንገር ይቻል ነበር ለአሁኑ እነሆ:-

ዋዜማ /የደብረ ታቦር፤

ዘራኤ ምሥጢር መለኮት፣
በገራጕተ ምሥጢር ታቦር ድኀረ ዘርአ ቃል ዘርአ
ዘይከል ስሂበ ዕበዩ እንሥሣ ተሐጥአ
እምእንሥሣሁ አርባዕ ዘየሐውሩ ርቱአ
ዋሕደ ላኀመ እስመ ኢያምጽአ
ወወአለ መሲሎ ጽሉአ
መወድስ (በገብርኄር ዕለት የተቀኙት)
እመ ሕሩያን መክሊትቡሩክተ አምላክ
ኢትዜከሮ በልብ ለዘረከባ ገዐር
አምጣነ ላቲ ተወልደ ዘያረሰአ ብሩር
ወረባሕ ለሰማዒሁ መክሊት ነገረ ልሳኑ
ለብሩር ማዕምር
እስመ ኢይወድቅ ዲበ ምድር
እንዘ ለጠቢባን ጥዑም ወለሐካያን መሪር
በትርሰ ወከበሮ ኢይትማሰሎ በግብር
እስመ በትር የዋሐ ልብ ኀበ ወሰድዎ የሐውር
ባሕቱ ቅሩብ ለየዋሐን ልብ አብትር
ማኅሌተ ስብሐት እግዚእ ኩሎ
ዘዲበ ኪሩቤል ይነብር። ✣

# ዘመነ ስብከት



ዘመን ማለት ረጅም ጊዜ ወይም አንድ ዓይነት አገዛዝ ሌላም የታወቀ (የጐላ) ነገር የተደረገበት ወቅት ሁሉ ዘመን ይባላል።

- ማርቆ.፩፥፲፭። ገላ.፬፥፬። ኤፌ.፪፥፯። ፩ኛጴጥ.፩፥፲፭።

ስብከት (ትንቢት) ማለትም መናገር፣ ማስረዳት፣ ማሳወቅ፣ ወደ ፊት ስለሚሆን ድርጊት በምሳሌም አለምሳሌም፣ በቃልም በድርጊትም መግለጥ ማለት ነው።

- ኢሳ፰፥፩–፯። ኤር.፲፱፥፩። ሕዝ.፬፥፩–፰።

ሁለቱም ሲናበብ ዘመነ ስብከት ወይም ዘመነ ትንቢት፣ የመናገር፣ የመገለጥ፣ የመተርጐም፣ የማስረዳት ጊዜ ወይም ወቅት ተብሎ ይተረጐማል።

ትርጉሙ እንዲህ ከሆነ ምክንያቱስ?

ስብከተ ነቢያት (ትንቢተ ነቢያት) የተነገረበት ምክንያትም እግዚአ ብሔር አምላክ የመጀመሪያዎቹን ሰዎች አዳምና ሔዋንን በንጹሕ ባህርይ ያለሞት ፈጥሮአቸው ነበር እንጂ ሞትን አልፈጠረም። «እግዚአብሔርሰ ኢገብረ ሞተ» መጽ.ጥበብ ፩፥፲፫

ይሁን እንጂ አዳምና ሔዋን የተሰጣቸውን ትእዛዝ በማፍረስ ስለበደሉ በሞተ ሥጋ ላይ ሞተ ነፍስን፣ በርደተ መቃብር ላይ ርደተ ገሐነምን ፈረደባቸው (ዘፍ.፫፥፲፩.፲፱.፳፬)።

አዳምና ሔዋን በመበደላቸው ከክብራቸው ተዋረዱ፤ ከጸጋቸው ተራቆቱ፤ ከተድላ ገነት ወጡ (ተባ ረሩ)። በራሳቸው (በሥራቸው) መከራ እንዳመጡ አውቀው በጥፋታ ቸው ተጨነቁ፤ ተጸጸቱ፤ አዘኑ፤ አለቀሱ፤ ፈጣሪያቸውን ለመኑት። ፈታሒ በጽድቅ ኵናኔ በርትዕ የሆነው እግዚአብሔርም፣ በፈታሒነቱ አን ጻር መሐሪነቱ አለና የአዳምና የሔዋን ንስሐቸውን ተቀብሎ፣ ኀዘናቸውንና ለቅሶአቸውን ተመልክቶ ሊያድ ናቸው ወደደ፤ ተስፋም ሰጣቸው። (ኢሳ.፳፫፥፳፤ ዕብ.፪፥፲፬–፲፯)

ለዚህም ነው አበው ሊቃውንት አምላክ ለገባው ቃል ሰው ለመሆኑ (ሥጋ ለመልበሱ) መሠረት የሆነው ስብከተ ነቢያት (ትንቢተ ነቢያት) ነው የሚሉት።

ምሥጢረ ሥጋዌን ለመማር በመጀመሪያ ስብከተ ነቢያትን መማር ይገባል። ምክንያቱም ጌታ ምሥጢረ ልደቱን ሳይናገር (ሳያናግር) በድንገት ሰው አልሆነም፤ ሥጋ አልለበሰምና ነው። ጌታ ሰው የሆነው፣ አስቀድሞ በነቢያት አድሮ ትንቢት አናግሮ ሱባኤ አስቆጥሮ ነው። ነቢያት በየትንቢታቸው አምላክ ከሰማየ ሰማያት ይወርዳል፣ ከድንግል ማርያም ይወለዳል በየጥቂቱ ያድጋል በ፴ ዘመኑ (ዓመቱ) በማየ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ይጠመቃል፣ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር በዓለም ላይ ዞሮ ሕገ ወንጌልን ይሠራል። ኃላፊያትን፣ መጻእያትን ለሰው እየገለጸ ትንቢት ያናግራል፣ ከዚህ በኋላ ለድኅነተ ዓለም በማዕከለ ምድር በቀራንዮ ይሰቀላል። «ወገብረ መድኃኒተ በማዕከለ ምድር» እንደተባለ ይሞታል። «ፈለግሰ ይሰጥቃ ለም ድር» እንደተባለ ከቀኝ ጐኑ ትኩስ ደም ለቍርባን፣ ጥሩ ውኃ ለጥምቀት የሚሆን ይፈሳል። በሥጋ ወደሙ ዓለ ምን ያድናል። ከዚህ በኋላ ይቀበራል። ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ ይነሣል። በተነሣ በ፵ ቀኑ መጽሐፈ ኪዳንን (ሥርዓተ ሃይማኖትን) አስተምሮ ወደ ሰማየ ሰማያት ያርጋል። በኋላም ይችን ዓለም ለማሳለፍ እና ለጻድቃን ዋጋ ለኃጥአን ፍዳ ለመክፈል ተመልሶ ይመጣል ብለዋል።

የነቢያት ትንቢት (ስብከት) የክርስቶስን ሰው መሆን (ሥጋ መልበስ) በመጽሔተ ትንቢት እያዩ ይደነቁና ይገረሙ ነበር። ነገር ግን ዓረፍተ ዘመን ገቶአቸው ከዘመኑ ሳይደርሱ መቅረታቸውን በመጥቀስ ጌታ በወንጌል «እስመ ብዙኃን ነቢያት ወጻድቃን ፈተው ይርአዩ አንትሙ ዘትሬእዩ ወኢርእዩ ወፈተው ይስምዑ አንትሙ ዘትሰምዑ ወኢሰምዑ» ያለው።

ብዙ ነቢያት በተለያየ ኅብረ አምሳል በተለያየ ኅብረ ትንቢት፣ በተለያየ መንገድ ሱባኤ በመቁጠር ትንቢት ተናግረዋል። የተናገሩትም ብዙ የብዙ ብዙ ናቸው። ከእነዚያም ውስጥ ለጊዜው ከአዳም ሰባተኛው ትውልድ የሆነው ነቢዩ ሄኖክ ስድስት ዓመት ከእግረ ገነት ወድቆ ፈጣሪውን በማገልገሉ ትንቢት ተናግሮ ሳይሞት ገነት ገብቷል። ከትንቢቱም «ወጽአ ሦር ጸዓዳ» ብሏል። ለትንቢቱም በት ውልድ ሱባኤ ቆጥሯል። ኢሳይያስም «ትወጽእ በትር እምሥርወ እሴይ ወየአርግ ጽጌ እምጕንዱ» ኢሳ.፲፩፥፩–፭ «ናሁ ይመጽእ መዋዕል ይቤ እግዚአብሔር ወይነግሥ ንጉሥ ዘይሄሊ ጽድቀ ወርትዐ» ብሏል ኤር.፳፫፥፭–፯ በተረፈ ትንቢቱም «ለሊሁ ኢየሱስ አምላክ ወልደ አምላክ ይመጽእ ውስተ ዓለም ወየኀሪ ሐዋርያተ ወይከይድ ውስተ ደብረ ዘይት ዘአነ ርኢኩ ሥግወ» ብሎ ተናግሯል። ሱባኤውንም በዕለት ቆጥሯል።

ዳንኤልም «መቅደስ ትትሐነጽ እስከ ክርስቶስ ንጉሥ» ብሏል ዳን.



www.ethiopianorthodox.org

፱፥፳፰ ሱባኤውንም በሰንበት ቆጥሯል። ዕዝራም «አንበሳ ተንሥአ እምገዳም ውእቱኬ ወልድ ውእቱ» ብሎ ተናግሯል። ሱባኤውንም በዓመት ቆጥሯል።

ነቢዩ ዳዊትም በትንቢት ከተናገራቸው ውስጥ «ናሁ ሰማዕናሁ በኤፍራታ ወረከብናሁ ውስተአመ ገዳም» ብሏል። ለዚህም ነው ቤተ ክርስቲያናችን «ዜነውነ ዜና ነቢያት ከመ ይመጽእ ወልድ በስብሐት» እያለች የምትዘምረው። ወልድ በጌትነቱ ሥጋ ለመልበስ (ሰው ለመሆን) እንደሚመጣ ነቢያት መልካሙን የምሥራች ነገሩን እንዲሁም ቅዱስ ያሬድ «ፈነወ ነቢያተ ነባቢያነ ከመ ይስብኩ ዜና ምጽአቱ ለክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር» «የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመምጣቱን ዜና ይሰብኩ ዘንድ ትንቢት የሚናገሩ ነቢያትን ላከ» ብሏል። ቅዱስ ዮሐንስም «ጺሁአ ፍኖቶ ለእግዚአብሔር ወዐሪዩ» «የእግዚአብሔርን ጐዳና ጥረጉ (አስተካክሉ)» ብሏል።

ነቢያት በአራቱ ክፍለ ዘመናት ሁሉ ትንቢት ተናግረዋል። አራቱ ክፍለ ዘመናት የሚባሉም ዘመነ አበው፣ ዘመነ መሳፍንት፣ ዘመነ ነገሥት፣ ዘመነ ካህናት ናቸው። ሲተነተኑም፣

ሀ. ዘመነ አበው ከአዳም እስከ ሙሴ ድረስ ያለው ፫ ሺህ ፰፻፵፪ ዓመት ነው።

ለ. ዘመነ መሳፍንት የሚባለው ደግሞ ከሙሴ እስከ ዳዊት ድረስ ያለው ፭፻፹፱ ዓመት ነው።

ሐ. ዘመነ ነገሥት ደግሞ ከዳዊት እስከ ዘሩባቤል ድረስ ያለው ፭፻፵፫ ዓመት ነው።

መ. ዘመነ ካህናት ከዘሩባቤል እስከ ልደተ ክርስቶስ ያለው ፭፻፰፮ ዓመት ነው።

እነዚህ በጠቅላላ ሲደመሩ ፭ ሺህ ፭፻ ዓመት ይሆናል።

በዚህ ክፍለ ዘመን ሁሉ ነቢያት ትንቢታቸውን ተናግረዋል። በአራቱ ክፍለ ዘመናት ትንቢት የተናገሩበት ምክንያትም፣

ሀ. በአራቱ ኪሩቤል ላይ የሚኖር

ለ. አራቱን መዓዝነ ዓለምን የፈጠረ አምላክ ሰው ይሆናል፣

ሐ. አራቱን ባህርያተ ሥጋ ነሥቶ ሰው ይሆናል (ሥጋ ይለብሳል) ሲሉ ነው።

ለዚህም ሁሉ በየዓመቱ ከኅዳር ፲፭ ቀን እስከ ልደተ ክርስቶስ (ታኅሣሥ ፳፱ ቀን) ድረስ የሚያዘውን በጥቅሉ ጾመ ነቢያት (ዘመነ ስብከት) ብላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትሰይመዋለች። በዚህ ውስጥ የሚገኙ ሣምንታትም የክርስቶስን ሰው መሆንና ትንቢተ ነቢያትን መነሻ በማድረግ ልዩ ልዩ ስያሜ ተሰጥቶአቸዋል።

እነሱም ስብከት፣ ብርሃን፣ ኖላዊ፣ ልደት ናቸው። ይህም ከታኅሣሥ ፯(፲፫) ቀን ጀምሮ እስከ ታኅሣሥ ፳፰ ቀን ድረስ ያለው ክፍለ ጊዜ ነው።

፩ኛ. እሑድ (ሳምንት) ስብከት ይባላል። ይህም በጠቅላላ ስለክርስቶስ ሰው መሆን (መምጣት) በኦሪተ ሙሴ በትንቢተ ነቢያት በመዝሙር አስቀድሞ ሲነገር መቆየቱን የሚያስታውስ ሳምንት ነው።

፪ኛ. እሑድ (ሳምንት) ብርሃን ይባላል። ይህም በጽልመተ ኃጢአት ተውጦ ለነበረው ዓለም፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ የዓለም ብርሃን ሆኖ እንደሚመጣ በትንቢት ተነግሮለት ለመቆየቱ ለማስታወስ የሚሰበክበት ሳምንት ነው።

፫ኛ. እሑድ (ሳምንት) ኖላዊ ይባላል። ጠባቂ አጥቶ ተበትኖና አርዌ ዓመፃ ዲያብሎስ ይበላው የነበረው የአዳም ዘርን (ምዕመንን) ለመጠበቅና ለማደን እውነተኛ ጠባቂ ሆኖ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመምጣቱ አስቀድሞ ለመነገሩ የሚታሰብበት ሳምንት ነው።

፬ኛ. እሑድ (ሳምንት) ዘመነ ልደት ጠቅላላ ሲነገር የነበረው ትንቢት ተፈጽሞ የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ በሕቱም ድንግልና ለድኅነተ ዓለም መወለዱን የሚነገር በት ሳምንት ነው።

በሌላ በኩልም ትንቢት የተናገሩት ነቢያት መታሰቢያቸው በእነዚህ ሳምንታት መሆን (መታሰብ) እንዳለበት ሊቃውንት ያስተምራሉ። ይህም ከአዳም እስከ አብርሃም የነበሩት አበው ነቢያት በስብከት። ከአብርሃም እስከ ዳዊት [illegible] በብርሃን። ከዳዊት እስከ ዘሩባቤል የነበሩት በኖላዊ። ከዘሩባቤል እስከ ልደተ ክርስቶስ የነበሩት በልደት ሳምንት ይታሰባሉ።

ነቢያት ጠቅላላ መንፈስ ቅዱስ እንደገለጸላቸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በተለያየ ስም ጠርተውታል (ሰይመውታል)። አንዱ የእግዚአብሔር ልጅ እያለ፣ ሌላው ደግሞ እውነተኛ ብርሃን፣ ቸር ጠባቂ በማለት በገለጸላቸው መጠን ጠርተውታል (መስክረዋል)።

እርሱ ራሱም ትንቢተ ነቢያትን ለመፈጸም ሰው በሆነበት ጊዜ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝም የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል (ዮሐ. ፰፥፲፪–፲፫፣ እኔ መልካም እረኛ ነኝ (ዮሐ.፲፥፲፩) በማለት እግዚአ ነቢያት ከመሆኑም በላይ ትንቢተ ነቢያትንና ስብከተ ነቢያትን ለመፈጸም እንደ መጣ ለማስረዳት የነቢያትን እውነተኛነት በቃሉ መስክሮአል፣ በግብርም አስረድቶአል።

ካብዙ በጥቂቱ ከረጅሙ በአጭሩ ዘመነ ስብከት የሚለውን ምሥጢር ይህን የሚመስል መሆኑን ከመጠቂሜም በላይ በተለይ ኢትዮጵያ አገራችን የሰው ዘር መገኛ፣ የታሪክ ማኅደር፣ የቅርስ ባለቤት መሆኗንና ለእስራኤል አገርና ሕዝብ አርአያና ምሳሌነቷንም ጭምር ነቢያት መስክረውላታል። ይኸውም «የእስራኤል ልጆች ሆይ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች (ሕዝብ) አይደላችሁምን ይላል እግዚአብሔር» በማለት ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። (አሞጽ.፱፥፯።)

ዛሬም ስለደኃራዊ ምጽአተ ክርስቶስ በነቢያትና በሐዋርያት እግር የተተኩ እውነተኞች ሰባክያን፣ መምህራን፣ ካህናት፣ ትምህርተ (ወንጌልን) ሃይማኖትን በመስበካቸው የዘመኑ ነቢያት ስለሆኑ ቃላቸው ተአማኒነት ስላለው ክርስቲያን የሆነ ሰው ሁሉ አሠረ ትምህርታቸውን ሊከተልና መሠረተ እምነቱን ሊያጸና ይገባል።

«ለሁሉም እግዚአ ነቢያት ጸጋውና በረከቱን ያድለን አሜን»

አቅራቢ ርዕሰ ደብረ መሐሪ ኃይሉ
የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት
የአስተዳደር መምሪያ ኃላፊ

# ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር

## ሁሉም መርከብ ይሥራ

ከሊቀ ሊቃውንት ያሬድ ከ[illegible]

ከጊዜው ማየ አይህ ከኤድስ ለመዳን
የሰው ልጅ በሙሉ መርከብ ይሥራ አሁን፤
በሚቀጥለው ቀን እሰራዋለሁኝ
ልደሰት ልዝናና የዛሬውን ተውኝ፤
ማለቱ ይቅርብህ ወዳጄ አትስነፍ
መርከብህን ሥራ ሕይወትህ እንዲተርፍ።
መደሰት መዝናናት ሕይወት ይዞ ጤና ሲኖር እኮ ነው
ያለ ሕይወት ደስታ ምንም ዋጋ የለው።
የዱሮዎቹ ሰዎች እንያ ሰብአ ትካት
ኖኅ መርከብ ሲሠራ ባዩት ጊዜ ድንገት፣
የምትሠራው ሥራ ምንድነው በውነት
እባክህ ንገረን ብለው ቢጠይቁት።
ኖኅም ለጥያቄው እንዲህ ሲል መለሰ
ፈጣሪ ለሰው ልጅ ክብሩን ያወረሰ
የማዘንም ነኝና ማየ አይህ በጊዜው
መርከብ ሥራ ብሎኝ እሠራለሁ ይኸው።
እኔና ልጆቼ ሌሎቹም ፍጥረታት
ከጥፋቱ ውኃ የምንድንበት።
ይህን መልስ ሰምተው እንያ ሰብአ ትካት
አሾፉ ቀለዱ ኖኅን እንዲህ አሉት።
አንተ ብቻህን ነህ የሚረዳህ የለም
ከልጆችህ ጋራ በል ሥራ በል ድከም፤
እኛ ግን ብዞች ነን ሥራውን ስናየው
ነገን እንሠራዋለን ያንድ ቀን ሥራ ነው።
እንብላ እንጠጣ እንጨፍር እንዝለል
ተድላ ደስታ እናድርግ፤ ሰው የፈለገውን ይበል።
ማየ አይህ የሚባለው ቢመጣም ባይምጣም
ዘመኑ ገና ነው በወሬ አንፈታም።
እንደሰት ብቻ ባገኘነው ጊዜ
አለምንም ሐሳብ አላንዳች ትካዜ።
እንደዚህ እያለ ሰይጣን ሲያሞኛቸው
አላስተውል ብሎ ደንዳናው ልባቸው፤
መርከቡን ሳይሠሩ እንደምኞታቸው
የጥፋቱ ውሃ ድንገት መጣባቸው።
ሲበሉ ሲጠጡ ሲያገቡ ሲጋቡ
ሲተከሉ ሲነቅሉ ሲያፈርሱ ሲገነቡ፤
በፈጣሪያቸው ቃል ሲያፌዙ ሲያሾፉ
አፍሶ ጠራርጎ ወሰዳቸው ጐርፉ።
እያሳሳቀ ነው ጐርፍ ሲወስድ ጥንቱ
የተባለው ለካ ለዚህ ነው ተረቱ።
እሺ በጀ ብሎ መርከቡን የሠራ
ኖኅ ከነ ልጆቹ ዳነ ከመከራ።
አንሰማም ያሉት ግን መርከቡን ያልሠሩ
ከገጸ ምድር ጠፉ ከንቱ ሁነው ቀሩ።
ዛሬም በጊዜያችን መድኃኒት የሌለው
ማየ አይህ መጥትዋል ኤድስ የተባለው።
እንደንፍሮ አንፍሮ ቀቅሎ እንደ ቅጠል
ሺ ጊዜ አሰቃይቶ ሺ ጊዜ የሚገድል።
የቀድሞ ማየ አይህ በታሪክ ያየነው
አርባ ቀን ነበረ ሊዘንም የቻለው።
የዛሬ ማየ አይህ ምሕረት የለሽ ኤድስ
መቼ አባራና ሰውን ከመደምሰስ።
ታዲያ ለዚህ ነገር ምን ይበጃል ቢሉ
መርከብ መሥራት ነዋ ሳያድሩ ሳይውሉ።
ምን ዓይነት መርከብ ነው ከኤድስ የሚያድን?
ብለህ ብትጠይቅ ወጣት የኔ ወገን፤
አንድ ላንድ ጋብቻ በዕኑእ ቃል ኪዳን።



www.ethiopianorthodox.org

ይኸው ነው መርከቡ ፍቱን መድኃኒቱ
ሊሠራው የሚችል ወጣት አዛውንቱ።
መርከቡን ለመሥራት ቀጠሮ አናብዛ
የሕይወት ጉዳይ ነው አንየው በዋዛ።
ተው ተመለስ ሲሉት እንስሳ እንኳ ሰምቶ
ይመለስ የለም ወይ ያሰበውን ትቶ።
የሰው ልጅ ካሰበ፣ ባለው ቀና መንፈስ
ዓለም ከሚፈራው ከመቅሰፍት ኤድስ፣
ስጋውን ለማዳን ነፍሱን ለመቀደስ
በቅድሚያ ዝሙትን፣ ያስወግድ ይደምስስ።
የበሽታዎች ምንጭ ዝሙት በመሆኑ
አስቀድመው ምንጩን ጠቢባን ይድፈኑ።
እኔስ የሚገርመኝ ሁል ጊዜ ሳስበው
ዝሙት የሕይወት ጠንቅ ፍቅር መባሉ ነው።
ዝሙትና ስካር እየተጋገዙ
በዓለም በቃኝ ወሆኒ ስንቱን ሰው አጋዙ!
በእሳት ነበልባል ቢጋመ በጋለ
ጎመራ ነደደ ሰዶም ተቃጠለ፣
በዝሙት እኮ ነው በሌላም አይደለ
ዝሙት አያመጣው ምንም ጣጣ የለ።
ንጉሡ ሰሎሞን ብልሁ አስተዋዩ
ብዙ ሴቶች ወዶ ጠማዊ ባሕርዩ።
የማይከፈለው የእስራኤል መንግሥት
ከሁለት ተከፍሎዋል በዝሙት ምክንያት።
ያለፈውን ታሪክ ከዚህ እንግታና
ዛሬስ እንዳይሰፍኑ ሰላምና ጤና።
የሚያተራምሰው ዓለምን በዋይዋይ
የዝሙት ተወላጅ ኤድስ አይደለም ወይ?
ሰው ነፍሱን አርክሶ እንስሳትን መስሎ
በስልጣኔ ሰበብ ምን አለበት ብሎ
ዝሙትን ሲፈጽም በየዋለበቱ
ምንም አያስገርምም ኤድስ መስፋፋቱ።
ፍትወት የደቀለው የሴሰኞች ግኝት

ይኸው ኤድስ ሆነ ምሕረት የለሽ መቅሰፍት።
ኤድስ አያማርጥ ኤድስ አያዳላ
አንዳፍታ አዳረሰው ዓለምን በመላ
እንደ ሰደድ እሳት ሁሉንም እየበላ።
ላወቀበት ሰው ግን አንድ አመል አለው
ሳይነኩት አይነካም ከነኩት እሳት ነው።
ስለዚህ ወገኔ አስተውል ተገንዘብ
እሱን እንዳትነካ ወደሱም አትቅረብ።
ሐኪሙ ዶክተሩ ስፔሻል ቢባሉ
ካልተጠነቀቁ አያመልጡም አሉ።
ምንም እንኳን ኤድስ ሁሉን ቢያዋርድ
ደጋግሞ ያጠቃል ወጣቱን ትውልድ።
ስለሚነካካው በአጉል ድፍረቱ
ጀብደኛው ዘመናይ ትኩስ ኃይል ወጣቱ፣
እጅግ ያሳዝናል ወጣት በእውነቱ
ልስራ ልስራ እያለ ጠንካራው ጉልበቱ፣
እሳት እሳት ሲሸት ትኩሱ እውቀቱ
የኤድስ ቀለብ ሁኖ ብላሽ በመቅረቱ።
ወገኑን ሊጠቅም አገሩን ሊያለማ
ተነስቷል ሲባል በኤድስ ተቀማ።
ወጣቱ ወንድሜ በል ስማኝ ልንገርህ
ከዚህ ከዚያ ማለት መቅብጥበጥ ይቅርብህ፣
እሷ ስለሆነች ታማኝ መድኃኒትህ
ባንዲትዋ ተወስን እስከ ጊዜ ሞትህ።
ወጣትዋ እህቴ ስሚኝ ልንገርሽ
ከዚህ ከዚያ ማለት መቅበጥበጥ ይቅርብሽ፣
እሱ ስለሆነ ፍቱን መድኃኒትሽ
ባንድ ተወሰኝ እስከ ጊዜ ሞትሽ።
አምላክ የፈቀደው ቅዱስ ጋብቻ
በሃይማኖት ጸንቶ አንድ ላንድ ብቻ።
አንዲት እናት ሔዋን ላንድ አዳም መፍጠሩ
ማለቱ እኮ ነበር አንድ ላንድ ኑሩ።

ጥንድ ሴት መያዝ ጥንድ በሬ ሳትይዝ፣
በሽታን ችግርን በራስህ መጋበዝ
መሆኑን እወቀው ፍጹም አትሁን ግብዝ።
አንተስ ከተሜው ተምሬአለሁ እያልህ
ደክመህ ባመጣኸው በገዛ ገንዘብህ፣
በሽታን ስትሸምት ሕይወትህን ሸጠህ
ኑሮህን ስትገፋ የሱስ ተገዥ ሁነህ
አይሰማህም ወይ አረ ተው ይሰማህ።
ካስነዋሪ ድርጊት ምሑራን ካልራቁ
ለወሬ ነው እንጂ መማሩ ማወቁ።
ምሑሩ አዋቂው አውቃለሁ እያለ
አጥር እየጣሰ ቅጥር እየዘለለ፣
በመጣው በሽታ ራሱን ከገደለ
የትምህርት ጥቅሙ እኮ ከምንዋለ?
ተምሬአለሁ ባዩ ከሆነ ጥቅም አልባ
አውቄአለሁ ባዩ ከሆነ ሕግ አልባ፣
እንዲህ ያለው ትምህርት ወድያ ገደል ይግባ
ለምንም ማንንም አይረባ።
ከገባበት ገብቶ ከኤድስ ጋር ፍጥጫ
ሕይወትን ለማጥፋት የሚደረግ ሩጫ።
እያነፈነፈ ዘማን የሚከተል
ለእርድ የሚነዳ ፍሪዳን ይመስል።
ኤድስ ብለው ሊቃውንት ሲመክሩ
ሰውን እንደ ቅጠል ሲያረግፍ በየ አገሩ።
እያዩ እየሰሙ የለም ብሎ ማውራት
ማንን ለመጉዳት ነው? ማንንስ ለማጥፋት።
ራስን ቤተሰብን አልፎም ወገንን በሙሉ፣
መጉዳት እንደሆነ ያሻል ማስተዋሉ።
ልባችን አይፅና ድንጋይ አናድርገው
እሺ ብለን ምክሩን ሥራ ላይ እናውለው።
አገር እንድትለማ እንዲወገድ ችግር
በሰላም በጤና ሕዝባችን እንዲኖር
ጓዙን ዝክትሉን አንዳችም ሳያስቀር

ጠቅልሎ ያውጣልን ከሀገር ይባረር
አገር ወራሪው ኤድስ የአዳም ልጆች ፀር።
በዚሁ እንስማማ አንድ ይሁን ምክራችን
ኤድስን ለማስወጣት ከኢትዮጵያ አገራችን።
የሁላችን ጤና አስተማማኝ ሁኖ
ኤድስ ጭራሽ ጠፍቶ እልም ብሎ በኖ
መቅሰፍት ተወግዶ ባገር ምሕረት ሰፍኖ
ለማየት እንድንችል ያለ አንዳች ተፅዕኖ።
ወጣቶች ጐልማሶች አድምጡኝ እባካችሁ
ሕገወጥ ጋብቻ ዝሙትን ትታችሁ፣
በዕውቀት እደጉ ይጠበቅ ጤናችሁ
ብቁ ዜጋ ሁኑ ለእናት አገራችሁ።
ለትምህርት ለልማት ላገር ብልፅግና
በቅድሚያ ወሳኝ ጤንነት ነውና።
እንግዲያውስ ይጥፋ ከሥር ይነቀሉ
የጤናችን ጠንቆች በሽታዎች ሁሉ።
መድኃኒቱ ይኸው ተነግሯል ተደጋግሞ
አንድ ለአንድ ጽኑ አይኑር ተቃውሞ።
ካስሩ ትእዛዛት ሙሴ ከጻፋቸው
ስድስተኛው ትእዛዝ አትሴስን የሚል ነው።
ስለዚህ ቤተክርስቲያን አትስስኑ እያለች
ለብዙ ዓመታት በአዋጅ ሰብካለች።
አዋጅዋን ስብከትዋን ሰው ቢሰማ ኖሮ
መድኃኒት የለሽ ኤድስ ባልኖረ ዘንድሮ።
የዝሙት መዘዙ መቅሰፍቱ ሲነገር
ይመስለን ነበር በነፍስ ብቻ የሚቀር።
መቼ በነፍስ ብቻ ያልፍና መዓቱ
መግዘፉም ስጋ ባሰ እንጂ መቅሰፍቱ።
እንዲህ ስለሆነ ጉዳዩ ችግሩ
መምህሩ ተማሪው መሪው ወታደሩ፣
ገበሬው ነጋዴው አናጺ ሹፌሩ
ሁሉም በያለበት ተረድቶት ነገሩ።
ከቤተክርስቲያን ጋር ባንድ ልብ ባንድ ቃል
አንድ ለአንድ እያለ ስብከቱን ይቀጥል።
እኛም ጠንቀቅ እንበል አንድ ለአንድ እንጽና
አስተማማኝ ፈውስ ይህ ብቻ ነውና።
ሁሉም ቻይ ፈጣሪ ርኅሩኅ ጌታችን
በሽታውን ሰዶ ጤናውን ያምጣልን።
ለመኖር እንድንችል አንድ ለአንድ ጸንተን
በልባችን ያድስ የቀና መንፈሱን። ✣



www.ethiopianorthodox.org

# ትምህርተ ኖሎት

ከሊቀ ጉባኤ ዕድ ክፍለ ዮሐንስ መኩንን



በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ «አቀድም አእኩቶቶ ለእግዚ አብሔር» ከሁሉ አስቀድሞ መዓልቱን በሌሊት፤ ሌሊቱን በመዓልት፤ ክረምቱን በበጋ፤ በጋውን በክረምት እያፈራረቀ ፍጥረቱን ሁሉ ለሚመግበው ለቸሩ አምላክ ለእግ ዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው አሜን።

ይህ ትምህርት የተዘጋጀው ኖት በተባለው ርዕስ ነው። ትምህርተ ኖሎት ማለትም በዚህ ዓለም ያሉትን በጐች ለሚጠብቁ እረኞች ሥጋዊ ጥረትና ትጋት እንደሚያስፈልጋቸው ሁሉ የእግዚአብሔር በጐች ምዕመናንን መክረው፤ አስተምረው ለሚጠብቁ ሰባክያነ ወንጌል መምህራንም የበለጠ መንፈሳዊ ጥረት እንደሚያስፈልጋቸው የሚያስረዳ በምሳሌ ላይ የተመሠረተ አምላካዊ ትምህርት ነው።

አብዛኞቹ ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉትም በዚህ መልክ መሆኑ ለሁሉም ግልጽ ሆኖ ይታያል፤ ስለሆነም ዓለምን ለማዳን ሰው የሆነው አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕዝቡንም ሆነ አሕዛቡን በሚያስተምርበት ጊዜ ያለ ምሳሌ እንዳላስተማራቸው ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል። ጥቅስ የ(ማቴዎስ ወንጌል ምዕ.፲፫ ከቁ.፴፭) ይሁን እንጂ በምሳሌነት ለተጠቀሱት በጐችም ሆነ ምሳሌው ለተጠቀሰላቸው ምዕመናን የምን ጊዜም ጠባቂያቸው ስለ ዓለም ቤዛ ሕይወቱን ለሞት አሳልፎ የሰጠው ቸር ጠባቂ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ በጐች አጠባበቅ ሲያስተምር በጐቹ ወደ ማደሪያቸው በሚገቡበት ጊዜም ሆነ በሚወጡበት ጊዜ እንዲሁም በሚሰማሩበት ጊዜ ለበጐች ጥበቃ የተመደበው ማንኛውም እረኛ በበጐቹ ላይ የሚነሳባቸውን ነጣቂ ተኩላ መከላከል እንዲችል ምን ጊዜም ቢሆን በበጐቹ ፊት ለፊት መሄድ እንዳለበትና ሕይወቱንም ስለ በጐቹ ቤዛ አሳልፎ እስከመስጠት ድረስ ታማኝነት ያለው ጠባቂ ሆኖ መገኘት እንዳለበት አምላካዊ መመሪያ ሰጥቷል።

በጐቹን ለጥፋት የሚሹ ወንበዴዎች እንዲሁም የበጐቹን ለምድ በመልበስ ተመሳስለው የሚመጡ፤ ለንጥቂያ የሚያደቡ ተኩላዎች መኖራቸውንም አስረድቷል። ስለሆንም ኄርናዊ ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚህ በጐች ከወንበዴዎች እጅም ሆነ ከተኩላዎች አፍ መዳን እንዲችሉ ጠባቂዎቻቸው የሚያስጧቸውን የሕይወት ድምፅ ከተኩላዎችና ከወንበዴዎች ድምፅ ለይተው ለመስማት እና ሕይወት በሚገኝበት መንገድ የሚመሯቸውን ጠባቂዎች ያለ አንዳች ምክንያት ለመከተል ፈቃደኞች መሆን እንዳለባቸው የሚያስገነዝብ ትምህርት በተከታታይ አስተምሯል። ጥቅስ የ(ዮሐንስ ወንጌል ምዕ.፲ ከቁ.፩–፲፯) ይህም ትምህርት ከፍ ብሎ በመሠረተ ሐሣቡ ላይ እንደተገለጸው ሁሉ ከምሳሌ ጋር የተዛመደ ስዕላዊ ትምህርት መሆኑ ከሁላችንም የተሰወረ አይደለም።

ይሁን እንጂ የቃሉ ባለቤት አንቀጸ አባግዕ ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን በመስቀል ላይ ሕይወቱን እንደሰጠ ሲያስረዳ ቸር ጠባቂ እኔ ነኝ በማለት አሻሚ በሌለው አምላካዊ ቃሉ አስተምሮናል።

ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል የሕይወታችንን መንገድ የምናይበት ዘለዓለማዊ ብርሃን መሆኑን አውቀን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እያንጻንጻችን ክርስቲያናዊ ግዴታችንን መወጣት እንድንችል ሕይወታችንን መመርመር ይኖርብናል።

ከዚህም ጋር በወንበዴዎችና በተኩላዎች ምሳሌነት የተገለጹት አጋንንት እንዲሁም መናፍቃን አንድነታችንን ለመፈታ[illegible] የባዘነውን ካገኙ ለመንጠቅ የሚያስችላቸውን መንገድ እየፈለጉ በፊት በኋላ በቀኝ በግራ እየተወራጩ ያሉበት ጊዜ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። እውነተኛው ቸር ጠባቂ ሊቀ ኖሎት ኢየሱስ ክርስቶስ ከበጐች መካከል ተለይቶ የባዘነውን አንድ በግ ማለትም ከዘጠና ዘጠኙ ነገደ መላእክት ተለይቶ ጠፍቶ የነበረውን አንድ አዳምን ለመፈለግ መለኮታዊ ባሕርይን ከሰው ባሕርይ ጋር አዋሕዶ ያለ ዘር ከድንግል ማርያም ተወልዶ በየጥቂቱ ካደገ በኋላ መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ቀራንዮ የተጓዘውን ጉዞ፤ እንዲሁም የተቀበለውን የመከራ ፅዋትው፤ ጠፍቶ የነበረውን በግ አዳምን ካገኘውም በኋላ የተደሰተውን መንፈሳዊ ደስታ እስከ መጨረሻይቱ ሕቅታችን ድረስ እያስታወስን መኖር አለብን። ጥቅስ የ(ሉቃስ ወንጌል ምዕ ፲፭ ከቁ.፬–፰) እንደ ዚሁም ሁሉ በየምክንያቱ ከማኅበረ ምዕመናን ተለይተው የጠፉትን ወገኖች ወደ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖታቸው መመለስ እንድንችል ከምን ጊዜውም ይልቅ የበለጠ ሃይማኖታችን የፀና ክርስቲያናዊ ምግባራችን የቀና መሆን እንዳለበት ነው።

እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ሰባክያነ ወንጌል መምህራን በዕድሜ፤ በጾታ ልዩነት ሳያደርጉ ምዕመናንን በመንፈሳዊ ሕይወት ተንከባክበው መጠበቅ እንዳለባቸው የፍቅር ጥያቄ አቅርቧል። ይህም አምላካዊ ጥያቄ የሚያስተምረን እያንዳንዱ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰባኪ ወንጌል መምህር እግዚአብሔርን የሚወድ ለመሆኑ በሚጠየቅበት ጊዜ አዎን እወደዋለሁ በማለት የቃል መልስ መስጠት ብቻ ሳይሆን ምዕመናንን መክሮ አስተምሮ በኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖት በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር መጠበቅ እንዲችል፤ ብሎም የምዕመናንን ሕይወት ከጥፋት ለማዳን መስቀሉን እስከ መሸከም ድረስ ለቤዛነት መዘጋጀት እንዲችል ነው። ጥቅስ የ(ዮሐንስ ወንጌል ምዕ ፳፩ ከቁ.፲፭–፲፱)።

ከዚህም ጋር ወደ አለፉት ዘመናት ተመልሰን ያጠባበቁን ሂደት የተመለከትን እንደሆነ ቸሩ አምላክ እግዚአብሔር የሚወዳቸው በጐች ምዕመናንን ምን ጊዜም ቢሆን ያለ ጠባቂ የተወበት ጊዜ እንዳልነበረ ነው። ስለሆነም በጐቹን እንዲጠብቁ ከመረጣቸው አበው አንድን ያዕቆብን ስንመለከት ያዕቆብ [illegible] ተኩላ እንዳይበላበት በትጋት መጠበቅ ብቻ ሳይሆን በተጨማሪ የበጐቹ መልክ ዥንጉርጉር ሽመልመላ ሆኖ እንዲያምርለት ልብን፤ ለውዝ ከሚባል ዛፍ የቆረጣትን ብትር ሽመልመላ መልክ እንዲኖራት በማድረግ በጐቹን ውኃ በሚያጠጣበት ጊዜ ያችን ብትር እያዩ እንዲጠጡ በውኃው ውስጥ ያዩትን በትር በማስመሰል ሽመልመላ የሆኑ ዥንጉርጉር መልክ ያላቸው የሚያምሩ ግልገሎችን እንዲወልዱለት በየጊዜው ሰፊ ጥረት ያደርግ እንደ ነበረ ነው።

ስለሆንም የዕቆብ በተጓዘበት ጉዞም ሆነ በሠራው ሥራ ሁሉ የእግዚአብሔር በረከት ያልተለየው ቅዱስ ሰው እንደ ነበረ ቅዱሳት መጽሐፍት ሁሉ ይመሰክሩለታል። የያዕቆብ ጥበቃ በእንስሳት ሕይወት ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን ቤተሰቦቹ ማለትም አሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ከአምልኮተ እግዚአብሔር ወደ አምልኮተ ጣዖት፤ ገቢረ ጽድቅ ወደ ገብረ ኃጢአት ሳይለወጡ «ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አብርሃም ወአምላከ ይስሐቅ ወአምላከ ያዕቆብ» እያሉ ዘወትር ከመጸለይ ጋር በሃይማኖታቸው ጸንተው እንዲኖሩ መክሮ አስተምሮ ይጠብቃቸው እንደ ነበረ ነው። ጥቅስ (ዘፍጥረት ምዕ ፴ ከቁ. ፴፯–፵፩) እንደ ዚህም ሁሉ በምስጢረ ጥምቀት አማካይነት ከአብራክ ሥላሴ የተወለዱ ምዕመናንን በኢየሱስ ክርስቶስ በከበረ ደሙ ፈሳሽነት በተቀደሰው መስቀል ሥር ተሰልፈው፤ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ጸንተው በቅድስት ድንግል ማርያም ቃል ኪዳን አምነው፤ በንስሐ ታድሰው፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ተቀብለው፤ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ በመሆን መንፈሳዊ ሕይወታቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ያማረ የተወደደ ሆኖ እንዲገኝ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰባክያነ ወንጌል ሆነው የተመደቡ መምህራን ሁሉ ደክመን፤ ሰለቸን ሳይሉ ለበጐቹ ሕይወት ይህን ያህል እንክብካቤ ያደርግ ከነበረው ከያዕቆብ ይልቅ «ረዓይከ አባግዕየ» የተባሉ ምዕመናንን በስብከተ ወንጌል ለማገልገል የበለጠ ጥረት ማድረግ እንደ ሚጠበቅባቸው ነው። ወደ ምሳሌውም ዘወር ብለን ትንታኔውን ስንመለከት ያዕቆብ የቀሳውስት፤ በትረ ያዕቆብ የመንፈስ ቅዱስ፤ መስቀል የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ነው ውኃው የጥምቀት፤ በጐቹ የጥሙቃን ምዕመናን፤ ሽመልመሌ የሆኑ ግልገሎችን በውኃው ውስጥ ያዩትን በትር አስመስለው መውለዳቸው ጥሙቃን ምዕመናንን በጥምቀት አማካኝነት ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ለመወለዳቸውና «ገጸሙሴ ለፃድቃን ምስብዒተ ይበርህ እምፀሐይ» እንደተባለው ሁሉ ትንሣኤ ሙታን በሚደረግበት ጊዜ ከፀሐይ ይልቅ ሰባት እጅ አብርተው አምረው፤ ደምቀው ለመነሳታቸው ምሳሌ ነው።

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት መምህራን ሰባክያነ ወንጌልም ከሁሉ አስቀድሞ ሊገነዘቡት የሚገባቸው አቢይ ቁም ነገር በስብከተ ወንጌል የምዕመናንን ሕይወት መጠበቅ ሲባል እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሁሉ ስለ ምዕመናንን ሕይወት ቤዛ ከመሆን ተለይቶ የማይታይ ሐዋርያዊ ተልዕኮ መሆኑን ነው። ጥቅስ (መጽሐፈ ሳሙኤል ካለዕ ምዕ ፳፬ ከቁ ፲፯።) ስለዚህም የእግዚአብሔር በጐች ምዕመናንን መክረው፤ አስተምረው መጠበቅ ሲገባቸው በምን ቸገረኝነት ችላ የሚሉትን ሐሰተኞች መምህራን ካህናተ ጣዖትን ነቢያተ ሐሰትን መምህራን አስመልክቶ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል «በጐቼን በትናችኋል፤ አባራችኋቸዋል፤ አልጐበኛችኋቸውም፤ እንሆ የሥራችሁን ክፋት እጐበኝባችኋለሁ፤ የመንጋዎቼም ቅሬታ ከተባረሩበት ምድር ሰብስቤ ወደ በረታቸው እመልሳቸዋለሁ። እነሱም ያፈራሉ ይበዙማል፤ የሚጠብቋቸውንም እረኞች አስነሳላቸዋለሁ፤ ዳግመኛም አይፈሩም እና አይደነግጡም። ከእነሱም አንድ እንኳ አይጐድልም»። ጥቅስ (ትንቢተ ኤርምያስ ምዕ ፳፫ ከቁ ፪–፭።) ዳግመኛም የበጐች ባለቤት የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ስለ ምዕመናን ሕይወት ደንታ የሌላቸውን መምህራን በሚዘልፍበት አንቀጽ እንዲህ ብሏል። የደከመውን አላጸናችሁትም፤ የታመመውንም አላከማችሁትም፤ የተሰበረውንም አልጠገናችሁትም፤ የባዘነውንም አልፈለጋችሁትም፤ የጠፋውንም አልፈለጋችሁትም፤ በጐቼ እረኛ በማጣት ተበተኑ፤ ለምድር አራዊት ሁሉ መብል ሆኑ፤ በጐቼ በተራሮች ሁሉና በረዘሙ ኮረብቶች ሁሉ ላይ ተቅበዘበዙ፤ የሚሻቸው የሚፈልጋቸውም አልነበረም። ጥቅስ (ትንቢተ ሕዝቅኤል ምዕ ፴፬ ከቁ ፫–፯)።

ከዚህም በመቀጠል እረኞቹ ችላ ከማለታቸውም የተነሳ በበጐቹ ላይ የደረሰባቸውን ችግር ሁሉ እንደሚያስወግድላቸው በዚሁ ምዕራፍ እንዲህ ብሏል። «እንሆ እራሴ በጐቼን እሻለሁ፤ እፈልጋቸዋለሁም፤ እረኛ በተበተኑት በጐች መካከል ባለ ጊዜ መንጋውን እንዲፈልግ፤ እንዲሁ በጐቼን እፈልጋለሁ፤ በደመናና በጨለማ ቀን በተበተኑበት ስፍራ ሁሉ አድናቸዋለሁ። ከአሕዛብም ዘንድ አወጣቸዋለሁ ከእየአገሩም እሰበስባቸዋለሁ። ወደ ገዛ አገራቸውም እመጣቸዋለሁ። በፈሳሾችም አጠገብ በምድርም ላይ ሰዎች በሚኖሩበት ስፍራ ሁሉ አሰማራቸዋለሁ፤ እኔ እራሴ በጐቼን አስመስጋቸዋለሁ። የጠፋውንም እፈልጋለሁ፤ የባዘነውንም እመልሳለሁ፤ የተሰበረውንም እጠግናለሁ፤ የደከመውንም አፀናለሁ፤ በፍርድም እጠብቃቸዋለሁ»። ጥቅስ (ትንቢተ ሕዝቅኤል ምዕ ፴፬ ከቁ ፲፩–፲፯)።

ስለሆንም ኃያሉ እግዚአብሔር ከመጀመሪያው እስከዚህ በተነገረው በቅዱስ ቃሉ የሚያስገነዝበው በመምህራንና በምዕመናን ሕይወት መካከል ባለው መንፈሳዊ አጠባበቅ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ከዚህ ባልተለየ መልኩ ማንኛውም ሰው የሌላውን ሰው ሕይወት በታማኝነት እንዲጠብቅ ከእግዚአብሔር የተሰጠው አምላካዊ አደራ መሆኑን ማወቅ እንዲችልና አንዱ ስለሌላው ሕይወት ቤዛ ሆኖ መገኘት የክርስትና ግዴታ መሆኑን አውቆ ተዘጋጅቶ መኖር እንዲችል ነው።

በአጠቃላይ ወላጆች ልጆቻቸውን፤ ልጆች ወላጆቻቸውን፤ መሪዎች ሕዝቦቻቸውን፤ ሕዝቦች መሪዎቻቸውን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በመንፈሳዊ ሕይወት በሰላምና በፍቅር መጠበቅ መቻል እንዳለባቸው ያስገነዝባል።

ይህ ሁሉ ሳይደረግ ቢቀር ግን የበጐች ባለቤት እግዚአብሔር በአመፀኞች እረኞች ላይ በትረ መዓቱን እንደሚያነሳ፤ የባዘኑትን፤ የትም የተበተኑትን በጐቹን በረድኤቱ እንደሚሰበስባቸው አስቀድሞ ተናግሯል። ስለዚህ ማንኛውም ሰው በሰራው ኃጢአት ምክንያት ኃያሉ እግዚአብሔር ከሚያመጣበት በትረ መዐት መዳን እንዲችል የሌላውን ሕይወት እንደ ራሱ ሕይወት አድርጐ ለመጠበቅ እግዚአብሔርን ከመፍራት ጋር እንደ እባብ ብልህ እንደ እርግብም የዋኅ ሆኖ መገኘት ይኖርበታል። ✣

www.ethiopianorthodox.org

# ለወጣቱ ለወጣቱ

## የእግዚአብሔር ስጦታ ከማንም ጋር ልናወዳድረው አንችልም

የብዕር ቅኝት በመምህር ዕንቈ ባሕርይ ተከሥተ

ዕለቱ መስከረም ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ከረፋዱ ፭:፴ ላይ መንበረ ፓትርካናው በልዩ ልዩ ኅብረ ቀለም አሸብርቋል። ባንዲራችን ከፍ ብሎ ይውለበለባል። የሰንበት ትምህርት ቤቶች መዘምራን ጣዕመ ዝማሬያ ቸውን ያወርዱታል። በመንገድ የሚያ ልፈው ሰውም ሥራውን ትቶ በመ ንገድ ተኰልኵለዋል።

ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ከቅዱስ አባታችን ጋር ከበሩ ወጥተው ቆመ ዋል። በሰው ፊት ሁሉ የሚታየውና የሚነበበው፣ ደስታ፣ ሣቅ ነው። አንዳ ንዱ ዛሬ በቤተክህነት ምን በዓል አለ? ብሎ የተገረመም ነበር። ሰዓቱ ደርሷል ልክ ፭:፴ ላይ በዚህን ጊዜ እነዚያ ብር ቅየ ውድ አትሌቶቻችን ብቅ አሉ። መዝሙሩ፣ ደስታው እልልታው አስተጋባ።

በርግጥም ጀግኖች አትሌቶቻችን ከባሕር ማዶ ሂደው ድል አድርገው ባንዲራችንን በተደጋጋሚ ከፍ ብላ እንድትውለበለብ አድርገዋልና እል ልታው ደስታው ይገባል። ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም ልጆችዋ በድል ስለተመለሱ የእናትነትዋን በረከት ልትሰጣቸው ነበር የጠራቻቸው። በዚህ ጊዜ የተገኙ አትሌቶቻችን:-

ጀግናው አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገብረ ሥላሴ

ጀግናዋ አትሌት ሻሊቃ ደራርቱ ቱሉ
ጀግናው አትሌት ሚልዮን ወልዴ
ጀግናው አትሌት ገዛኸኝ አበራ
ጀግናዋ አትሌት ሻምበል ጌጤ ዋሚ
ጀግናው አትሌት አሰፋ መዝገቡ

ጀግናው አትሌት ተስፋዬ ቶላ ሲሆኑ ሌሎችም፣ አሰልጣኞች፣ ጋዜ ጠኞች፣ ተገኝተዋል።

እኛም በዛሬ ዝግጅታችን ጀግናው ሻለቃ ኃይሌ ገ/ሥላሴና ጀግናዋ




ሻለቃ ደራርቱ ቱሉ ከሰጡት ገለጻ ላይ ባጭሩ ልናቀርብላችሁ ወደድን።

ክቡር ሻለቃ ኃይሌ ገብረ ሥላሴ አትሌቶችን ወክሎ ያደረገው ንግግር።

ቅዱስ አባታችን በቅድሚያ እኔ ከፍተኛ ምስጋና እንዳቀርብ ይፈቀ ድልኝ። በእውነቱ ዛሬ ቅዱስነትዎ በመግቢያ ንግግሮዎ ላይ «እኛ እንደ ቤተ መንግሥቱ ባይሆንም» ብለው ነበር።

እኔ ግን እንደኔ የምለውን ነው መናገር የምፈልገው፣ ከዚህ የበለጠ ስጦታ መመኘት በእውነት የተሳሳተ አመለካከት ነው የምለው። ለምን ቢባል ሁላችንም በምድር ላይ እንኖራለን። ሁሉም ነገር በምድር ላይ ይኖራል። ሁሉም በዚህ ምድር ነው የሚከናወነው። ከምድር ላይ ስናልፍ ግን ይዘነው የምንሄደው ነገር ይኸን ስጦታ ብቻ ነው። (መጽሐፍ ቅዱስን እያሳየ) የዚህን ዓለም ኮንትራት ጨርሰን ወደ እግዚአብሔር መንግ ሥት የምንገባበት ስለሆነ ወደዚያ የሚያመራን ይኸው ስለሆነ ትልቁን የእግዚአብሔር ጸጋ የእግዚአብሔር ስጦታ ከማንም ጋር ልናወዳድረው አንችልም። የእግዚአብሔር ጸጋ የእግዚአብሔር ነው የምንለው እንጂ ዋጋ አይተመንበትም ይኸ ነው ብሎ አይገመትም። ስጦታው፣ የሕይወት መመሪያ ከስጦታዎች በላይ ስጦታ ነውና በጣም በጣም አድርጌ በእኔና በአትሌቶች ቡድን እንዲሁም በቡድኑ ስም ከፍተኛ ምስጋናዩን አቀርባለሁ። ለቅዱስነትዎ ጤናና ዕድሜ ይስጥልን አመሰግናለሁ። ብሏል።



ጀግናዋ ሻለቃ ደራርቱ ቱሉ ደግሞ፤

ለተደረገልን ስጦታም ሆነ መስተ ንግዶ በእግዚአብሔር ስም በጣም እናመሰግናለን። የሁላችን ኃይል እግዚአብሔር በመሆኑ እኛም በእግዚ አብሔር ኃይል ሩጠን ይኸ ሁሉ በማምጣታችን በጣም ደስ ይለናል። በእግዚአብሔር ኃይል ነው ሁሉ ነገር የሚደረገው። ሩጫ ብቻ ሳይሆን ሁሉም ነገር በእሱ ኃይል ስለሆነ ይህ ስጦታ ለእኛ በጣም ትልቅ ነገር ነው። ዛሬ እኛ በጣም ነው ከመጠን በላይ የተደሰትነው። አጠቃላይ የቡድኑ አባላት በጣም ደስ እያለን ነው። በጣም እግዚአብሔር ይስጥልን» ብላለች።

እኔም ከዚህ በመቀጠል ጀግናዋ አትሌታችን ሻለቃ ደራርቱ ቱሉን ቀረብ ብዬ እንኳን ደስ ያለሽ አልኳት።

እሷም ቀበል አድርጋ እንኳን አብሮ ደስ አለን አለችን። አያይዤም አንቺ አሁን በማሸነፍሽ ምን ይሰማሻል? ስላት ደራርቱም ከደስታ በላይ ምንም ነገር የለም በጣም ነው ደስ ያለኝ አለች። (ከፊትዋ ደስታ እየተነበበ)

በመቀጠልም የኢትዮጵያ ኦርቶ ዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያደረገችላችሁ አቀባበል እንዴት አየሽው (ተመለከትሽው) አልኳት። ደራርቱ ቅድም እንደተናገርኩት በጣም ነው የሚያስደስተኝ። መቼም ይኼ መጽሐፍ ቅዱስ የሕይወት ማስተማሪያ ነው። አሁንም ደግሜ ደጋግሜ በእግዚአብሔር ስም አመሰግናለሁ። አለች። የተደረገላት አቀባበል በጣም አስገርሟታል። ከዚህ ጋር በማያያዝ የወደፊቱ ዕቅድሽ ምንድነው? አልኳት

ደራርቱ ለዚህ በአጭር አገላለጽ እንዲህ ገልጻዋለች። በተቻለኝ መጠን አባታችን እንዳሉት የምናውቀውን ለማሳወቅ፣ የማናውቀውን ለማወቅ በሃይማኖቱም በኩል በሩጫውም በኩል ያው ለመቀጠል ነው በእግዚአ ብሔር ኃይልና ፈቃድ።

ኤድስን ለማቆም ምን ማድረግ አለብን ብየ ላቀረብኩላት ደራርቱ እንዲህ ትላለች፤ እንግዲህ እኛም ድርሻችንን ለመወጣት ሕዝቡን መንገር ነው። ቅዱስነታቸው እንዳ ሉት በትክክል ሕዝቡም ያዳምጣል። አሁንም እየሠራን ነው በሬድዮም፣ በቴሌቪዥንም እየተላለፈ ነው። አሁ ንም በተቻለ መጠን ከዚያ በላይ ለማስ ተማር ነው ሐሳባችን ስትል ተናግ ራለች። እኔም ጊዜው በጣም የተጣ በበና እንሂድ የማለት የመኪና ክላክስ እየጮኸ ስለነበር ለወጣቱ የምታስተ ላልፈው መልእክት ምንድነው ስል ለመጨረሻ ጠየኳት።

ደራርቱም የማስተላልፈው መል እክት ቢኖር በመጀመሪያ ደረጃ ወጣ ቶች ራሳቸውን ከኤድስ እንዲከላከሉ መምከር ነው። ወጣቱ ራሱን ከጠበቀ ችግሩ ይቃለላል፤ ትላልቆቹ ብዙ ያውቃሉ፤ ወጣቱ ግን የግድ መማር አለበት፤ ራሱን ከኤድስ መከላከል አለበት ነው የምለው። አለች እኔም እግዚአብሔር ይጠብቅሽ አልኳት ደራርቱም አሜን አለችና እሷ ወደመኪናዋ እኔም ወደ ሥራዬ ቀጠልኩ። ✣

www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሠዐጀሐሬት

## የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ከዋሽንግተን ዲ.ሲ.ተመለሱ

«ኤች.አይ.ቪ ኤድስን ለመቋቋም የሃይማኖት መሪዎች ሚና ምን መሆን አለበት» በሚል ርእስ በኋይት ሐውስ በተዘጋጀው ስብሰባ አጀንዳ ለመነ ጋገር በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የተመራው የልዑካን ቡድን ማክሰኞ ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ምሽት ላይ ወደ አሜሪካ አምርቶ በዋሽ ንግተን ዲ.ሲ.ኋይት ሐውስ ተደርጎ በነበረው ስብሰባ በመገኘት ተልዕኮውን ካከናወነ በኋላ ኅዳር ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም በሰላም ተመልሷል።

የልዑካኑ ቡድን ወደ አሜሪካ ሊሔድ የቻለው ክቡር የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ቢል ክሊንተን ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ባደረጉላቸው የክብር ጥሪ መሠረት ነው።

ቅዱስነታቸው ረቡዕ ኅዳር ፳ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ከፍራንክፈርት በሉፍታንዛ አየር መንገድ ተጉዘው በሀገሩ ሰዓት አቆጣጠር ከቀኑ ፮:፴ ሰዓት ዋሽንግተን ዲሲ አሜሪካ እንደ ደረሱ ብፁዕ አቡነ ማትያስ በዩ.ኤስ.ኤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ከየአቅጣጫው የመጡትን ካህናትና ምእመናን በመያዝ ከፍተኛ አቀባበል አድርገውላቸዋል።

በቬርጂኒያ እስቴት በሚገኘው አውሮፕላን ማረፊያ የተደረገው የአቀባበል መርሐ ግብር እንዳበቃ ሃያ አምስት ኪሎ ሜትር ያህል በመኪና ጉዞ በማድረግ ለማረፊያው ወደተዘጋጀላቸው ቦታ እንደደረሱ በዚያም አቀባበል ተደርጎላቸዋል። ከየአቅጣጫው ለአቀባበል የመጡትንም ካህናትና ምእመናን አንድ ባንድ አነጋግረዋል። በዚህም ጊዜ በኅዳር ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ስለሚከፈተው ጉባኤ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለሥልጣናት ጋር ተነጋግረዋል።

ከላይ እንደተገለፀው ኅዳር ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ከዓለም ዙሪያ የመጡት የሃይማኖት መሪዎችና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በተገኙበት በሜይ ፍላወር ሆቴል አዳራሽ በተደረገው አጠቃላይ ስብሰባ የክቡር ፕሬዚዳንት ክሊንተን ቀ·ወካይ እንኳን ደኅና መጣችሁ በማለት ንግግር አድርገዋል።

ከዚህ በኋላ በቀረበው አጀንዳ መሠረት ውይይቱ ቀጥሎ ከዓለም ዙሪያ የመጡት የሃይማኖት መሪዎችና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ኤድስ በአፍሪካ፣ ኤድስ በእስያ በአጠቃላይም ኤድስ በዓለም ዙሪያ እያደረሰ ስላለው እልቂት በየተራ እየተነሡ ሐሳባቸውን ገልፀዋል።

በይቀጥላልም ይኸው አስከፊ ደዌ በአፍሪካ፣ በተለይም በደቡብ አፍሪካ እያደረሰ ያለውን እልቂትና መካነ መቃብሩን አጉልቶ የሚያሳይ ፊልም በጉባኤው እንዲታይ ተደርጓል።

በዚሁ ዕለት የፊልሙ እይታ እንዳበቃ የጉባኤው ተሳታፊዎች በተዘጋጀላቸው አውቶቡስ ጉዞ ካደረጉ በኋላ በኋይት ሐውስ የመሰብሰቢያ አዳራሽ የትውውቅ ፕሮግራም ተደርጎ ስለ ኤድስ የተጀመረው ውይይት ቀጥሏል።

በዚህም መሠረት ኤድስን በሚመለከት ያለውን አጠቃላይ ችግር በየፈርጁ አጥንቶ ለውጤት ማብቃት አስፈላጊ በመሆኑ ጉባኤ ያተኞቹ በሦስት ግሩፕ ተከፋፍለው ጥናቱ በስፋትና በጥልቀት ተካሒዶ እንዳበቃ የሪሲፕሽን ግብዣ ተደረገ።

ከዚህ በኋላ በመርሐ ግብሩ መሠረት በኋይት ሐውስ አቅራቢያ ወደሚገኘው የሰማዕቱ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በማምራት እግዚአብሔር አምላካችን ሕሙማኑን እንዲፈውስ፣ ነፍሳተ ሙታንን ሀገረ ሕይወትን መንግሥተ ሰማያትን እንዲያወርስ፣ ሕያዋኑን እንዲጠብቅ፣ በአጠቃላይም ለዓለሙ ሁሉ ሰላሙን እንዲሰጥ የማኅበር ጸሎት ተጸልዮ እንዳበቃ ለማረፊያ ወደተዘጋጀው ሜይ ፍላወር ሆቴል መልስ ሆኖአል።

ኅዳር ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ከጠዋቱ በ፫ ሰዓት በዋሽንግተን ከተማ ዳርቻ ወደሚገኘው ሐዋርድ ዩኒቨርስቲ በአውቶቡስ ጉዞ በማደረግ ጉባኤያተኞቹ በዩኒቨርስቲው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ከተገኙ በኋላ ከየአቅጣጫው ከመጡት መካከል የተጋበዙት ሊቃውንት ኤድስን በተመለከተ ንግግር አድርገዋል።

በዚሁ ዕለት ከቀኑ ፫ ሰዓት ሲሆን በዩኒቨርስቲው ቅጽረ ግቢ ባለው ቤተ ክርስቲያን ሁሉም እንደተሰበሰበ የዩኤስኤ ፕሬዚዳንት ክሊንተን በስብሰባው ቦታ በመገኘት በዓለም የኤድስን ስርጭት አስመልክተው ስብሰባው በኋይት ሐውስ የተደረገበትን ምክንያት በዝርዝር፣ በስፋትና በጥልቀት አስረድተዋል።



ፕሬዚዳንት ክሊንተን ወደ ሕዝቡ መጥተው ንግግር ከማድረጋቸው በፊት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖትንና ሌሎችንም የሃይማኖት መሪዎች ተቀብለው እያንዳንዳቸውን በግል አነጋግረዋል። በዚህም ጊዜ ቅዱስነታቸው ለፕሬዚዳንቱ ስጦታን አበርክተዋል።

በሐዋርድ ዩኒቨርስቲ በኩል የተያዘው መርሐ ግብር ፍጻሜ እንዳገኘ ወደ ሜይ ፍላወር ሆቴል መልስ ሆኖ ጠቅላላው የጉባኤ አባላት በተገኙበት ውይይቱ ከቀጠለ በኋላ ከአሜሪካ ታዋቂ ተናጋሪዎች መካከል እነ ሬቨረንድ ጀሲ ጃክሰንና ሌሎችም ተናጋሪዎች ኤች.አይ.ቪ ኤድስን በተመለከተ ሰፊ ገለፃን አድርገው እንዳበቁ የጉባኤው ፍጻሜ ሆኗል።

በዚሁ ዕለት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት በአሜሪካ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት አምባሳደር ብርሃነ ገብረ ክርስቶስን ተቀብለው አነጋግረዋል።

ከዚህ በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ቀዳሚት ኅዳር ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም በቬርጂኒያ እስቴት ዋሽንግተን ዲ.ሲ አጠገብ ባለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አቡነ አረጋዊ ቤተ ክርስቲያን ከጡዋቱ ፲፪ ሰዓት ተገኝተው ኪዳን አድርሰው፣ ቀድሰው አስትምረው ሕዝበ ክርስቲያኑን አንድ ባንድ አነጋግረዋል።

ቅዱስነታቸው ከላይ ወደ ተጠቀሰው ቤተ ክርስቲያን እንደደረሱ ብፁዕ አቡነ ማትያስ በዩ.ኤስ.ኤ. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ጽንሐሕና መስቀል አሲዘው ምእመናንና ምእመናት በሆታ፣ በእልልታ፣ ካህናት በዝማሬና በቅኔ፣ የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በመዘመር የደመቀ አቀባበል አድርገውላቸዋል።

ከዚህ በኋላ የቅዱስነታቸውን መምጣት የሰሙ ሁሉ ከአራቱ ማዕዝናት በመምጣት የጸሎተ ቅዳሴው ተካፋዮች በመሆን ቡራኬን ተቀብለዋል። ሌሎችም ከኒውዮርክ የመጡ አራት ሦስት አፍሮ አሜሪካዊያን በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት አምነው በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቀው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባላት ሆነዋል።

ከቅዳሴው ሥነ ሥርዓት ፍጻሜ በኋላም ከየአቅጣጫው የመጡት በቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ በሚገኘው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ስለ ቅዱስነታቸው ክብር በተዘጋጀው የምሳ ግብዣ ላይ ተገኝተዋል። በዚህም ጊዜ እያንዳንዱ ባለጉዳይ እየቀረበ መስቀል እየተሳለመ የደስታውን ስሜት ገልጿል፤ መመሪያም ተቀብሏል።

በቬርጂኒያ እስቴት ባለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አቡነ አረጋዊ ቤተ ክርስቲያን ስም የተያዘው ፕሮግራም እንዳበቃ ቅዱስነታቸው ዋሽንግተን ዲ.ሲ.ወደሚገኘው ሜይ ፍላወር ሆቴል በመጡበት አኳኋን ተመልሰዋል።

በዚሁ ከላይ በተጠቀሰው ዕለት ማለትም ቀዳሚት ኅዳር ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ከቀኑ ፲፩ ሰዓት ሲሆን ቅዱስነታቸው በዋሽንግተን ዲ.ሲ ወደሚገኘው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ኤምባሲ ጽ/ቤት በመሄድ በአምባሳደር ብርሃን ገብረ ክርስቶስ አማካይነት አዲሱን የኤምባሲውን ጽ/ቤት ቢሮ አንድ ባንድ ተዘዋውረው ጎብኝተዋል። በይቀጥላልም አምባሳደሩ ለቅዱስነታቸው ክብር በመኖሪያ ቤታቸው የዕራት ግብዣ አድርገውላቸዋል። ከዚያም ቅዱስነታቸው ለማረፊያ ወደተዘ ጋጀላቸው ቦታ ሜይ ፍላወር ሆቴል ተመል ሰዋል።

ከዚህ በኋላ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የተመራው የልዑካን ቡድን ኅዳር ፳፬ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ከቀኑ ፲፩ ሰዓት ሲሆን በሉፍታንዛ አየር መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ጉዞውን ቀጥሎ ሰኞ ኅዳር ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ከምሽቱ በ፬ ሰዓት ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ደርሷል።

ቅዱስነታቸው ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ እንደደረሱ

ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ወኤጲስ ቆጶሳት

የጠቅላይ ቤተ ክህነት የየመምሪያ ኃላፊዎች

ካህናትና መዘምራን የላቀ አቀባበል አድርገውላቸዋል።

በዚህም ጊዜ ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ሠራተኞችና ለሌሎችም ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ስለ ተልዕኮው ሁኔታ ሰፋ ያለ መግለጫ ሰጥተው ወደበትረካናቸው በሰላም ገብተዋል።

አባ ገሪማ

የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት

የውጭ ግንኙነት የበላይ ኃላፊና

የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ሊቀ ጳጳስ

## በአሥር አኅጉረ ስብከት ሰሚናር ተካሄደ

የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ለ፲፱፻፺፪ ዓ.ም እና ለ፲፱፻፺፫ ዓ.ም በያዘው የሥራ ዕቅድ መሠረት በዘንድሮ ዓመት ከኅዳር ፩–፳፰ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ድረስ ባደረገው የሥራ እንቅስቃሴ በሰባቱ አኅጉረ ስብከት በሰባት የሰሚናር ማዕከላት በተሳካ ሁኔታ ሴሚናር አካሂዷል።

እነዚህ ሰሚናር የተካሄደባቸው አኅጉረ ስብከት በሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት በወልድያ ከተማ፣ በዋሕግ ሕምራ ሀገረ ስብከት በሰቆጣ ከተማ፣ በደቡብ ትግራይ ሀገረ ስብከት በማይጨው ከተማ፣ በመቀሌ ሀገረ ስብከት በመቀሌ ከተማ፣ በትግራይ ምሥራቃዊ ዞን ሀገረ ስብከት በዓዲ ግራት ከተማ፣ በትግራይ ማዕከላዊ ዞን ሀገረ ስብከት በአክሱም ከተማ፣ በትግራይ ምዕራባዊ ዞን ሀገረ ስብከት በሽሬ እንደ ሥላሴ ከተማ ሲሆኑ፤

በእነዚህ ትምህርታዊ ሰሚናሮች ላይ ከየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ በርካታ ካህናት ዲያቆናት፣ መምህራነ ወንጌልና የሰንበት ትምህርት ቤቶች ወጣቶች ተካፋዮች በመሆን ትምህርቱን በንቃትና በከፍተኛ መንፈሳዊ ስሜት የተከታተሉ መሆናቸውንና በተለይም በኤድስ ዙሪያ ስለተማሩት ትምህርት እጅግ እንዳረካቸው በመግለጽ ትምህርቱም ቀጣይ እንዲሆን በርካታ ጥያቄዎች መቅረባቸውን ሰሚናሩ ከተካሄደባቸው አህጉረ ስብከት ከተላኩልን ዘገባዎች ለመረዳት ችለናል። በዚህ ስምሪት ላይም ከልዑካኑ የተበረከቱ ቅኔዎች ነበሩ፤

### ደቡብ ትግራይ ሀገረ ስብከት በማይጨው ከተማ የተበረከቱ ቅኔዎች

ከንቡረዕድ ክፍለ ዮሐንስ መኮንን

፩. ዑጽፍተ ልብሰ ወርቅ ዘቈፋዝ አድያሙ እንደርታ

በገቦ ደብረ ጽዮን ሰምዓት ምስለ ትርጓሜሃ ገፀንባብ

አምጣነ ይቤ ሰሎሞን ጉባዔ ሊቃውንት ጠቢብ

ተንስአ ሰሜን ዓዘቦ ወነዓ ደቡብ

ሃብተ ቡራኬሃሰ ለእንደርታ

እምቃለ ንባቡ ለይስሐቅ ወእምድምጸ ጳውሎስ ከመንህብ

ለዓለም

አመስፍሓሰ ክንፈሆሙ ሊቃውንተ ወንጌል አረጋብ

አሰረ ፍኖቱ ለንስጥሮስ በክርሰ ደመና ኢይትረከብ

እስመ ሆሳዕና ድንግል መድኃኒተ ኩሎሙ ሕዝብ

መብልዓ ደብረ ጽዮን ለአዕሩግ ወለሕፃናት ስቴ ሐሊብ

፪. ትእምርተ በገው ለይስሐቅ ምስለ ዕጕለ ነጌ፣

ክፍለ ደቡባዊ ትግራይ ስምዓ ትንሳኤሁ ለአልዓዛር

ሶበ ከመ ባህርይ ነበርኪ በርዕሰ ርትዓን እድባር

ሐመልማለ ገነት ክሂለ ርዕሰ

እሕመልመልኪ ወተመሰልኪያ ለዘአሮን በትር

www.ethiopianorthodox.org

እምጣነ ውእቱ ብርሃንኪ!

እግዚአብሔር ስቡሕ በምክረ ቅድሳን እንበለ ነውር።

ለዓለም

ማይጨውሂ እመዓዘበ አርምሞትኪ መንከር

እምጣነ ኢኮንኪ ማየጼው እንበለ ጸእሙ ዘትረ መዓር

ወእመ ተደለወ ለኪ ተንከተመ ጳውሎስ ፍቅር

አስተማስሎኪ ነቢያት ዕፀ ደብረ ሲና ደብረ ታቦር።

፫. እመ አስተጋባእኪ ሕልፈ ዘበቤተ መረዓ

ዓረቦነ ጸጋ ወጽድቀ አፍራሰ ወልደ እሞጽ ትጼዓኒ

ታቦተ መስዋዕቱ ለይቤሐቅ ወልደ አብርሃም መሆኒ

ለጨርጨር ወለአለማ መድኃኒተ ኩኒ

እምጣነ ጨርጨር ወአጣማ!

መዋረስተ ገበዓን ድኅኑ በኪዳን ቃልኪ ኢ.ማሳኒ።

ለዓለም

ይቤለኪስ ገባሬኩሉ ዘዓለማተ ኩናኒ

ከመ አራጎራጎከኒ-በእንደርታ በመድረ አዘቦ አራጎራጎኒ

እስከ እመ ትቤ ማገፈጨው ለባሲተ መስቀል እሉኒ

ለአምላከ ጳውሎስ እሴብሖ እምጣነ ምሕረቱ ቀጸበተኒ።

ይህ በዚህ እንዳለ በ፲፱፻፺፪ ዓ.ም ከሚያዝያ ፳፯ ቀን እስከ ግንቦት ፴ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም በሰሜን ምዕራብ ሸዋ፣ በቦረና፣ በደቡብ ወሎ፣ በእጋዴን በድሬዳዋ አጎራረ ሰብከት ተመሳሳይ ስምሪት መደረጉ የሚዘነጋ አይደለም።

## ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ የተሰጠ መግለጫ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሐዋርያዊት እንደመሆኗ ፍትሕ መንፈሳዊ በሚያዘው ቀኖና መሠረት ቅዱስ ሲኖዶስ በዓመት ሁለት ጊዜ እየተሰበሰበ ውሳኔ የሚሰጥ ሲሆን ከዚህም ጋር ጊዜ የማይሰጥ ጉዳይ ሲያጋጥም አስቸኳይ ጉባኤን በማድረግ ውሳኔ ያሳልፋል።

በዚሁ መነሻነት ከጥቅምት ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ሱባኤ የመጀመሪያውን ዓመታዊ ስብሰባ በማድረግ በ፲፱፻፺፪ ዓ.ም በቤተ ክርስቲያኒቱ የሥራ ዘርፍ ስለተከናወኑትና ወደፊትም መከናወን ስለሚገባቸው አጠቃላይ ጉዳዮች ሲወያይ ሰንብቷል።

ውይይቱም የተካሔደው

፩ኛ. ባለፈው ዓመት የተከናወነውን ሥራ ለመገምገምና የወደፊቱን ዕቅድ ለመንደፍ እንዲቻል ከቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት የቀረበውን ሪፖርት በማዳመጥ፤

፪ኛ. ጥቅምት ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ስለሚፈጸመው የግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ፍልሰተ አፅም ሥርዓተ ቀብር መርሐ ግብር አፈጻጸም በመወያየት፤

፫ኛ. በተለያየ ምክንያት ከሀገራቸው ወጥተው ከእናት ቤተ ክርስቲያናቸው ተለይተው በሰው ሀገር የሚገኙት የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ንስሐ ገብተው ወደ ሀገራቸው ተመልሰው በሰላማዊ መንገድ ድርሻቸውን እንዲያበረክቱ የሰላም ጥሪ በማስተላለፍ፤

፬ኛ. ከሀገር ውጭ ከሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አህጉረ ስብከት ከቀረበው ሪፖርት አስፈላጊው ይፈጸም ዘንድ ትኩረት በመስጠት፤

፭ኛ. አሥራ ዘጠነኛው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ያሳለፈው የጋራ መግለጫና ውሳኔ ተስተካክሎ ለቋሚ ሲኖዶስ ይቀርብ ዘንድ መመሪያን በመስጠት፤

፮ኛ. በክልል ትግራይ ስለሚገኘው የከሳቴ ብርሃን ሰላማ መንፈሳዊ ኮሌጅ አመሠራረትና በጀት አመዳደብ፤

፯ኛ. ለዓለም ኅብረተሰብ ጠንቅ ሆኖ ጎልቶ ከሚታየው ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ ለመከላከል ስለተሰጠውና ስለሚሰጠው ትምህርት ተግባራዊነት፤

፰ኛ. የ፲፱፻፺፫ ዓ.ም በጀትን በተመለከተ ከመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የቀረበውን ሪፖርት በመመልከትና በማጽደቅ፤

፱ኛ. በአጠቃላይም ቤተ ክርስቲያኒቱ ስለምትፈጽመው መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት የቀረበውን ሪፖርት በማዳመጥና መነሻ በማድረግ፤

ቅዱስ ሲኖዶስ ከዚህ በላይ ከ፩–፱ ተራ ቁጥር በተጠቀሱት ነጥቦች በስፋትና በጥልቀት ከተወያየ በኋላ፤

የቤተ ክርስቲያናችን እምነትና ሥርዓት ተጠብቆ እንዲኖር

በሀገርና በመላው ዓለም ሰላም እንዲሰፍን

ፍቅር አንድነት እንዲስፋፋ

መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት እንዲዳብር

በአጠቃላይም ቤተ ክርስቲያናችን ደረጃ በደረጃ ማደግ እንድትችል ውሳኔ ሰጥቷል።

እግዚአብሔር አምላካችን ለሀገራችንና ለዓለሙ ሁሉ ሰላሙን፣ ለሕዝባችን ፍቅር አንድነቱን ይስጥልን።

አሜን!!

ጥቅምት ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ዘመናዊ አዳራሽ ተሠራ

የብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት ከ፯ ዓመታት የአዳራሽ እጥረት በኋላ አቶ ወልደጊዮርጊስ ይዘንጋው በተባሉ ባለጸጋ ከ፰ መቶ ሺህ (ስምንት መቶ ሺ ብር) በላይ በማውጣት ለሰንበት ት/ቤቱ በውስጡ ልዩ ልዩ የቢሮ ክፍሎችና ቤተ መጻሕፍት የያዘ ዘመናዊ አዳራሽ አሠርተው በ፲፭/፩/፲፱፻፺፫ ዓ.ም ከቀኑ ፯:፴ ሰዓት ላይ የቤተክርስቲያን አባቶችና እንግዶች በተገኙበት ተመርቆ ተከፍቷል።

❖❖❖

# እስትጉቡእ

(እስትጉቡእ - ጥርቅም፣ የተቀመመ፣ የተሰባሰበ ማለት ነው)

## የጎሩይ ጊዮርጊስ ደብር አመሠራረት

ጎሩይ ጊዮርጊስ ከደብረ ታቦር ከተማ በግምት ከ፭ ኪሎ ሜትር ርቀት የሚገኘው፣ በአሠራሩ ልዩ የሆነ፣ አፄ ዮሐንስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ያሠሩት ደብር ነው። የአፄ ዮሐንስ ለምድ፣ ዙፋን፣ በአፄ ዮሐንስ ዘመን የነበረ የኢትዮጵያ ባንዲራ በዚሁ ደብር ይገኛል።

ጎሩይ ጊዮርጊስ የበለጸገው በታሪክ እና ቅርስ ብቻ አይደለም። በቅዱስ ያሬድ ደቀ መዛሙርትም ደምቋል።

ስብሐተ እግዚአብሔር ከዓመት ዓመት አይቋረጥም፣ ዘወትር ይደርሳል።

ደቀ መዛሙርቱ በየቦታው ሆነው ቃለ እግዚአብሔሩን ሲናገሩ ለሰማ ሰው በሕሊናው አንድ ነገር ይሰማዋል። እሱም ኢየሩሳሌም ሠማያዊትን ያስታውሳል።

ዛሬ በጎሩይ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ደቀ መዛሙርት የድጓ ደቀ መዛሙርት ፵፯

የዝማሬ እና መዋሥዕት ደቀ መዛሙርት ፲፯


የአቋቋም ተማሪዎች ደቀ መዛሙርት ፲፫ በድምሩ ፹፯ ደቀ መዛሙርት ይገኛሉ።

በዛሬ የእስትጉቡእ አምድ የዚህ ታላቅ ደብር አመሠራረት ይዘንላችሁ ቀርበናል።

ጎሩይ ማለት «ጎረየ» ካለው የተመረጠ ምርጥ ማለት ነው። የጎሩይ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተው በአፄ ሰይፈ ያርእድ ነው። ዘመኑ ፩ሺህ ፪፫ (አንድ ሺህ አንድ መቶ ሰባ) ይሆናል። የጎሩይ ጊዮርጊስ አትኝ ሸንኮር (የሰው ስም) ይባላል።

ሸንኮር ከማቅናቱ በፊት ጋሻጮች

፩ኛ. ግርሜ ፪ኛ. በጆ የሚባሉ ነበሩ። እኒህ ቢጋሻ እያሉ ሸንኮር አምስት ልጆች ይዞ ከሸዋ መርሐ ቤቴ መጣ። የልጆቹ ስም ዝርዝር ፩ኛ. ክፍለ ማርያም ፪ኛ. ዘማርያም ፫ኛ. ላሐ ማርያም ፬ኛ. መክፍለተ ማርያም ፭ኛ. መዓዛ ገነት የሚባሉትን ልጆቹን ይዞ ከመጣ በኋላ ጎሩይ ጊዮርጊስ ሲደርስ ታቦተ ሕጉን የጊዮርጊስን ፅላት በመያዝ ቤተ መቅደሱን ሸንኮር መሠረተ። ከመሠረተም በኋላ ዳንኤል በተባለ ሐናጺ ቤተ መቅደሱን በደብተራ አራት አምሳል በኖራ፣ በግንብ ቤተ መቅደሱና



ዙሪያው ተሰርቶ ቆይቷል። ዛሬም ለቅርስ ያህል በቤተ ክርስቲያኑ በሰሜን በኩል ኖራ ግንብ ይገኛል።

ከዚህ በኋላ ስዩመ እግዚአብሔር ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የተባሉት በአክሱም ጽዮን ዘውድ ደፍተው ከነገሡ በኋላ ለሀገር ሰላም ለመከላከልና ለመጐብኘት ከመቀሌ ወደ ጐንደር ደብረ ታቦር አየር ማረፊያ አቁና ከተባለው ቦታ ደርሰው በድንኳን ከአደሩ በኋላ ወደ ጎሩይ ጊዮርጊስ ደረሱ።

ጎሩይ ከደረሱ በኋላም በጎሩይ ጊዮርጊስ መካከል ስመራ ከምትባል ተራራ ደረሱ፣ ስመራ የተባለችው በግራ በቀኝ ጅረቶች እና ሰላሳሰባት ምንጮች፣ የበርና የወርቅ ማንጠሪያ አፈር ያለባት በመሆኑ ይህች ማን ትባላለች? ብለው አፄ ዮሐንስ ጠየቁ፣ አባቶች «ስመራ» ትባላለች አሏቸው። አፄ ዮሐንስም «ዕፀ ብሩክ» ስመርናሃ እኛም ወደድ ናት አሉ። በኋላ በዚያ ስመራ በሚባለው ቤተ መንግሥታቸውን መሠረቱ፣ ብምሥራቅ በኩል እራስ ሐጎስን፣ በሰሜን በኩል እራስ ገብረ መስቀልን፣ በደቡብ በኩል እራስ ኃይለ ማርያምን፣ በቤተ መንግሥታቸው ዙሪያ ፩ኛ. ደጅ አዝማች ገድሉን፣ ፪ኛ ደጅ አዝማች ይመርን፣ ፫ኛ ደጅ አዝማች ወንዴን የመሳሰሉትን ደጅ አዝማቾች እና መሳፍንቶችን በመያዝ ቤተ መንግሥታቸውን ከመሠረቱ በኋላ ከግብፅ ፩ኛ. እጨጌ ቴዎፍሎስን ፪ኛ. አቡነ ማቴዎስን፣ ፫ኛ. አቡነ ማርቆስን፣ ፬ኛ. አቡነ ሉቃስን፣ ፭ኛ. አቡነ ጴጥሮስን ግብፃውያን ሊቃነ ጳጳሳትን ወደ ኢትዮጵያ አመጡ።

የእጨጌ ቴዎፍሎስ ቦታ አፄ ቴዎድሮስ መድፉን ከአሠሩበት አካባቢ ጋፋት ከሚባለው ግቢያቸውን መሠረቱ። ከዚህም በኋላ አፄ ዮሐንስ መሐንዲስ ከግሪክ ሙሴ ናርቲ የተባለውን አስመጥተው የጎሩይ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንን በ፲፰፻፸፪ ዓ.ም እንዲጀመር አደረጉ። የቤተ ክርስቲያኑ ፕላን በግሪክ ይሁን በኢትዮጵያ ይሁን አይታወቅም። የመሀንዲሱ መለኪያ ሜትር ዛሬም በቦታው ይገኛል። ቤተክርስቲያኑን ከሰሩ በኋላ የገዳም መዓርግ ሲሰጡ ዳሩ እሳት፣ መሐሉ ገነት በማለት በአምስት ሊቃነ ጳጳሳት፣ በአራት መቶ መነኮሳት፣ በአምስት መቶ ሊቃውንት፣ በብዙኅ ሠራዊት ለመምህር አፈ መምህር፣ ለማኅበር መጋቢ፣ በበቅሎዩ በገበዙ ትዳኝ በማለት በመምህር ሀብተ ገብርኤል በመምህርነት «እስመ መምህረ ሕግ» ተብሎ ተሰብኮ ደብረውታል (ገዳም አድርገውታል)። በኋላም መተዳደሪያ ሰጥተዋል።

፩ኛ. ከወንጀል መቀጫ፣ ከጥቁር ደም እሸር (ቅጣት) ከሚባለው ሲሶ እበል ለደብሩ ሰጥተዋል። የገበያ ቀረጥ ሲሶ እበል ሰጥተዋል፣ አራት ደብሮች ለጊዜው በማለት ፩ኛ. ሰላምኮ ጊዮርጊስ ፪ኛ. ጌራ ተክለሃይማኖት ፫ኛ. ማገሬ ማርያም ፬ኛ. ድንስር ጎጥ የሚባሉት በሙሉ እምቾ(ክፍያ) እበል እንዲከፍሉ እና ቅፈፋ እንዲሆኑ አዘዋል፣ ወስነዋል።

ለቤተ መቅደሱ ፅላቶችን፣ የብራና መጻሕፍቶችን፣ የብር መስቀሎችን፣ አልባሳትን፣ ቅርሶች ወዘተ የመሳሰሉትን ንዋየ ቅድሳትን ሰጥተው ይገኛሉ።

የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በወርቅ አንበሳ ምስል የተሠራ መያዣው የብር ጉብ ጉብ የሆነ፣ በዘመነ መንግሥታቸው የነበረው ሰንደቅ ዓላማ በዚሁ ደብር ይገኛል። ሌላው፣ ፩ኛ. አፄ ምኒልክን ንጉሥ ብለው አንድ ጳጳስ ሰጥተው ለሸዋ ክፍለ ሀገር፣ ፪ኛ. ንጉሥ ተክለሃይማኖት ብለው፣ አንድ ጳጳስ ሰጥተው ለጎጃም ክፍለ ሀገር፣ ፫ኛ. ንጉሥ ሚካኤል ብለው አንድ ጳጳስ ሰጥተው ሾመዋል። ስያሜውን የሰጡት ቦታ ጃንሆይ ሜዳ ይባላል። ልዩ ስሙ አደባባይ ተብሎ ዛሬ ስሙ ይጠራል። አፄ ዮሐንስ ንጉሠ ነገሥት ሊያስኙቸው የቻለ ነገሥታቱን በውስጣቸው በመሾማቸው ነው። ይህን ከአደረጉ በኋላ በጀግንነታቸው ስም «ለበዝበዝ ካሳ» የጎንደር ሊቃውንት ደብዳቤ ሃፉላቸው ደብዳቤው የሚለው «እግዚአ ቦእ አህዛብ ውስተ ርስትከ ወአርኩስዋ ለጎንደር ከመልገተ አቃቢ ቀምህ» ብለው ቢጽፉላቸው ወዲያውኑ ሠራዊታቸውን ይዘው ዘመቱ፣ በመተማ ላይ በድርቡሽ እንገታቸውን እንደ ሰማእታት ተሰውተዋል። እጨጌ ቴዎፍሎስም አብረው ተሰውተዋል። ቀብራቸውም በመተማ ሆኗል። ዛሬም መቃብራቸውም ላይ የምንጭ ውኃ ይፈልቃል፣ ድውያንን ይፈውሳል ከረጅሙ በአጭሩ የአፄ ዮሐንስ ታሪክ ይህን የመስላል።

❖

የጀርባ ፎቶ መምህር ዕንቁባሕርይ ተከሥተ

ፈለገ ጥበብ

www.ethiopianorthodox.org